ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
ንግሥተ-ጽዮን ወንግሥተ-ነገሥታት ዘኢትዮጵያ።

---

# ልዑል እግዚአብሔር፡

## ከረዥም ዘመናት በኋላ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፤ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፥ በሰማይ እና በምድር ፍጥረታተ-ዓለማቱም ኹሉ፤ በኢትዮጵያዊው የእግዚአብሔር እውነት እና የመንፈስ-ቅዱስ ሥርዓተ-አምልኮ፤ ለ፯ሺ፭፲፩ ዓመታት፡ ከጥር ፳፰ እስከ፴ ቀን ለሚከበረው ለዘንድሮው የ፳፻፲፩ (፪ሺ፲፩) ዓመተ-ምሕረቱ

# በዓለ-ኢትዮጵያ፤

## እንኳን፡ በደኅና እና በሰላም አደረሰን! በያለንበትም፡ ልንቀደስበት በቃን!

# በዓለ-ኢትዮጵያ

*[የበዓሉ፣ የምስጋናና የሓሜት ሥርዓተ-ጸሎት፣ ከዚህ መልእክት ጋር፣ ተያይዞ ይገኛል።]*

## በዓለ-ኢትዮጵያ፡ ምንድር ነው?

**በዓለ-ኢትዮጵያ፡** እውነተኞች የኢትዮጵያ ልጆች፡ **ለ፯ሺ፭፻፲፩ ዓመታት፡ ከእግዚአብሔር** እና የእግዚአብሔር ወገን ከኾኑት፡ በሰማይ እና በምድር ከሚኖሩት ፍጥረታተ-ዓለማቱ ኹሉ ጋር፣ በእያመቱ፡ ከጥር ፳፰ እስከ፴ ቀን ድረስ ባሉት ሦስት ቀኖች ውስጥ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ የሚያከብሩት በዓል ነው።

አዎን! ይህ በዓለ-ኢትዮጵያ፡ **"እግዚአብሔር ቆመ፡ ውስተ ማኅበረ አማልክት፤ ወይኴንን በማእከለ አማልክት።** እግዚአብሔር፡ በአማልክት ማኅበር ውስጥ ተገኝቶ ቆመ! ተቀምጦም፡ በአማልክቱ መካከል ይፈርዳል።" እንዲህ ሲል፦ **"አንሰ እቤ፡ 'አማልክት አንትሙ! ወደቂቀ ልዑል ኵልክሙ!** እኔም እላችኋለሁ፦ እናንተ፡ አማልክት ናችሁ! ኹላችሁም፡ የልዑል እግዚአብሔር ልጆች ናችሁ።" ብለው፡ የቀደሙት ነቢያት፡ ይናገሩት የነበረው ነው። (መዝ. ፹፩፥ ፩-፯።)

ደግሞም፡ "እግዚአብሔርን፡ በሃይማኖት እናውቀዋለን!" የሚሉት፡ አይሁድ፥ ክርስቲያኖችና እስላሞች፣ እንዲሁም፡ ባዕዳኑ አረማውያንና አሕዛብ ኹሉ ሳይቀሩ፣ ጥንታውያኑ የግሪክ ፈላስፎች ጭምር፡ ***"እግዚአብሔር አምላክ፡ ከሰማየ ሰማያት ወርዶና በመካከላቸው ተገኝቶ፡ የተቀደሰ በዓላቸውን፡ ዐብሯቸው የሚያከብርላቸው ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት!***" እያሉ ይጽፉት የነበረው እውነታ ነው፡ ይህ በዓለ-ኢትዮጵያ።

አዎን! በከባድ የክህደት ኃጢኣቱ ምክንያት፡ ከሥጋዊው እና ከምድራዊው የዓለም ኅብረተሰብ፡ ለአያሌ ዘመናት ተሠውሮ የኖረው፡ ያ **በዓለ-ኢትዮጵያ** ነው፡ ዛሬ፡ እነሆ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** እንደገና ተከሥቶና ተገልጾ፥ እውን ኾኖም እየተከበረ ሲፈጸም የሚታየው።

እኒያ የቀድሞዎቹም ኾኑ፣ እኒህ የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የዚህኑ በዓላቸውን አከባበር፡ **በኢትዮጵያዊው የእግዚአብሔር እውነት እና የመንፈስ-ቅዱስ ሥርዓተ-አምልኮ መሠረትነትና አማካይነት፣** በሥውርም፣ በገሃድም ሲፈጽሙት ኖረዋል። አኹንም፡ ይኸው ይፈጽሙታል። ወደፊትም፡ የሚፈጽሙት ኾኖ ይቀጥላል። ይህ፡ **በዓለ-ኢትዮጵያ፡** በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ የሚከበርበትን መልክና ይዘት፡ ከሌሎቹ፡ "የእግዚአብሔር አማኞች ነን" ከሚሉት ከባዕዳኑ፡ ሕዝቦችና አሕዛብ፣ ከጥንቶቹም፣ ከዛሬዎቹም የሚለየው፡ ይህ፡ የአምልኮ ባሕርዩ ነው።

"በሥውር" የተባለው፡- የበዓሉ አከባበር፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ባለውና ምንም ዓይነት ግዙፍ የመገልገያ መሣሪያ በማያስፈልገው፡ <u>በእውነተኛውና በመንፈሳዊው አምልኮ ብቻ መኾን ስላለበት ነው።</u> በዚህም ምግባር፡ **"ትመጽእ ሰዓት፤ ወይእዜ ይእቲ፤ አመ እለ በርቱዕ በአማን ሰጋድያን፡ ይሰግዱ ለአብ፡ <u>በመንፈስ፥ ወበጽድቅ፤</u> እስመ አብኒ፡ ዘከመዝ የኅሥሥ፡ እለ ይሰግዱ ሎቱ። እስመ እግዚአብሔር፡ መንፈስ ውእቱ፤ ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ፡ <u>በመንፈስ ወበጽድቅ፡</u> ሀለዎሙ ይስግዱ ሎቱ።'"**

"ያች ሰዓት መጥታለች፤ እርሷም፡ ይህች የአኹኗ ናት። በእምነትና በትክክል የሚያመልኩ ሰዎች፡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩት፡ <u>በመንፈስና በእውነት</u> ነው። እግዚአብሔር፡ እርሱን፡ በእግዚአብሔርነቱ የሚያመልኩት ኹሉ፡ እንዲህ፡ እንዲያመልኩት ይሻል። እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነውና፤ የሚያመልኩትም፡ <u>በመንፈስና በእውነት</u> ሊያመልኩት ይገባቸዋል።'" የሚለው፡ የመለኮት ቃል፡ ተፈጻሚ ኾኗል።

ከላይ እንደተወሳውና እንደተጠቀሰው፡ **እግዚአብሔር፡ በኢትዮጵያ ልጆች መካከል ተገኝቶ፡ ይህንኑ በዓለ-ኢትዮጵያን ዐብሯቸው የሚያከብረው፡** ከዚህ የተነሣ መኾኑ፡ በጥልቅ ግንዛቤ፡ ሊታወቅ ይገባል። (ዮሐ. ፬፥ ፳፫-፳፬።)

"በገሃድ" የተባለውም፡ ይኸው በዓለ-ኢትዮጵያ፡ ጊዜ ተወስኖለትና ተመድቦለት፡ በይፋ ሊፈጸም ስላስፈለገ ነው። ለምን፡ ይህ አፈጻጸም እንዳስፈለገም፡ ምክንያቶቹን፡ ባጭርም ቢኾን፡ እዚህ ላይ፡ መግለጹ፡ አስፈላጊ ይኾናል። ይኸውም፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ እያንዳንዱ የህልውናቸው ቅጽበት፡ በበዓለ-ኢትዮጵያ ምስጋናና ደስታ የተመላ መኾኑ ቢታወቅም፤ አኹን ግን፡ "በተለይ፡ በእያመቱ፡ ከጥር ፳፰ እስከጥር ፴ ቀን ድረስ ባሉት ሦስት ቀኖች ውስጥ፡ እንዲህ፡ በገሃድ እንዲያከብሩት አግባብ የኾነው፡ ለምንድር ነው?" ለሚለው ጥያቄ፡ ከዚህ የሚከተሉት እውነታዎች፡ መልስ ኾነው ቀርበዋል። እነዚህም፡-

በቀዳሚነት፡ ያ፡ የጥንቱ፤ የመሠረቱ ሥርዓት የቀጠለ መኾኑን፡ ለማሳወቅና ለማሳየት ነው።

ቀጥሎ፤ ይህንኑ **በዓለ-ኢትዮጵያን** በሚመለከት፡ በግንቦት ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓ.ም. የታወጀው፡ ፲፫ኛው ቁጥር መለኮታዊ የዐዋጅ ቃል፡ በተግባር ላይ መዋል ስላለበት ሲኾን፡ እውንነቱ እንዲህ፡ የሚረጋገጥበት ኾኗል።

ከዚህ ተከትሎም፡ በዓሉ፡ ለዚህ መለኮታዊ የዐዋጅ ቃል የበቃው፡ ይኸው፡ በዓለ-ኢትዮጵያ የሚውልበት ጊዜ፡ ባለፉት ዘመናት፡ "ጾመ-ነነዌ" እና "ጾመ-ኢትዮጵያ" በሚሉ ተከታታይ ስያሜዎች፡ በመደበኛነት ሲዘከሩበት የኖሩት ሃይማኖታውያኑ ምግባራት፡ የሚፈጸሙበት ስለነበረ መኾኑ ይታወቃል።

በመጨረሻም፡ እነዚህ ቊም-ነገሮች እንዳሉ ኾነው፡ ለእነርሱ ኹሉ ጭምር፡ መነሻ ኾኖ፡ በዋናነት የሚጠቀሰው፡ መሠረታዊው ምክንያት ደግሞ አለ፤ እርሱም፡ በፍጥረታተ-ዓለማቱ ዘንድ፡ እውነተኛ ማንነቱን፡ ለዝንተ-ዓለም፡ በምትሓታዊ ጥበቡ ሲለዋውጥ በኖረው ዲያብሎሳዊው መንፈስ የሚመራው፤ ክፉውና ከሃዲው፥ ዓመፀኛውና አመንዛሪው የፍጡር ወገን፡ ድብቅ ኾኖ ከኖረበት ጠንቀኛ ህልውናው፤ አኹን፡ በግዱ ተከሥቶና ወጥቶ፡ መጋ ለጡ ብቻ አይደለም።

ነገር ግን፡ በእግዚአብሔር ፀርነቱ፡ በፍጥረት ላይ ላደረገው ጥፋትና ላደረሰው ጉዳት፡ በተጠያቂነት፡ ተገቢውን የፍርድ ዋጋ እንዲቀበልበት፡ በሃይማኖታዊ ተስፋ ሲጠበቅ የኖረው ጊዜ፡ በትክክል፡ ይህ የምንገኝበት ዘመን መኾኑ፡ ተረጋግጦ የታየበት መኾኑ ጭምር ነው።

ስለዚህ፡ በዓለማዊ ጥበቡና በሥጋዊ ሥልጣኔው የታበየው፡ ይኸው ፀረ-መልካሙ ወገን፡ ከዚሁ ተቃራኒ አቋሙ የተነሣ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ላይ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ ሲያካኺድ የኖረውን፣ ይህንኑ የተፃራሪነት ዘመቻውን እያጠናከረ ኺዶ፡ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ፡ ጽዋው ሞልቶ፣ ሊፈስስ የተቃረበበት፣ እርሷን፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን**ም ሊደመስስበት ባከማቸው ኃይሉ ኹሉ፡ ራሱን፡ በራሱ ሊያጠፋ የሚጣደፍበት በኾነበት፡ በዚህ ጊዜ፡ አንድ መለኮታዊ ትንግርት ታየ። እርሱም፡ ይህ ነው፡-

ይህችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ተፃራሪዋ ወገን፡ በቀንደኛነት ለሚመራው፡ ለዚሁ ፍጥረተ-ዓለም፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ መሪዎቿ ባለቤትነትና የዐዋጅ ቃል፡ ራሷን ገልጣ፡ የፈጣሪነትና የቸርነት ሥራዋን፡ ከማንነቷ ጋር፡ በገሃድ ለማሳየት፣ ለትንቢቱ መፈጸሚያም፡ ተገቢው ጊዜ መድረሱንና ብቁው መድረክ ኾኖ መገኘቱን ለማረጋገጥ፡ **በዓለ-ኢትዮጵያ፡ እንዲህ፡ በይፋ እንዲከበር፡ ፈቃደ-እግዚአብሔር ኾነ።**

# በበዓሉ የሚካኼደው፡
# የሓሤቱና የምስጋናው አፈጻጸም ሥርዓት።

በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** የሚካኼደው፡ ይህ **የበዓለ-ኢትዮጵያ አከባበር ሥርዓት፡** በመላው የዓለሙ ሕዝቦችና አሕዛብ ዘንድ፣ "ኢትዮጵያ" በሚለው ስም፡ በምትታወቀው ምድር ሳይቀር፡ ሲካኼድ እንደሚታየው፡ እንደእነርሱ፡ እንደዓለማውያኑና እንደሥጋውያኑ የተለያየ ባዕድ የበዓል አከባበር ልማድ፡ የሚፈጸም አይደለም።

አዎን! በአንድ በኩል፡ ሥጋዊ በኾነው ጌጣጌጥ በማሸብረቅ፥ በሥጋዊው መብልና መጠጥ፥ ዘፈንና ጭፈራ በመደሰት፣ ለዚሁ ሥጋዊ ደስታ፣ አምልኮ ባዕድንም ለመፈጸም ሲባል፣ ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸውን፡ እንስሳትንና የአዕዋፋት ወገኖች የኾኑትን ዶሮዎችን በማረድ፥ እንዲህ፡ የሥጋ ፍላጎትን በማርካት፣ <u>ሥጋዊ በዓልን፡ ለብቻ ማክበር አይደለም።</u>

በሌላ በኩል ደግሞ፡ ***"ከትብኻዎች ከፍተኛ የገቢ ምንጭን ለመፍጠር!"*** በሚል ዓላማ፡ እንግዳ የኾነ፡ የገንዘብ ማሳደድ ዘመቻን በማካኼድ ጭምር፡ መንፈሳዊዉን ማኅሌትና ምስጢረ ቅዳሴን በማርከስ፡ <u>**መንፈሳዊ በዓልን፡ ለብቻ ማካኼድም**</u> አይደለም።

**በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** የሚካኼደው፡ ይህ **የበዓለ-ኢትዮጵያ አከባበር ሥርዓት፡** ከእነዚያ፡ ከሥጋውያኑም፣ ከመንፈሳውያኑም፡ ከኹለቱም ዓይነቶች፡ የበዓል አከባበር ሥርዓቶች፡ በተለየ ኹኔታ፡ የኹለቱንም፣ የሥጋዊዉንም፥ የመንፈሳዊዉንም የበዓል አከባበር ሥርዓቶች አቀነባብሮና አቀናጅቶ፡ አንድ በሚያደርግ መልክና ይዘት፡ ግርግርና ትርምስ የሌለበት ኾኖ፡ በሥጋዊው፥ በነፍሳዊውና በመንፈሳዊው፡ በአጠቃላይ ኹለንተናው፡ በውስጣችን በሚሰማን፡ በፍጹም ጸጥታና ሰላም፣ ደስታና ሓሤት፥ ለፈጣሪያችንም በምናቀርበው ምስጋናና ለሌላው የተፈጥሮ ወገናችን በምናበረክተው በጎ አገልግሎት ተካኺዶ፡ በአንድ አካልነትና በአንድ ባሕርይነት የሚፈጸም ነው እንጂ።

አዎን! ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን ኹሉ፡ አንድ አድርጎ ለሚያዋሕደው፣ ለዚሁ፡ ለበዓለ-ኢትዮጵያ አከባበር ሥርዓታችንም፡ ዘለዓለማዊዉንና መለኮታዊዉን ዘውድ አቀዳጅተን፡ እንድንቀድስበትና እንድንሸልምበት፣ ከፈጣሪያችን ተዘጋጅቶ የተሰጠን፡ ታላቅ ጸጋ አለን። ይኸውም፡ የሰውነትን ነፍስና ሥጋ፥ መንፈስንም፡ አንድ ከሚያደርገው፡ ከእግዚአብሔር የበዓል ድግሥ ገበታ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለሰላም ቤዛ መስቀሉ፡ ከምሥ ዋዕ መድኃኒታችን፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣውን፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በመሳተፍ የምንቀበልበት፡ የቅዱስ ቊርባን ሥርዓት ነው።

እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ በበዓለ-ኢትዮጵያ ዕለት፡ ይህን ሃይማኖታዊ ምግባር በምንፈጽምበት ጊዜ፡ እንቀደስበታለን፤ እንሸለምበታለንም። ከዚህ የተነሣ፡ የበዓለ-ኢትዮጵያ አከባበራችን፡ ከመጀመሪያው እስከማብቂያው፡ ያማረና የሠመረ ይኾንልናል።

ከግለሰቡና ከቤተሰቡ ዝግጅት አንሥቶ፡ እስከብሔረሰቡ፣ ከዚያም፡ እስከሰማይና ምድር፡ ኀብረ-ዓለማት-ዐቀፉ ድረስ፡ እግዚአብሔር፡ በመንበረ-ቅድስት ሥላሴነቱና በመንፈስ ቅዱስነቱ ክብር፡ በምልዓት የሚገኝበት በመኾኑ፡ አዎን! **በዓለ-ኢትዮጵያ፡** ከሰብኣዊውና ከፍጡራዊው የበዓል አከባበር፡ በተለየና ራሱን በቻለ መልክ ተካኺዶ የሚፈጸም ነው።

በእነዚህ ሦስት ዕለታት፡ የመላዎቹ ፍጥረታተ-ዓለማት፡ ነዋሪ የኾነው ፍጡር ኹሉ፣ ይልቁንም፡ ሰብኣዊው፣ በይበልጥም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ወገን፡ ወንዱም፣ ሴቱም፡ በነፍስ ወከፍ ኾነ፡ በኅብረት፡ የሚያደርገው ነገር አለ።

ያም የሚያደርገው ነገር፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ መገለጫ ለኾነችው፡ **ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** <u>የሚያቀርበውን፡ የፍጹም ምስጋናውን ውለታ፡ ራሱ፡ በውስጡ በሚሰማው፡ በፍጹም ደስታው ገልጦ ማሳየት ብቻ ይኾናል።</u>

ይኸውም፡ በዓሉ ተለይቶ የሚታወቅበትንና የሚከሡትበትን፣ አዎን! ውብና ዕፁብ፣ ድንቅና ግሩም አድርጎ፡ በራሱ መልክና ባሕርይ የፈጠረው፣ የሰማይና የምድር መኖሪያውንም፡ እንዲህ አሳምሮና አስጊጦ፣ አሟልቶና አትረፍርፎ ያዘጋጀለት፡ ረቂቅ መንፈስ የኾነው አምላኩ፡ በሥነ-ፍጥረትና በሰውነት ገዝፎ የተገለጠባት፡ እርሷ፡ ራሷ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** በመኾኗ ነው።

ሥፍር ቍጥር የሌለው መልካም የተደረገለት ፍጡር፡ ሴቱም፥ ወንዱም፡ ይህን ኹሉ ላደረገችለት፡ **ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**፡ ሊያበረክተው የሚቻለው፣ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን እና እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን የኾነችው፡ እርሷ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**፡ በእርካታ ልትቀበለው የምትፈቅደው፡ ሌላ፡ ከዚህ የበለጠና የተሻለ፡ የምስጋና ስጦታና ገጸ-በረከት፡ በሥነ-ፍጥረት ዘንድ፡ ምንም ነገር፡ ከቶ የለም። **እግዚአብሔር፡ የሚቀበለው፡ ስጦታና ገጸ-በረከት፡ የለም እንጂ፡ ቢኖር ኖሮ፡ ደስ ብሎት የሚቀበለው፡ የምስጋና ስጦታና ገጸ-በረከት ፡የፍጡሩን ደስታ ብቻ ነው።** አዎን! **የሚቀበለው፡ የፍጡሩን ደስታ ብቻ ነው።**

ይኸውም፡ በአንድ በኩል፡ እንስሳትና አራዊት፣ አዕዋፋትና ዓሣት፡ ለፈጣሪያቸው፣ በሌላው በኩል ደግሞ፡ የሥጋ ወላጆች፡ ለሕፃናት ልጆቻቸው እንደሚኾኑት ኹሉ፡ ማለት ነው። በውኑ! ወላጆች፡ ለሕፃናት ልጆቻቸው ለሚያደርጉላቸው በጎ ነገር፡ ከእነዚሁ፡ በጎ ካደረጉላቸው ሕፃናት ልጆቻቸው፡ ምስጋናን ይሻሉን? ፈጽመው አይሹትም፤ ተፈጥሮም፡ በውስጣቸው ስላላኖረችላቸው፡ መሻቱ፡ በአሳብ እንኳ አይመጣላቸውም።

እዚህ ላይ፡ "**ወሶበ እንዘ እኩያን አንትሙ፡ ተአምሩ ሠናየ ሀብተ፡ ውሂበ፡ ለውሉድክሙ፣ እፎ ፈድፋደ አቡክሙ ዘበሰማያት፡ ይሁብ ሠናየ፡ ለእለ ይስእልዎ?**

"እናንተ፡ በሰውነታችሁ የባሕርይ ምርጫ ምክንያት፡ ክፋዎች ስትኾኑ፡ ለልጆቻችሁ፡ መልካሙን ስጦታ ብቻ የምታደርጉላቸው ከኾነ፣ በባሕርዩ፡ ፍጹም ደግ የኾነው፡ የሰማዩ አባታችሁማ፡ ለእናንተ ለፍጡራን ልጆቹ፡ የሚያደርግላችሁ መልካሙ ስጦታ፡ እንዴት የተትረፈረፈ አይኾንም?" የሚለው፣ ኀሊናን የሚተረኵስ፣ መለኮታዊ ቃል፡ ትዝ ይላል። ይህ፡ ረቂቅ የመንፈስ እውነታ፡ በአንደበት ኾነ፣ በጽሕፈት ቃላት ሊገለጽ፡ ፈጽሞ አይቻልም። (ማቴ. ፯፥ ፲፩።)

እንግዲህ፡ የመላዎቹ ፍጥረታተ-ዓለማት፡ ነዋሪ የኾነው፡ በተለይ፡ ሰብአዊው ፍጡር፡ ሕያው ኾኖ መንቀሳቀስና በሕይወት የመኖር ህልውናውን መቀጠል ካስቻሉት፣ ከሚያስችሉትም፡ ከነፋሱና ከፀሓዩ፥ ከውኃውና ከመሬቱ ጋር፡ ሌላውን የሚያስፈልገውንም ኹሉ፡ ያለማቋረጥ፡ እንዲያገኝ ከማድረግ ጀምሮ፡ በተትረፈረፈ ምልዓት ያበረከተችለት፣ አኹንም እያበረከተችለት ያለችውና ወደፊትም የምታበረክትለት፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** መኾኗን፡ በተፈጥሮውም፥ በሃይማኖቱም፡ አረጋግጦ ያውቃል።

አዎን! እውነታውን፡ እንዲህ ስለሚያውቅ፡ ከላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሠረት፡ በተሰጠው በዚህ ጸጋው፡ በግሉ፡ ደስታውን እየፈጸመ፤ ምስጋናውን፡ በዚሁ ደስታው አማካይነት፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም መለኮትነትና ትስብእትነት፡ በአንድነትና በሦስትነት የተገለጡት፡ የፈጠሩት፡ እግዚአብሔር ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ የተቀበሉለት መኾኑን ዐውቆና አምኖ፡ ደስታውን፤ ወደሓሤት [ወደፍጹም ደስታ] ከፍ አድርጎ፡ በዚሁ ሓሤቱ መቀጠል ይጠበቅበታል።

ይኸው፡ የበዓለ-ኢትዮጵያ አከባበርና ሓሤቱ፡ ከግል፥ ወደጋራ ተሻግሮ፡ ባልና ሚስትን እና ጓደኞችን፤ ከዚያም፡ ልጆችን የሚያካትተውን ቤተሰብንና ኅብረተሰብን በመሰሉ፡ ቊጥራቸው፡ በኹለትና በሦስት፥ ከዚያም በላይ በኾኑ ግለሰቦች መካከል የሚካኼድና የሚፈጸም ሊኾ ን ይችላል።

በዚህ ጊዜና በዚህ እውነታ፡ እግዚአብሔር ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ የኾነችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ በመካከላቸው ስለምትገኝ፤ "**እስመ ኀበ ሀለዉ ...እምኔክሙ... ክልኤቱ ወሠለስቱ፡ ጉቡአን በስምየ፤ ህየ፤ ሀለውኩ አነ ማእከሎሙ።** ...ከእናንተ፡...ኹለት፤ ሦስት ኾነው፡ በስሜ በተሰበሰቡበት፡ በዚያ፡ እኔ እገኛለሁ።" የሚለው፡ መለኮታዊው የተስፋ ቃል፡ እውን ኾኖ መፈጸሙ ይረጋገጣል። "እግዚአብሔር፡ በኢትዮጵያ ልጆች መካከል ተገኝቶ፡ በዓለ-ኢትዮጵያን፡ ዐብሯቸው ያከብራል!" የሚለው፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የነቢያቱና የጥንታውያኑ፡ የዓለም ፈላስፎች ንግርም፡ በዚሁ መለኮታዊ የተስፋ ቃል፡ ዐብሮ ይጸድቃል። (ማቴ. ፲፰፤ ፲፱-፳።)

<u>**የበዓሉ ማክበሪያ ቦታ፡-**</u> በየግልም፤ በቤተሰብም፤ በኅብረተሰብም ደረጃ የሚካኼደው፡ የበዓለ-ኢትዮጵያ አከባበራችን፡ ኪዳናዊው የኢትዮጵያዊነት መንፈሳችን የሚያሳስበንንና የሚመራንን በመከተል፡ ከቤታችን ጀምሮ፡ የተመቻቸና የሚቻል ኾኖ በሚገኝበት፤ በያለንበትና በማናቸውም ቦታና ኹኔታ ሊፈጸም ይቻላል።

<u>**የበዓሉ መገለጫ ጸሎት፡-**</u> የግልም ኾነ፤ የማኅበር ጸሎታችን፡ በሙሉ፡ ከልመናና ከምልጃ፤ ከምሕላና ከአቤቱታ፤ ከኀዘንና ከትካዜ ፈጽሞ የነጻና የጠራ ኾኖ፡ የምስጋናና የደስታ መገለጫዎች በኾኑት፡ በስባሔና በውዳሴ፤ በቅዳሴና በአኰቴት፥ በማኅሌትና በይባቤ ብቻ የተሞላ ይኾናል። እርሱም፡ በጽሑፍም፤ በድምፅም ተዘጋጅቶ፡ ከዚሁ መልእክት ጋር ተያይዞ ይገኛል።

<u>**የበዓሉ አለባበስ ባህል፡-**</u> አለባበሳችን፡ ኢትዮጵያዊዉን ብሔራዊ የበዓል አለባበስ ባህል የተከተለና የትንሣኤ ብርሃን ልጆች መኾናችንን የሚያመላክተው፡ ጸዓዳው ነጭ ያገር ልብስ ቢኾን ይመረጣል።

<u>**የበዓሉ ድግሥ ዝግጅት፡-**</u> የመብል መጠጥ ግብዣችን፤፡ ከጾም ግዴታ፡ ነጻ የኾነ ምርጫን የተጎናጸፈ የፍስክ ኾኖ፡ በየፈቃዳችንና በየፍላጎታችን ላይ የተመሠረተውን፤ ለመንፈሳዊው የብቅዓት ደረጃ የደረሰውንም፡ የጾምና የፍስክ ሥርዓታችንን የተከተለ ይኾናል።

# በዓለ-ኢትዮጵያ፡
# በዚህ መልኩና ይዘቱ እንዲከበር ያስቻለው፡
# መለኮታዊው ፈቃድና ውሳኔ።

**በዓለ-ኢትዮጵያ፡** በአኹኑ ዘመን፡ በእነዚህ ሦስት ቀናት፡ በዚህ መልኩና ይዘቱ ሊከበር የበቃው፡ ለምን እና እንዴት እንደኾነ፡ ይህንኑ ርእሰ-ነገር በሚመለከት፡ **ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡-**

አንደኛ፡ በየካቲት ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት፡ በቍጥር ፲፩/፳፻፰፣

ኹለተኛ፡ በግንቦት ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ-ምሕረት፡ በቁጥር ፲፫/፳፻፰፡ ለፍጥረታተ-ዓለማቱ፡ በይፋ በተላለፉት፡ ኹለት መለኮታውያት ዐዋጆች ውስጥ የሠፈሩት ቃላት ያስረዳሉ። እነርሱንም፡ ከዚህ በታች በማከታተል ጠቅሰናቸዋል።

## የመጀመሪያው የዐዋጅ ቃል፡ እንዲህ ይላል፡-

**"እኔ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም፡...** እስካኹን ሳሰማችሁ የቆየሁትን፡ መግለጫዬንና ማብራሪያዬን፥ ምክሬንና ማሳሰቢያዬን መሠረት በማድረግ፡ ይህን፡ የአኹኑን፡ መለኮታዊዉን የዐዋጅ ቃሌን፡ እንዲህ እያልሁ ዐሳውቃችኋለሁ፡-

"እናንተ፡ የእኔ፡ የቅዱሱ ኪዳን "ኢትዮጵያ ልጆቼ" የኾናችሁት፡ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት፡ **በ"ጾመ-ኢትዮጵያ"** እና **በ"ሰላም ለኢትዮጵያ" ምሕላዎቻችሁ አማካይነት፡** በእነዚያ፡ በአለፉት የአርባ ዓመታት የንስሓ ዘመን ውስጥ፡ በያላችሁበት የፈጸማችሁት ሃይማኖታዊ ምግባራችሁ፡ ልክ፡ እንደዚያ፡ እንደተነሳሒው [በንስሓ እንደተመለሰው] የነነዌ ሕዝባችን ኹሉ፡ እናንተም፡ እየራሳችሁን፡ ያን ለመሰለው፥ እኛ ለተቀበልነው፡ እውነተኛ ንስሓ አብቅታችሁ አግኝተናችኋልና፡ ደስ ይበላችሁ!

"ባለፈው በዐሥረኛው መለኮታዊ ዐዋጃችን ላይ እንደተገለጸው፡ **ወይሰበክ ዝ ወንጌለ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ ከመ ይኩን ስምዐ፡ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ። ወይእተ አሚረ፡ ይበጽሕ ኅልቀት።**

"ለአሕዛብም ኹሉ፡ ምስክር እንዲኾን፡ ይህ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥራች፡ በዓለም ኹሉ ይሰበካል። በዚያን ጊዜ፡ መጨረሻው ይመጣል።" ባለው፡ በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ቃል መሠረት፡ የተጻፈውንና የተነገረውን፥ የደረሰውንና የኾነውን ዐውቃችሁታል።

"ይኸውም፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ በእኛ፡ በቅድስት ሥላሴ ፈቃድ፡ እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የመሠረትናትና የገለጥናት፥ የምንመራትና የምንጠብቃት፥ የምንመግባትና የምንቈጣጠራት፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ምስክር ይኾንባቸው ዘንድ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ የምሥ ራች ዜናዋና መልእክቷ፡** በቃልና በጽሑፍ ብቻ ሳይኾን፡ በጎዋው የብዙኃን መገናኛ አውታሮች ሳይቀር፥ በሰፋድልና በተንቀሳቃሽ የሥዕል መጽሔቶች ጭምር ተሠራጭቶ፡ እነሆ፡ ለመላዎቹ የዓለም ሕዝቦችና አሕዛብ ኹሉ እየተሰበከ በመካኼድ ላይ በመኾኑ፡ ያ የመጨረሻው ጊዜ የመድረሱ ምልክት እየታየ መኾኑ ሊታበል፡ ከቶ አይቻልም። (ማቴ. ምዕ. ፳፬፥ ፲፬።)

"ከዚህ የተነሣ፡ የዛሬ ኹለት ሽህ ስምንት ዓመታት፡ በእኔና በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሰውነት፡

"-በዚህ፡ በምድራዊውና በሥጋዊው ዓለም ላይ፡ ገዝፋና ተከሥታ የታየችው፥

"-በዚህ እውን ህልውናዋም፡ የነፍስና የሥጋ፥ የመንፈስም ሥራዋንና አገልግሎቷን፡ በገሃድ አካኺዳ ያከናወነችው፥

"-እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በምድር ላይና በሰብአውያን ፍጡሮቻችን መካከል፡ የመጣንበትን ተልእኳችንን፡ ከፈጸምን በኋላ፡ ወደሰማያት ዐርገን፡ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነታችን ተመልሰን፡ በመላው ፍጥረተ-ዓለም መልተን፡ በአባትነትና በእናትነት፥ በሊቀ -ካህናትነትና በቤተ ክህነትነት፥ በንጉሠ-ነገሥትና በንግሥተ-ንግሥታትነት እየመራናትና እየጠበቅናት፥ እየመገብናትና እየተቈጣጠርናት ያለችው፡ ይህችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡**

"-በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆቻችን በቀር፡ በሌሎቹ ሃይማኖታውያንና ድርጅቶቻቸው ዘንድ ኹሉ፥ "ክርስቲያኖች ነን!" በሚሉት ዘንድ ሳይቀር፡ ተትታና ተጥላ፥ እንዳልነበረችና እንደሌለችም እንድትቆጠር ከማድረግ ጋር፡

"-በረThም ዘመን ምስጢራዊ ሴራቸው ሲጠና በኖረው ዕቅዳቸው፡ የመጨረሻ ድምሳሴዋን፡ ከግብ ለማድረስ፡ ዘመቻቸውን እያጠናከሩ ባሉበት፡ በዚህ፡ በአኹኑ ጊዜ፡

"-እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ-ምሕረት፡ ባሰማነው፡ በመጀመሪያው መለኮታዊ ዐዋጃችን፡ እየራሳችንን፡ በእውን በመግለጽ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያን** መኖር፡ በይፋ ለማስታወቅ የወሰንነው፡ ከዚሁ፡ ከ"ጾመ-ኢትዮጵያ" እና ከ"ሰላም ለኢትዮጵያ" የአርባ ዓመታት የምሕላ ጸሎታችሁና የሱባኤ ጾማችሁ በተገኘው እውነተኛ ንስሓችሁ ብቅዓት በመኾኑ፡ ደስ ይበላችሁ!

"አዎን! ከዚህ የተነሣ፡ የዛሬ ኹለት ሽህ ስምንት ዓመታት፡ መላውን ምድራዊ ፍጥረተ-ዓለም፡ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ ይቅር ባልንበት፥ እንግዴህ ወዲህም፡ በእኔና በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ መለኮታዊ እውነትነትና መንፈስ ቅዱሳዊ የአምልኮ ሥርዓታችን፡ የሰማይና የምድር ፍጥረታተ-ዓለማቱን የምትመራውና የምትጠብቀው፥ የምታስተዳድረውና የምትቈጣጠረው **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** በተገለጠችበት፡ ኪዳነ-ምሕረታችን፡ እነሆ! ዛሬም፡ እናንተን፡ ኹላችሁንም፡ ከየኃጢአታችሁ፡ ይቅር ብለናችኋልና፡ ደስ ይበላችሁ!

"በዚህ፡ በእናንተ፡ የአርባ ዓመታት የንስሓ ብቅዓታችሁም ምክንያት፡ ዐፅመ-ርስቴ የኾነችውንና እስካኹን፡ በስሜ የተጠራችውን፥ እናንተም፡ "አገራችን" ስትሏት የኖራችሁትን፡ የኢትዮጵያን ምድር፥ ርስት ጕልቴ ከኾናችሁት፡ ከእናንተ፡ ከሕዝቤ ጋር፡ ከየኃጢአታችሁ፡ ይቅር ብለናችኋልና፡ ደስ ይበላችሁ!

"እናንተን ብቻ ሳይኾን፡ በእግዚአብሔር እም'ነቴ [እናትነቴ]፡ ተወዳጇና ታማኙ አገልጋዬ የኾነው፥ በድንግል ማርያም ትስብእትነቴም፡ ምዝላቴ የኾነውና "ኢትዮጲስ" በሚለው ስሙ፡ እኔን፡ "ኢትዮጵያ" አሰኝቶ ያስጠራኝ፡ መልከ-ጼዴቅ፡ በቈረቈራትና በሠራት፥ በሚስቱ፡ በልጃችን፡ በሳሌምም ስም፡ "ኢየሩሳሌም [ሀገረ-ሰላም]" ብሎ በሰየማት፡ በዚያች በተቀደሰች ከተማችን፥ በይሁዳና በገሊላ፥ በቀሩትም አውራጃዎቿ ኹሉ የምትኖሩትን፥ እንዲሁም፡ በመላው ዓለም የሠፈራችሁትን፡ የቃል ኪዳን ልጆቻችንንና የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን የኾናችሁትን ኹሉ፡ በእኛ በኩል፡ ኃጢአታችሁን ኹሉ፡ ይቅር ብለናልና፡ ደስ ይበላችሁ!

"እንግዴህ ወዲህ፡ በዚህ፡ የኪዳነ ምሕረት ዐዋጃችን ምክንያት፡-

"በቀዳሚነት፤ ባለፉት መለኮታውያን ዐዋጆቻችን፥ በተለይም፡ በዐሥረኛው ዐዋጃችን በኩል የተነገረውን በመፈጸም፡ እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ዐብቅታችሁ የተገኛችሁ ኹሉ፡ የዚህ፡ የኪዳነ ምሕረታችን፡ የይቅርታ ታላቅ ጸጋና በረከት ተቀባዮች የመኾን ዕድል ብቻ ሳይኾን፡ በእያንዳንዳችሁ ላይ፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም፡ ሊመጣባችሁ ከሚችል፡ ከማናቸውም፡ የተፈጥሮም ኾነ፥ የሰው-ሠራሽ ጕዳትና ጥፋት፡ የመዳናችሁ ዋስትና የተረጋገጠ ኾኖላችኋል።

"በዳግምነት፤ 'ጾመ ኢትዮጵያ' እና 'ሰላም፡ ለኢትዮጵያ' በሚሉ ስያሜዎች፡ በየዓመቱ መንፈቆች፡ በየካቲት ወርና በጳጕሜ ይፈጸም በነበረው፡ ሃይማኖታዊና ምግባራዊው፡ የጾምና የጸሎት ሥርዓታችሁ የተካኼደው፡ የአርባው ዓመታት የምሕላ ሱባኤ፡ መለኮታዊ የኾነውን፡ የይቅርታና የምሕረት ፍሬያማ መልሱን ስላስገኘ፡ አብቅቷል።

"ከዚህ የተነሣ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንና እኛ መሪዎቿ፡** እኔ እግዝእተብሔር እም፡ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፥ እኔም፡ ወልደ አብ፡ ወልደ ማርያም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ በገሃድ የመገለጣችን እውነታ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት፡ ይፋ በወጣው፡ በ፩ኛው ቍጥር፡ መለኮታዊ ዐዋጃችን እንደተነገረ ታውቃላችሁ።

"ስለዚህ፣ ይኸው እውነታም፡ እስከዚህኛው እስከ፲፩ኛው ቊጥር ድረስ ባሉት፡ መለኮታውያት ዐዋጆቻችን በመረጋገጡና በመጽናቱ፡ ካኹን በኋላ፡ **በእናንተ በኩል ሊቀ ርብልን የሚገባው፥ እኛም፡ የምንቀበለው ቊርባን፥ ልመናና ምሕላ ሳይኾን፡ የምስጋና ጸሎትና የሓሤት ዝማሬ ብቻ ይኾናል።**

"የጳጉሜው ጾም፡ እንደነበረው፡ በጾምነቱ፡ በጊዜው የሚፈጸም ኾኖ፡ በዓመቱ እኩሌታና ማብቂያ፡ "ጾመ-ኢትዮጵያ" እና "ሰላም ለኢትዮጵያ" ተብለው፡ ለአርባ ዓመታት፡ ሲዘከሩ የቆዩት፡ የጾምና የጸሎት ጊዜያቶች፡ በአንድነት ተጠቃልለው፡ በዓመቱ እኩሌታ፡ ከሰኞ እስከ ረቡዕ፡ ባሉት የሦስት ዕለታት፡ ‹**በዓለ-ኢትዮጵያ!**› ተብሎ፡ በየዓመቱ፡ በእነዚሁ ሦስት ቀኖች፡ የሚከበር ይኾናል።"

## ኹለተኛው፡ የዐዋጅ ቃል፡ እንዲህ ይላል፡-

"**እኔ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም፡...** የዓመቱን አጽዋማትና በዓላት በሚመለከት፡ በተለይ፡ የእኛ፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ሕያው ቅርስ ኾኖ የኖረውን ሥርዓት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ልጆቻችንና ነጋሢዎቻችን፥ ካህናት አገልጋዮቻችንም ለኾናችሁት፡ ለእናንተ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከዚህ በሚከተለው የዐዋጅ ቃሌ አሰማችኋለሁና፡ ሰምታችሁ የምትፈጽሙት ይኹን!

"በቅድሚያ፡ የእኔ፡ የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና የልጄ የወዳጄ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የኾኑትን፡ እነዚህኑ፡ የዓመቱን አጽዋማትና በዓላት፡ የእኛ ልጆቻችን፥ የእናንተም፡ የቀደሙት ምዝላቶቻችሁ የኾኑት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በእየራሳቸው አሳቢነትና ወጣኝነት፥ ፍላጎትና ፈቃድ፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው አማካይነት፡ ለዝንተ-ዓለም፡ ሲጾሟቸውና ሲያከብሯቸው እንደኖሩ ታውቃላችሁ፤

"ቀጥሎ፡ እንደእነርሱ ኹሉ፡ እናንተም፡ የዛሬዎቹ ልጆቻችን፡ እስካኹን፡ በውስጣችሁና በየግላችሁ፡ እንዴት ስትጾሟቸውና ስታከብሯቸው እንደኖራችሁ፡ በእየራሳችሁ ትገነዘቡታላችሁ፤

"በመጨረሻ፡ እነዚሁ አጽዋማትና በዓላት፡ በዓመቱ ዑደታቸው ጊዜ፡ እንዲውሉባቸው የተደረጉትን ዕለታት፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ አቋም ለመቀበል፡ የቱን ያህል ያዳግታችሁ እንደነበረ ታዘክሩታላችሁ።

"ከዚህ የተነሣ፡ እናንተም፡ እንግዲህ ወዲህ፡ እነዚህኑ አጽዋማትና በዓላት፡ በዓመቱ ዑደታቸው ውስጥ፡ ይጾሙባቸውና ይከበሩባቸው በነበሩት፥ በእነዚያዎቹ፡ በትክክለኞቹና በመደበኞቹ ቀኖቻቸው፡ ከዚህ በሚከተለው ሥርዓት መሠረት፡ መጾማችሁንና ማክበራችሁን ትቀጥሉ ዘንድ፡ ይህን ማሳሰቢያ፡ በእኔው የዐዋጅ ቃል፡ እንድትሰሙት፡ አስፈላጊ ኾነ።

"ይኸውም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ራሷን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ገልጣ፡ ቸርነቷን በይፋ ማካኼድና መፈጸም በጀመረችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ዘንድ፡ ያንኑ፡ የኪዳናውያኑንና የኪዳናውያቱን ምዝላቶቻችሁን ፈለግ ተከትላችሁ የምታደርጉት፡ ያው ሥርዓት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል። ...

በዚህ መሠረት፡ "ከ**ጥር ፳፰ እስከ፴ ቀን**፤ ያሉት፡ እነዚህ፡ ሦስት ቀኖቿ፡ በያመቱ ይለዋወጡ የነበረችው፥ ከሰኞ እስከረቡዕ ያሉት፡ ተከታታይ ዕለታቷ ግን ሳይለዋወጡ፡ ትፈጸም የነበረችው፡ የቀድሞዋ ጾም፡ "ጾመ-ነነዌ" ትባል እንደነበረ ታስታውሳላችሁ፤

"ኋላ በመካከሉ፡ ይህን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን፡ የዚህን ዘመን፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ አመንዝሪና ክፉ ትውልድ ሊቀ ጣ፡ የፍርድ ሠይፍን ታጥቆ የተላከው ደርግ፡ ከተነሣበት፡ ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ፡ በእናንተ በዛሬዎቹ፡ ታማኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቹ፡ ይህችው ጾም፡ **"ጾመ-ኢትዮጵያ"** ተብላ፡ ለአርባ ዓመታት፡ በሱባኤ ምሕላ መልክና ይዘት ስትጾም እንደቆየች ታውቃላችሁ፤

"ቀጥሎ፡ ይህችው፡ የሱባኤ ጾምና የምሕላ ጸሎት፡ ከፊታችን ደርሳ፡ የኪዳነ-ምሕረት ቸርነታችንን ጸጋ ስላስገኘች፡ ደርግ፡ ተልእኮውን እንዲያበቃ አድርገን፡ ከሥልጣን እንዳስወገድነው ትመሰክራላችሁ፤

"በመጨረሻም፡ የአኹኖቹም ተተኪዎች፡ በሥልጣን መሥራት እስኪጀምሩ ድረስ፡ በርስተ-ጒልት ምድራችንና በቃል-ኪዳን ሕዝባችን ላይ፡ አንዳች ጥፋትና ዕልቂት እንዳይደርስ ያደረግነውን **መለኮታዊ ጥበቃ** ታዘክራላችሁ፤"

ይህ **መለኮታዊ ጥበቃ፡** ምን ዓይነት እንደነበረ፡ ከዚህ ዐዋጅ በኋላ፡ **ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ከተላለፈ፡ ከሌላ መልእክት የተገኘውን ጽሑፍ፡ እዚህ ላይ፡ እንደሚከተለው ጠቅሰን አቅርበነዋል፡-

«ይኸውም፡-

«፩ኛ. Communism [ኮሚዩኒዝም] በሚባለው፡ የ"እግዚአብሔር የለም!" የምሥ ራቃውያን ባዕዳን፡ ሰይጣናዊ ፍልስፍና እየተመራ፡ የኃይልና የግፍ፥ የጭካኔና የጭቆና፥ የግድያና የጥፋት፥ የቅጣትና የመቅሠፍት አገዛዙን፡ ለ፲፯ ዓመታት ሲያካኼድ የቆየው፡ "ደርግ" የተባለው፡ አምባገነንና ግዙፍ ወታደራዊ ድርጅት፡

«-በተቃዋሚው፡ ጦር መሣሪያ ብልጫነትና በሠራዊት ብዛት ሳይኾን፡ **በፍቱኑ መለኮታዊ የቅዱሱ ኪዳን ጸጋና እውነት ተወግዶ፡**

«-በዚያው፡ የደርግ በኾነው፤ ነገር ግን፡ Democracy [ዲሞክራሲ] በሚባለው፡ በምዕራባውያን ባዕዳን መሠሪና ረቂቅ ***"የከፋፍለህና የለያይተህ"*** አመራርና አገዛዝ ፍልስፍና በተመሠረተው አንጃ በተተካ ጊዜ፡

«-ተፈጥሮ በነበረው መንግሥት-አልባ በመሰለው ክፍተት ውስጥ፡

«-ቀደም ብሎ፡ በአብዮትና በጦርነት ምክንያት፡ በመላዋ አገር፡ ያለሕግና ያለፍርድ፡ በእልፍ-አእላፋት ላይ፡ ከተፈጸመው የግፍ እስራትና ሥቃይ፥ ግርፋትና ግድያ የተነሣ፡

«-በሕዝቡ መካከል፡ በደመኛነትና በቂም በቀል ቁርሾ፡ **ሊደርስ ይችል የነበረው፡ ታላቅ የደም መፋሰስና የእርስ በርስ ዕልቂት፡ ታግዶ እንዲያልፍ የተደረገው፡** የቅዱሱ ኪዳን ባለቤት በኾነችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፣** የእርሷ መሪዎቿ በኾኑት፡ በእግዝእተብሔራችን እም፡ ድንግል ማርያም እና በእግዚአብሔራችን ወልድ ኢየሱስ መሲሕ አይደለምን? አዎን! ነው። ታዲያ! በማን መሰላችሁ!? ለመኾኑ፡ ይህን እውነታ የምታውቁ፡ ስንቶች ናችሁ?

«፪ኛ፣ በዚያኑ ጊዜ፡ መላውን፡ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ፣ ከነንብረቱ፣ ከቅዱሳት መካናቱ ጋር ጭምር፣ በአጠቃላይ፡ የኖረውንና "አለ!" የሚባለውን፡ ሕያዉንና በድኑን ቅርስ፡ እንዳለ፡ ጨርሶ በመደምሰስ፡

«-መናገሻ ከተማዋን፡ ባዶ አድርጎ፡ አዲስ የኾነ ከተማን፡ በዘመናዊ መልክ ለመመሥረትና በአዲስ ነዋሪዎች ለማቋቋም ሲባል፡

«-የሰይጣን ወገኖችና የባዕዳን መሣሪያዎች በኾኑ፣ ቂም-በቀልንም በተመሉ፡ ክፉዎች ሰዎች መሠሪነት፡ በምስጢራዊ ተንኮል ታስቦና ታቅዶ፡ በተግባር ላይ እንዲውል ተደርጎ የነበረው፡

«-በከተማይቱ፡ በውስጧ፥ በመካከሏና በዙሪያዋ ባሉት የጦር መሣሪያዎችና ፈንጂዎች ግምጃ ቤቶች፥ በነዳጅ ዘይት ጋኖችና ማከማቻዎች ላይ፡ "ኾን" ተብሎ፡ በዚያው ሰሞን እንዲፈነዳ፡ ተነጣጥሮና ተተርኵሶ የነበረው የእሳት ገሞራ፣

**«-ሊቀ ጣጠል እንዳይችል ተደርጎ፡ የተጠበቀውን አሠቃቂ ዕልቂት ሳያደርስ ሊጠፋ የበቃው፡ አኹንም፡ በማን መሰላችሁ?**

**«በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፣** የእርሷ መሪዎቿ በኾኑት፡ በእግዝእተብሔራችን እም፡ ድንግል ማርያም እና በእግዚአብሔራችን ወልድ ኢየሱስ መሲሕ አይደለምን? አዎን! ነው። ታዲያ! በማን መሰላችሁ!? ለመኾኑ፡ ይህን እውነታ የምታውቁ፡ ስንቶች ናችሁ?»

"በእነዚህ ኹሉ ትንግርቶች፡ **ልክ፡ የአርባው ዓመት፡ የጸረ-ኢትዮጵያ ሱባኤ ሲፈጸም፡ የቅጣቱ መከራ ዘመን አብቅቶ፡ እነሆ፡ የምሕረቱና የምሥ ራቹ ጊዜ የጀመረ መኾኑን የሚያበሥረው መለኮታዊው ዐዋጃችን፡ በእኔ ቃል እንደተነገረ፡** የተገነዘባችሁት፡ የቅርብ ጊዜ እውነታ ነው።

"ስለዚህ፡ እነዚህ ሦስት ዕለታት፡ በመላው ፍጥረተ-ዓለም፥ በተለይም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን ልጆቼ ዘንድ፡ በየዓመቱ፡ "በዓለ-ኢትዮጵያ" ተብለው፡ እንዳለፉት ዘመናት፡ **ቋሚዎቹ የጥር ፳፰ እስከ፴ ቀኖቻቸው፡** የሚለዋወጡ ሳይኾኑ፥ ዧሪ ዕለቶቻቸው፡ ሰኞ፥ ማግሰኞና ረቡዕ ግን፡ የሚለዋወጡ ኾነው፥ ጊዜያቸውም፡ የምሕላና የጾም ሳይኾን፡ በፍጹም የዝማሬና የማኅሌት ምስጋና፥ በታላቅ ኹለንተናዊ ሓሤት፥ በፋሲካ የአለባበስ ድምቀትና የድግሥ ሥርዓትም የሚከበሩ ይኾናሉ።"

# በዓለ-ኢትዮጵያ፡
# ከአያሌ ዘመናት በኋላ፡ የመጀመሪያ ለኾነው፣
# ለዚህ እግዚአብሔራዊ አከባበር ያበቃው
# የገድል ጕዞና ፍሬው።

የዚህን ንኡስ-አርእስት ፍሬ-ነገር፣ የዝክረ-ነገሩንም ዝርዝር፡ ጸመ-ነነዌንና ጸመ-ኢትዮጵያን፣ ሰላመ-ኢትዮጵያንና በዓለ-ኢትዮጵያንም በሚመለከት፡ ራሷ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ከላይ ፡ በአንደኛ ተራ ቍጥር በተጠቀሰው፡ በየካቲት ፲፯ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረቱ፡ ቍጥር ፲፩/፳፻፰ መለኮታዊ ዐዋጇ፡ የተናገረችውንና ተጽፎም የሚነበበውን፡ እንደገና፡ እንዳለ ማቅረቡን ስለመረጥን፡ ይህንኑ መለኮታዊ ቍም-ነገር፡ እንደሚከተለው አሥፍረነዋልና ተመልከቱት፡-

"እንዳለፈው፡ እንደ፲ኛው መለኮታዊ የዐዋጅ ቃሌ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እግዝእተብሔር እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመ-ቤታችሁና ምድረ-ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም ነኝ**።

## መቅድም።

"ካለፈው ዓመት አቻምና፡ ከነሓሴ ፲፯ ቀን፥ ፳፻፫ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ፡ በቅድሚያ፡ በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሢሕ፥ ከዚያም ተከታትሎ፡ በእኔ፡ በእናቱ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም በኲል፡ በተነገሩት የዐዋጅ ቃሎቻችን አማካይነት፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያን**፡ የህልውና ዝክረ ነገር በሚመለከት፡ መለኮታዊ እውነታውን፡ በይበልጥ፡ ለእናንተ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ልጆቻችን ብቻ ሳይኾን፡ ለቀረው፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍጥረታችን ኹሉ፡ በይፋ በመግለጥ፡ በየጊዜያቱ፡ የቃለ ዐዋድ መልእክቶቻችንን ስናስተላልፍላችሁ እንደቆየን ታስታውሳላችሁ።

"አኹን፡ እነዚያን የዐዋጅ ቃሎቻችንን መርሕ በመከተል፡ በእግዚአብሔር አብና በእኔው በራሴ፡ በእግዝእተብሔር እም፥ በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሢሕና ሕይወታችን በኾነው፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም፡ እንደገና፡ በአኹኗ ሰዓት፡ በዐዋጅ ቃሌ ላናግራችሁ፡ ይኸው መጥቼላችኋለሁ።

"ይገቡላችሁ የመጣሁት፡ የዐዋጅ መልእክቴም፡ በአንድ ወገን፡ እናንተ፡ ጥቂቶቹ ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን፡ "የእግዚአብሔር እና የኢትዮጵያ ልጆች" ተብላችሁ፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም፡ በምድር ላይ፡ በሥጋዊው አካልና ባሕርይ ሣላችሁ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውስጥ፡ በአንድነት እየኖራችሁት ያላችሁት፡ የሰላምና የፍቅር፥ የደስታና የብልጽግና ሕይወት፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ "የክፉውና የሰው ልጆች" ተብላችሁ በመጠራት፡ እየራሳችሁን፡ ለዚያ የብፅዕና ሕይወት ላላበቃችሁት፡ ለብዙዎቻችሁ ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን ኹሉ፡ እርግጡን፡ አጕልቶና አግዝፎ የሚያሳያችሁ እውነታ ነው።

"ያም እውነታ፡ ከእናንት ልጆቻችን መካከል፡ አንዱ በኾነው፡ በዛሬው ኢትዮጵያዊ አገልጋያችን፡ በኪዳናዊው ኤርምያስ በኩል፡ ከዚህ አስቀድሞ፡ "**ጾመ ኢትዮጵያ**"ን እና "**ሰላም ለኢትዮጵያ**"ን በሚመለከት፡ እንዲተላለፍላችሁ ስናደርግ በቆየነው፥ እኔም፡ አኹን፡ ያን በማዘከርና በማጠቃለል፥ በማጽናትና በማደስ በማቀርብላችሁ፡ በዚህ፡ የምሥ ራች መልእክታችን አማካይነት የሚከሠተው ነው።

"ይኸው የምሥ ራች መልእክታችን፡ በ፳፻ (በ፪ሺ) ዓመተ ምሕረት፡ ለጥቂት ጊዜ የተፈታው ዲያብሎስ፡ በተለይ፡ ከዚያ ወዲህና በዚህ፡ በ፳፻፲፩ኛው (፪ሺ አሥራ አንደኛው) ዓመተ-ምሕረት፥ ወደፊትም፡ የሚያስከትልበትን የፈተናና የችግር ማዕበል፡ በድል አድራጊው ኢትዮጵያዊው አንበሳ፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሢሕ፥ ከእርሱ አስቀድሞም፡ እጆቼን፡ ምንጊዜም፡ ወደእርሱ፡ ወደእግዚአብሔርነታችን ዘርግቼ ባደረስሁት፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያዋ ቅድስት እናቱ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ የቃል ኪዳን ኃይል፡ ይህ፡ ኢትዮጵያዊው ኪዳናዊ ትውልዴ፡ እስከዛሬ፡ በየዓመቱ፡ ሲያካኺድ በቆየው፡ በ"ጾመ ኢትዮጵያው" እና በ"ሰላመ-ኢትዮጵያው" ምሕላ አማካይነት፡ ለመቋቋምና ለማስወገድ ስለቻለበት መፍትሔ፡ የሚናገረው ቃላችን ነው።

## የአርባ ዓመታት ምሕላና ሱባኤ ፍሬ።

"በዚህ ረገድ፡ አገልጋያችን ኤርምያስ፡ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ያደረገውን ልተወውና፡ ከ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ወዲህ፡ እስከአኹኑ ዓመት ድረስ፡ ለአርባ ዓመታት፡ እናንተ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቻችን፡ በተለይ፡ **በየካቲትና በጳጉሜ ወራት፡ "ጾመ ኢትዮጵያ" እና "ሰላም ለኢትዮጵያ" በሚሉ ስያሜዎች፡ በየመንፈቀ ዓመቱ፡ ስታቀርቡልን የኖራችሁት፡ የቅዱሱ ኪዳን የምሕላ ጾምና ጸሎታችሁ፡** "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን ትውልዴን፡ በታላቁ የክህደት ፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢኣቱ ምክንያት፡ ሊጠፋ ከተቃረበባት ሰዓት ለማዳን፡ አስተዋጽኦውን፡ የቱን ያህል እንዳበረከተ የምታውቁ ስንቶቻችሁ ናችሁ?

"ከዚህ ጋር፡ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ በስሜ የተጠራችውን አገራችሁን፡ ከቤተ ሕዝቧ፥ ከቤተ ምልክናዋና ከቤተ ክህነቷ ጋር፡ በዘለዓለማዊው የነጻነት ህልናዋ እንዳለች ኾና እንድትቀጥል በማድረጉ ረገድ፡ ምን ያህሉን፡ ድርሻ እንደፈጸመ የምታውቁስ፡ ስንት ትኾናላችሁ? ምናልባት፡ የማታውቁ፥ ዐውቃችሁም፡ ያልተረዳችሁ ካላችሁ፡ ይህን እውነታ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ልታውቁትና ልትረዱት፥ ልትገነዘቡትም ይገባል።

"በይበልጥ፡ ልታውቁትና ልትረዱት፥ ልትገነዘቡትም የሚገባው ግን፡ የዚሁ እውነታ ዐቢይ አካል የኾነውን፡ **<u>በእኛ በኩል፡ ይህ የቸርነታችን ሥራ፡ ሊደረግላችሁ የተቻለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት መኾኑን ነው።</u>**

"እንዲህ ባይኾንማ ኖሮ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ዘንድ፡ ስደት እንደሌለ፡ የሚታመንበት ኾኖ ሳለ፡ ነገር ግን፡ የኢትዮጵያዊነቱን ሃይማኖትና ምግባር ሳይፈጽም በመቅረቱ፡ እንዲያው በከንቱነትና በግብዝነት፡"ኢትዮጵያዊ ነኝ!" እያለ የሚመጻደቀው ይህ ትውልዴ፡ ራሱን፡ ለስደት ና ለልዩ ልዩ ፈተና ዳርጎ፡ ፈጽሞ እየባዘነ፡ የመከራ ኑሮውን፡ በእልኽ ኝነት ከመቀጠል በቀር፡ በእነዚያ ፵ (አርባ) ዓመታት ውስጥ፡ በየግሉም ኾነ፥ በቤተ-ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ እየራሱን፡ ለእውነተኛ ንስሓ ማብቃት አቅቶት እያለ፡ መለኮታዊ የኾነው፡ ይህ የእኛ የቸርነት ሥራ፡ በአኹኑ ኹኔታና ጊዜ፡ እንዴት ሊደረግለት ይቻል ነበር? አዎን! አይቻልም ነበር።

"ይኸው ትውልድ፡ በእነዚያ ፵ ዓመታት ውስጥ፡ እየራሱን፡ ለእውነተኛ ንስሓ አብቅቶ ተገኝቶ ቢኾንማ ኖሮ፡ "አገሬ" በሚላት ምድራችን የሚኖረው ኾነ፥ በየዓለሙ፡ የሰዎች አህጉራት ተበታትኖ፡ ይኸው እየተንከራተተና እያማረረ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ ከሚሠቃይበት መከራ፡ እየራሱን፡ እስካኹን በድል አድራጊነት ነጻ አውጥቶ፡ ያለምንም ጥርጥር፡ ኹለንተናዊዉን የትድግና አክሊል ሊቀ ዳጅ በቻለ ነበረ። እንደነነዌ ሕዝባችን ማለት ነው።

"የኃጢአቱ ጽዋ ሞልቶ፡ በራሱ ክፋት፡ ሊጠፋ የነበረው፡ ያ፡ የነነዌ ሕዝባችንማ፡ የፈጸመውን ድንቅ ምግባር፡ ምንጊዜም የምታዘክሩት እንጂ፡ ልትዘነጉት የሚቻላችሁ አይደለም። አዎን! ወደዚሁ፡ ወደነነዌ ሕዝባችን ልከነው የነበረው፥ እርሱ ግን፡ የሰጠነውን ተልእኮ፡ "አልቀበልም!" ብሎ ቢኮበልልም፡ በተአምራ ችን፡ ወደዚያችው የነነዌ ከተማ መልሰን ያደረስነው፡ ሞገደኛው ነቢያችን ዮናስ የተናገረውን፥ የነነዌም ሕዝብ የሰማውን ቃል፡ ታውቁ የለምን? አዎን! ታውቃላችሁ።

"ያም ቃል፡ ዮናስ፡ ተገድዶ በተናገራት፡ በአንዲት የስብከት ዐረፍተ-ነገር ብቻ የተጠቃለለ፥ እርሱም፡ ያውም፡ በነቢዮቻችን ዘንድ እንደተለመደው፡ <u>"ልትጠፉ ነውና፡ ከመጥፋታችሁ በፊት፡ ንስሓ ግቡ!"</u> በሚል የማስጠንቀቂያ መልእክት የተገለጸ ሳይኾን፡ <u>"በሦስት ቀን ውስጥ፡ ነነዌ ትገለበጣለች!"</u> በሚል የቁጣና የውሳኔ አስደንጋጭ ቃል፡ የታወጀው ነው።

"ይህን፡ የመልእክታችንን ቃል ሰምቶና አዳምጦ፡ ወዲያው፡ በምግባር ላይ ያዋለው፥ በሦስት ቀኖች የጾምና የጸሎት ምሕላውም፡ ወደፍጹም ንስሓ በመመለሱ፡ ከታዘዘ መቅሠፍት የዳነውም ወገን፡ ያ፡ ከተራው ዜጋ፡ እስከንጉሡ ያለው፡ የነነዌ ሕዝባችን ነው። (ዮና. ምዕ. ፩ እስከ፬።)

"እንደነነዌ ሕዝብ ኾኖ ለመገኘት ላቃታችሁ፥ ለዚህ፡ በስሜ ለተጠራው፡ ኢትዮጵያዊ ትውልድ፥ በመላው ዓለም ለሚኖረው ሰብአዊ ትውልድ ጭምር፡ በአኹኑ ጊዜና ኹኔታ፡ **በእኛ በኩል፡ ይህ የቸርነታችን ሥራ፡ ሊደረግ የተቻለው፡ ለምን እንደኾነ፡** አሳውቃችኋለሁና፡ ስሙኝ!

"ይኸውም፡ **በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት የመኾኑን ሓተታ ነውና፡ ይህን** **ሓተታ፡ እኔው ራሴ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ ስለማቀርብላችሁ፡** የእናትነት ጥሪዬን፡ በሚሰማው መንፈሳዊ ጆሮአችሁ፡ ልብ ብላችሁ በማስተዋል አዳምጣችሁት፡ እየራሳችሁን፡ ለዚያ የብፅዕና ኑሮ ያላበቃችሁት ኹሉ፡ እርሱን፡ ሕይወታችሁ አድርጋችሁ ትኖሩት ዘንድ፡ በእናትነቴ፡ እንደገና፡ አደራ እላችኋለሁ።

"ዋናውን የዐዋጅ ቃሌን ላሰማችሁ ከመጀመሬ በፊት፡ አገልጋይ ልጃችን ኤርምያስ፡ **"ጾመ ኢትዮጵያ"** እና **"ሰላም ለኢትዮጵያ"** የተባሉትን አርእስተ-ጉዳዮች በሚመለከት፡ እስካኹን፡ ከእኛ፡ በመንፈስ ቅዱስ እያገኘ፡ ሲያቀርብላችሁ ከቆየው መልእክቶቻችን ውስጥ፡ ከዚህ መለኮታዊ የዐዋጅ ቃሌ ጋር የተያያዙትንና ዐበይት የኾኑትን፡ አንዳንዶቹን ቍም-ነገሮች፡ እስኪ፡ **ለአንክሮና ለተዘክሮ ያህል፡** እኔም ዛሬ፡ በትስብእት አንደበቴ እየጠቃቀስሁ ላውሳላችሁ!

"እነዚህም ቍም-ነገሮች፡ እናንተ፡ በቅዱሱ ኪዳን ታማኞቹ ልጆቼ፡ ኢትዮጵያውያኑና ኢትዮጵያውያቱ፡ በምስጋና ጸሎታችሁ፡ **'ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም!**

**"'ፍጥረተ ዓለሙ፡ በአንቺ ዳነ! በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!'** እያላችሁ፡ ዘወትር በምታሰሙት መዝሙራችሁ መሠረት፡ በመጀመሪያ፡- **እኔ፡ የዓለም መድኃኒት የመኾኔ መገለጫ በኾነው፡ በ'ጾመ ኢትዮጵያ'** የሱባኤ ጾማችሁ፥ በተከታይነትም፡ **ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በድል አድራጊነት፡ የዓለሙ ሰላም አስገኚ የመኾኑ መገለጫ በኾነው፡ በ'ሰላም፡ ለኢትዮጵያ!'** የምሕላ ጸሎታችሁ ውስጥ ተካትተው የነበሩ ናቸው።

## "ጾመ ኢትዮጵያ"ን በሚመለከት።

"**<u>አንደኛው ቍም-ነገር፡</u>** 'ጾመ ኢትዮጵያችን፡ ምን ዓይነት ፍሬን አስገኘች?' በሚል ንኡስ አርእስት፡ ኤርምያስ ያቀረበው ነው። እርሱንም፡ እንዲህ ሲል ጽፎታል፡-

"«ይህን [የቅዱሱን ኪዳን] እውነታ፡ በእውነት አምነውበት፡ ለሚያመልኩት ታማኞች ተከታዮቹ፡ በቅዱስ መንፈሱ የሚገለጠው፥ ያ፡ በኀሊናዬ ያለው፡ እግዚአብሔር፡ በጾመ ኢትዮጵያ ፍጻሜ ላይ፡ ለእኔም፡ እንደማንኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ገልጾልኝ እንዳስተውለው አደረገኝ።

"«አዎን! **የዓለሙ ሰላም እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡** ለማንኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ እንደሚያደርገውና በቀደሙት ዓመታት፡ በ‹ጾመ-ኢትዮጵያ› እና በ‹ሰላም ለኢትዮጵያ› የጾም ጊዜያት እንደፈጸምናቸው ቀኖናት ኹሉ፡ አኹንም፡ በዚህ፡ በ[ዘመኑ] ዓመተ ምሕረት፡ የሦስቷ ቀናት ጾምና ጸሎት፥ ምሕላና ስግደት ፡ የቀረበለትን፡ የእኔንም አቤቱታ ሰምቶ ኖሮ፡ በኀሊናዬ ውስጥ ያሳደረውን፡ ነፍሳዊ የዕውቀት ባሕርይ፡ በፍጻሜው ላይ፡ በቅዱስ መንፈሱ ቀሰቀሰው!

"«ቀስቅሶም፡ በንስሓ ለመመለስ ፈቃደኛ ኾኖ ስላልተገኘው፡ ስለዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ **'ምን አድርግ ነው፡ የምትለኝ?'** በሚለው የኃዘኔታ ጥያቄው፡ ለአቤቱታዬ መልስ ሰጠኝ።

"«እኔም፡ ከፊቱ ወድቄ እያለሁ፡ 'ጌታዬ! አምላኬ! አቤቱ! እንግዴህ፡ እባክህ ይብቃ!' አልሁት።

"«እርሱም፡ **'ምኑ?'** አለኝ።

"«ኹሉን የሚያውቅ ፈጣሪ በመኾኑ፡ ለዚህ፡ መለኮታዊ ጥያቄ፡ መልስ መስጠት እንደማያስፈልገኝ ተገንዝቤ፡ ጸሎቴን፡ እንዲህ እያልሁ ቀጠልሁ፡-

"«'በቅድስት እናትህ ስም የሚጠራውንና ለእርሷ፡ ልጆቿ አድርገህ የሰጠኻውን፡ ይህን የኢትዮጵያ ትውልድ፥ ደግሞም፡ በእርሷ ስም የምትጠራውንና ለእርሷ፡ ርስት ጕልት አድርገህ የሰጠሃትን፡ ይህችን፡ የኢትዮጵያ ምድር፡ የትውልዱን፡ የሃይማኖት መኳደልና የምግባር መሰነካከል ሳትመለከት፡ እንዲያው፡ ስለቅዱሱ ስምህ ስትል፥ በእናትህ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ኪዳነ ምሕረትነት፡ በአንተና በእኛ መካከል ጸንቶ ስላለው፡ ስለቅዱሱ ኪዳንህም ስትል፥ እንዲሁም፡ ስለባለሟሎችህ መላእክት፥ በሕይወተ-ሥጋና በሕይወተ-ነፍስ ስላሉት፡ ታማኞች አገልጋዮችህ ቅዱሳንና ቅዱሳት ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታትም ስትል፡ በቀደሙት ዘመናት፡ ስታደርግ የኖርኸውን፥ እኔም፡ ይኸው፡ በሕይወተ-ሥጋ ቆሜ፡ በዓይኖቼ እንዳይ ያደረግኸኝን፡ ይህን የቸርነት ሥራህን አስታውሰህ፡ ዛሬም ደግሞ፡ እባክህ ይቅር በል!'

"«ስሟን ስለጠራሁ፡ ታማኞች አገልጋዮቿ፡ ‹አፍጣኒተ-ረድኤት!› (ፈጥና ለእርዳታ የምትደርስ) የምንላት እመቤታችን፡ ድንግል ማርያም፡ በዚያው ጎሊናዬ ውስጥ ስላለች፡ ድንገት፡ በልቦናዬ መድረክ ላይ፡ በመንፈስ ተገልጣ፡ **'ልጄን፥ ወዳጄን፡ ምን አድርግ ነው የምትለው?'** ስትል እንደጠየቀችኝ ተሰማኝ።

"«እኔም፡ በዚህ ድንገተኛ ኹኔታ፡ ለጥቂት ተደናግጬና መንፈሴ ታውኮብኝ፡ ከወደቅሁበት ሳልነሣ፡ እንደተደፋሁ፡ 'ውይ!? እምዬ፥ እመቤቴ! ቅድስት ድንግል! አንቺም!?' አልኳት።

"«እርሷም፡ በጽኑ ቃል፡ **'አዎን! ልጆቼን፥ ይኼን የዛሬውን ትውልዴንም የምፋረድ፡ እኔ ነኝ እንጂ፡ እርሱ፡ ልጄ ወዳጄ አይደለም!'** አለችኝ፤

"«ቃሏንም፡ እንዲህ ስትል ቀጠለች፡- **'እርሱማ፡ ‹ድል አድራጊው አንበሳ›፡ የዛሬ ኹለት ሺህ ስምንት ዓመት፡ በራሱ መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ ፈጽሞ ይቅር ብሎ፡ ለመቼውም ጊዜ፡ ምሕረቱን አድርጓል። ምን ቀረበትና ነው፡ አኹን፡ እንደገና፡ ‹ይቅር በል!› የሚባለው?**

"«**'ልጄ ወዳጄ! ይህንኑ ምሕረቱን፡ በእኔ ዋስትና፡ በቃል ኪዳኑ ዐትሞ፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ሰጥቷል፤ ለዚህ ይቅርታውና ምሕረቱ፡ ማረጋገጫ የኾነውን፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን፡ በእንጨት ላይ፡ ራቁቱን ተሰቅሎና በጦር ተወግቶ ሲቆርስ፥ ሲያፈስስም፡ እኔ እናቱ፡ ከመስቀሉ አጠገብ ቆሜ፡ በዓይኖቼ ተመልክቻለሁ፤ ከመስቀል ባወረዱትም ጊዜ፡ ይህንኑ የተቆረሰ ቅዱስ ሥጋውንና የፈሰሰ ክቡር ደሙን፡ በሰውነቱ ላይ እንዳለ፡ ዐቅፌው፡ በእጆቼ ዳስሼና አብሼ፡ ስሜዋለሁ።**

"«'የይቅርታውና የምሕረቱ ማረጋገጫ የኾነው፡ ይኸው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ያለማቋረጥ፡ በየቀኑ፥ በየቤተ-ክርስቲያኑ፡ እንዲዘጋጅ እያደረገም፡ እነሆ፡ 'ብሉኝ! ጠጡኝ!' በሚለው፡ በጸሎተ-ቅዳሴው ያውጃል።

"«'በዚህ፡ በቅዱስ ቁርባኑም ግብዣ፡ በሥጋ ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስና በመንፈስም፡ ለተራበውና ለተጠማው፥ ለታረዘውና ለታመመው፥ ለታሠረውና ለተሰደደው ኹሉ፡ያለከልካይና ያለዋጋ፡ በፍቅርና በሰላም፥ በነጻነትና በሓሤት ያቀርበዋል።

"«'ታዲያ! ከእርሱ፡ ከልጁ ከወዳጄማ፡ ምን የጎደለበት፥የቀረበትም ነገር ኖሮ ነው፡ አኹን፡ እንደአዲስ፡ ይቅርታና ምሕረት የሚጠየቀው? ይህንም፡ አንተም ታውቀዋለህ።' አለችኝ፡ በዚያው፡ በጎሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ።

"«እኔም፡ ዓይኖቼን ጨፍኜ እንደተደፋሁ፡ 'አዎን! እናታችን! ቅድስት ድንግል! አውቀዋለሁ።' በማለት፡ ፈጥኜ፡ በጎሊናዬ መለስሁላት።

"«'ታዲያ! ካወቅኸው፡ ለምን፡ ልጄ ወዳጄንም፥ እኔንም፡ ታስቸግረናለህ?' ያለችኝ መሰለኝ፡ በዚያው፡ በጎሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ፤ መደንገጤንና መፍራቴን ዐውቃ፤ መለስ ባለ፡ በለሰለሰ ድምፅ።

"«'ቢቸግረኝ ነዋ! እምዬ! እመቤቴ! ታዲያ! ምን ላድርግ? ወዴትስ እኼዳለሁ?' ብዬ፡ በዚያው በጀመርሁት፡ የፍቅር ድፍረቴ መለስሁላት፤ ንግግሬንም በመቀጠል፡ 'ለልጅሽና ለአንቺ፡ ‹አቤት!› ከማለት በቀር፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውንና ኢትዮጵያውያት፡ ሌላ የምንጮህበት፡ ምን መኼጃ አለን? ይህንማ፡ አንቺ ያስተማርሽን፡ ሥርዓታችን አይደለምን?' አልኋት፡ አኹንም፡ በዚያው፡ በጎሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ።

"«እርሷም፡ 'በዚህ ሃይማኖትህና ምግባርህ በመጽናትህማ፡ ይኸው፡ ለዚህ ዕድል በቅተሃል! አኹንም፡ የእኔ፡ የእግዚአብሔር እም ብቻ ሳይኾን፡ የእግዚአብሔር አብም ልጅ የኾነው፡ ይህ፡ በስሜ የተጠራው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፥ ርስት ጕልቴ የኾነችው፡ ይህችም ምድር፡ ከልጄና ከእኔ ስም፥ ከቅዱሱ ኪዳንና በዚሁ ኪዳን ጸንተው ከሚገኙት፡ ታማኞች ልጆቼ፡ ገድል የተነሣ፡ ኹለቱም አይጠፉም!' የሚል፡ የሚያጽናና ቃልን አሰማችኝ።

"«በዚህ ቃሏ፡ መንፈሴ፡ በበለጠ ተነቃቅቶና ዕዝነ-ልቦናዬ ለመስማት፡ ወደቃሏ አዘንብሎ ሣለ፡ በዚያው፡ በጎሊናዬ ውስጥ እያለሁ፡ ምሥራቿን፡ እንዲህ ስትል፡ ቀጠለችልኝ፡- 'ለዚህ ሕዝቤ፡ ለእያንዳንዱ ግለሰብ ሳይቀር፥ ለዚች ምድሬም፡ የበጃቸውና የጠቀማቸው፡ ቅዱሱ ኪዳንና የእርሱ፡ የቅዱሱ ኪዳን መኖር ነው።

"«'እርሱንም፡ የቀደሙት፡ ታማኞቹ አገልጋዮቼ፡ የዚህ ሕዝቤ ወላጆቼ፡ ከጥንት ጀምረ ው የነበሩት፥ ዛሬም ያሉት፥ አንተ፡ በአካለ-ሥጋ የማታውቃቸው፥ ልጄ ወዳጄና እኔ ግን የምናውቃቸው፡ ጥቂቶቹ ጭምር፡ አክብረውና ጠብቀው፥ በመሥዋዕትነታቸውም፡ አጽንተውት፡ እስከዚህ ጊዜ አቆይተውታል።

"«'ይህን እውነታ፡ ወገኖችህና ሌላው ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ እንዲገነዘቡት ለማድረግ፡ መንፈስ ቅዱስ ባመለከተህ፡ የምታካኺደውን ጥረት አታቋርጥ!

"«'ይህን ጥረትህን፡ በመፃረር፡ ከዲያብሎስ፥ መናፍስትና ሰብአውያን ከኾኑት፡ ከሠራዊቱ፡ በግልጽም፥ በሥውርም፡ እየገጠመህ ያለውን ብርቱ ተቃውሞ፡ ልጄ ወዳጄና እኔ እናያለን፤ ይህ አገልግሎትህ፡የተጠራህበት ተልእኮህ ብቻ ሳይኾን፡ ገድልህም ስለኾነ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአንተ ጋር ነውና፡ በሚደርስብህ ጥቃት ሳትዳከም፡ ቀጥልበት!' አለችኝ፡ እመቤቴ፡ በሚያጽናና ቃሏ።

"«ከዚህ የተከተለውን ንግግርዋን የጀመረችው፡ 'ግን' በሚለው ያሉታ ቃል ስለኾነ፡ 'እመቤቴ፡ አኹን ደግሞ፡ ምን ልትለኝ ይኾን!?' ብዬ፡ መንፈሴ፡ በድንጋጤ፡ እንደገና ሊታወክብኝ ሲቃጣው፡ 'ግን፡ ለልጆቼ የምታደርስላቸው መልእክት፡ ይህ ነው፡-' የሚለውን ቃሏን፡ በዕዝነ ኅሊናዬ ስሰማው፡ ተረጋጋሁና፡ ከተደፋሁበት፡ ቀና አልሁ፡ በፊቴ ያለች መስሎኝ።

"«ለካ ንግግራችን የሚካኼደው፡ በመንፈስ ኖሮ፣ በአካለ-ሥጋ ላያት የምችል መስሎኝ፡ ቀና በማለት፡ በፈጸምሁት የስሕተት አድራጎቴ፡ 'ብፁዓንሰ፡ እለ እንዘ ኢይሬእዩኒ፡ የአምኑኒ!

"«'ሳያዩ የሚያምኑብኝ፡ ብፁዓን ናቸው!' ከሚለው፡ ከኢትዮጵያ ልጆች፡ ብቸኛ ባለቤትነት፡ ውጭ የሚያደርገኝ፡ ታላቅ የእምነት ጉድለት መኾኑን አምኜ፡ ፈጣሪዬን፡ በቅጽበት ንስሓዬ፡ 'ይቅር በለኝ!' ብዬ ከለመንሁት በኋላ፡ ያለሁበትን እውነታ በመቀበል፡ ወደነበርሁበት ስግደቴ፡ ተመልሼ፡ በግንባሬ ተደፋሁ።

"«እመቤቴ፡ ድንግል ማርያምም፡ 'ለልጆቼ የምታደርስላቸው መልእክት፡ ይህ ነው!' ስትል መናገርዋን፡ እንዲህ በሚል ቃል ቀጠለች፡-

"«'የጎደለውና የቀረው፡ ከልጄ ከወዳጄ ሳይኾን፥ ከእኔም ከእናታችሁ ሳይኾን፡ ከእናንተ ነው፤ ቅዱሱን፡ የይቅርታና የምሕረት ኪዳን፡ በሃይማኖታችሁ ጉድለትና በምግባራችሁ ርኵሰት፡ ልታፈርሱ የሞከራችሁ፡ እናንተ ናችሁ፤ ኪዳኑ፡ መለኮታዊ ስለኾነ፡ በዘለዓለማዊነቱ፡ በየጊዜው እየጸና የሚኼድ ከመኾኑ በቀር፡ በማንም ፍጡር፡ ሊፈርስ ቀርቶ፡ ሊነካ አይቻልም፤ሊያፈርሰው የሚሞክር ቢኖር፡ ያ የሞከረው ፍጡር፡ ራሱ ይፈርሳል እንጂ፡ እርሱ፡ ቅዱሱ ኪዳን፡ ፈጽሞ አይነካም።"

"«'እኔና ልጄ ወዳጄ፡ ቅዱሱን ኪዳን የሰጠናችሁ፡ እናንተን ለመጥቀም፥ ለእናንተው ደኅንነትና መልካም ሕይወት እንዲኾንላችሁ እንጂ፡ ለሰጪው፡ ለእርሱ፡ ለእግዚአብሔር፡ የሚያስፈልገው ኾኖ አይደለምና፡ ለየራሳችሁ ጥቅም ስትሉ፡ ኪዳናችሁን ጠብቁት!

"«'ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በከፈለው መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ እኔ እናቱ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ሕያው ማደሪያውና ዋስትናው፥ ምስክሩና ምልክቱ የኾንሁለት፡ ይህ ቅዱሱ የምሕረት ኪዳን፡ ከእናንተ፡ ከእያንዳንዳችሁ የሚጠይቀውን፡ የየበኩላችሁን ግዳጅ ፈጽሙ! የአኹኑ ግዳጃችሁ፡ በክህደት ፥ በዓመፅና በአመንዝራነት ኃጢአታችሁ ምክንያት፡ በእየራሳችሁ ላይ፡ የወረደውን ፍዳ፡ <u>በእውነተኛ ንስሓ ማስወገድ ነው።</u>

"«'ይህን ካላደረጋችሁ፡ የእኔንና የልጄ የወዳጄን ይቅርታና ምሕረት አታገኙትም። በዚያው ኃጢአታችሁ እስካላችሁ ድረስ፡ እንዴት ልታገኙት ይቻላችኋል? አይቻላችሁም። የእያንዳንዳችሁን ጥፋትና የኀብረት በደላችሁንማ፡ እናንተ ከምታውቁት በላይ፡ ልጄ ወዳጄም፥ እኔም፡ እናውቀዋለን፤ ከእኛ ልትሸሽጉት አይቻላችሁም። ቅዱሱን ኪዳን፡ አክብራችሁ ስትጠብቁት፡ እርሱም፡ በክብር ይጠብቃችኋል፤ ንቃችሁ ስትተዉት ግን፡ ለእየራሳችሁ፡ የሥጋ ፈቃድና ፍላጎት፡ አሳልፎ ይሰጣችኋል፤ ለፍጹም ድምሳሴ ግን፡ አይዳርጋችሁም፤ በንስሓ ስትመለሱ፡ በሓሤት ሊቀ በላችሁ፡ ይጠባበቃችኋል። ስለዚህ ተመለሱ!

"«'የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ' የምትሰፍነው፡ በሰዎች ልቦና ውስጥ እንደኾነ ታውቃላችሁ፤ እንዲህ ከኾነ፡ 'የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ'፡ በየልቦናችሁ ውስጥ ትሰፍን ዘንድ፡ ሰውነታችሁ፡ በእርግጥ፡ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነውን?

"«'በእኔና በልጄ በወዳጄ ላይ ያላችሁ፡ የሃይማኖትና የአምልኮት ታማኝነታችሁ፡ እንዴት ነው? እስከምንስ ነው? በምግባራችሁስ፡ እንዴት ናችሁ?

"'ለመኾኑ፡ ዛሬ የምትኖሩት፡ ልጄ ወዳጄ፡ በጥንቱ፥ በመካከሉና በመጨረሻው ዘመናት፡ የሠራላችሁን ሥርዓት ተከትላችሁ ነውን? በኹለንተናችሁ ሠልጥኖ፡ በነጻነት እንዲመራችሁ የተቀበላችሁት፡ ማንን ነው? የእርሱንና የእኔን ቅዱስ መንፈስ? ወይስ፡ በባርነት እንዲገዛችሁ የፈቀዳችሁለትን፡ ባዕዱን፥ ክፉ መንፈስ?

"«'እስኪ፡ እየራሳችሁን፡ በእውነት መርምሩ! ኹለንተናችሁ፡ በሃይማኖታችሁና በአምልኮታችሁ፥ በምግባራችሁና በኑሮአችሁ፡ ፍጹም ንጹሕ ነውን? ልጄ ወዳጄ፥ ጌታዬና ሕይወቴ እግዚአብሔር፡ የሚቀበለው አምልኮ፡ በእውነትና በመንፈስ የሚቀርብለትን ብቻ መኾኑን ታውቃላችሁ።

"«'እንዲያ ከኾነ፡ እናንተ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚህ፡ ለእርሱ እውነተኛ አምልኮና ሕይወት፡ በንስሓ ስለማብቃታችሁ፡ በሰው ፊት ቀርቶ፡ በየኅሊናችሁና በእግዚአብሔር ፊት ትመሰክራላችሁን?

"«'ስለእኔስ ያላችሁ ፍቅር፡ ከልባችሁ፡ የእውነት ነውን? ወይስ፡ በአንደበት ብቻ የሚነገር ነው? እንደልጄ ወዳጄ የአደራ ቃል፡ እኔ እናታችሁ፥ እናንተም፡ ልጆቼ ከኾናችሁና በስሜ ከተጠራችሁ፡ የምትኖሩት፡ ቃሌን ሰምታችሁና ተቀብላችሁ፡ ልጄ ወዳጄ በሠራላችሁ ሥርዓት ነውን?

"«'አለዚያ፡ እንዴት፡ ‹ልጆቼ!› ተብላችሁ፡ በልጄ ወዳጄ ስም፡ ‹ክርስቲያኖች!›፥ በእኔም ስም፡ ‹ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት› ተብላችሁ ልትጠሩ ትችላላችሁ? አይኾንም፤ ልጆቼ!

"«'በቃና ዘገሊላ የሠርግ በዓል ላይ፡ የተደረገውን ተአምር፡ ታስታውሱ የለምን? ያ ተአምር፡ እውን የኾነው እኮ፡ በዚያ የነበሩት አገልጋዮች፡ እኔ፡ ‹አድርጉ!› ያልኋቸውን ቃሌን ተከትለው ስለፈጸሙት እንደነበረ ታውቃላችሁ።

"«'እነርሱ፡ ለዚያ ቃሌ፡ ታዛዦች በመኾናቸው፡ ልጄ ወዳጄ፡ ‹ጊዜዬ፡ ገና አልደረሰምና፡ አላደርገውም!› ያለውን ቃሉን ሳይቀር፡ ለእኔ፡ ለእናቱ ሲል አሻሽሎ፡ የምሕረትና የቸርነት ሥራውን ፈጽሞልኝ፡ አስደስቶኛል።

"«'እናንተ፡ ከልጄ ከወዳጄ ተለይታችሁ፡ እርሱንና እኔን የሚያሳዝነውን ጥፋት ልታደርጉ ይገባችኋልን? ልጆቼ ከኾናችሁ፡ እርሱ፡ ፈቃዴን ተቀብሎ እንደፈጸመልኝ፥ እነዚያ አገልጋዮችም፡ ትእዛዜን ሰምተው እንደፈጸሙት፡ እናንተስ፡ ቃሌን ሰምታችሁ፡ የማትቀበሉትና የማትፈጽሙት፡ ለምንድር ነው? (ዮሐ. ፪፥ ፩-፲፩።)

"«'በእናንተ፡ በቃል ኪዳን ልጆቻችን በኩል፡ ልታደርጉት የሚገባችሁን፡ ልንገራችሁ ብዬ ነው እንጂ፡ ልጄ ወዳጄ እና እኔማ፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ እርሱ፡ የአባትነቱን ቸርነት፥ እኔም፡ የእናትነት ርኅራኄዬን አናጓድልባችሁም!' በላቸው።

"«'እንግዴህ፡ በአንተም አንደበት፡‹ተዉ! አይኾንም፤ ይበቃል፤ በንስሓ ተመለሱ!› ሊባሉ የሚገባቸው፡ የቃል ኪዳን ልጆቼ፡ እነርሱ እንጂ፡ ልጄ ወዳጄ፡ የቀረበት፡ የቸርነት ሥራ ኖሮ፡ ‹'ይህን አድርግ!'› ተብሎ አይጠየቅም፤ሊለመንም አይገባም!› ስል፡ ቀደም ብዬ የተናገርሁህ፥ ልጄ ወዳጄም፡ ‹ምን አድርግ ነው የምትለኝ?› ያለህ፥ እኔም አስከትዬ፡ ‹ልጄ ወዳጄን፡ 'ምን አድርግ ነው የምትለው?'› ያልሁህ፡ ለዚህ ነው።

"«'አኹንም፡ ይህን ቃሌን መሠረት አድርገህ፡ ልጄ ወዳጄ ያለህን፥ እኔም ያልሁህን፡ ይህን መልእክት፡ ለዚህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ አድርስላቸው!' አለችኝ፡ በዚያው፡ በነበርሁበት፡ የኅሊና ተመስጦዬ ውስጥ እንዳለሁ።

"«እኔም፡ 'እመቤቴ! በዚህ ረገድ፡ በእኔ በኩል፡ የምችለውን ኹሉ፡ በዓቅሜ አድርጌአለሁ፤ ሳልፈጽመው የቀረብኝ ተልእኮ ያለ አይመስለኝም። ይህንኑም፡ አንቺም፥ ልጅሽም፡ የምታውቁት ስለኾነ፡ ለመግለጽ መሞከሩ፡ የሚገባኝ አይደለም።

"«'የልጅሽንና የአንቺን መልእክት፡ ለትውልዱ ማቅረብ የጀመርሁት እኮ፡ ገና፡ በልጅነት ዕድሜዬ፡ በትምህርት ቤት ሣለሁ ነበር፤ ኋላም፡ ትልቅ ኾኜ፡ በሥራው ዓለም፥ ቀጥሎም፡ በደርግ እሥር ቤት፥ ግዞትና የባሕር ማዶ ስደት ኑሮዬ ጊዜያት እንኳ ሳይቀር፡ የተጠመድሁበትን፡ ይህንኑ ተልእኮዬን በመቀጠል፡ በቃሌና በአካል ተዘዋውሬ፡ በየቦታው በመገኘት፥ በጽሑፍና በመጽሓፍ፥ በዘመኑ የድምፅና የምሥ ል መገናኛ አውታሮች ጭምር፡ የአንችንም፥ የልጅሽንም መልእክቶች አዳርሼ ጨርሻለሁ። በእነዚያ ጊዜያት፡ የተናገርኋቸው ኃይለ-ቃላት፥ የጻፍኋቸው ቍም-ነገሮችስ፡ ከራሴ የፈለቁ፡ የእኔ ናቸውን? ‹ከማን አገኘሁት?› ወይስ፡ ‹ከማን ተማርሁት?› ልል ነው?

"«'ገና፡ በልጅነቴ፡ ተማሪ ሣለሁ፡ **‹ሕፃኑ ሰማዕት፡ ቅዱስ ቂርቆስ!›** እና **‹እየው ያን መከራ! የደስታ ጮራ!›** በሚሉ አርእስት፡ የጻፍኋቸውን ተውኔቶች፡ በሰበካዬ ማርገጃና ድንኳን፥ በትምህርት ቤትና በሕዝብ አዳራሾች መድረክ ላይ ቀርበው እንዲታዩ ያደረገ፥

"«ከዚያም፡ **‹ምናሴ! የመከራዬ ደስታ! ዓለምን ረታ!›** የሚለውን መጽሐፈ ራእይ፡ ያስደረሰ፥ ያሳተመና ያሠራጨ፥ በመጨረሻም፡ እውን ያደረገ ማን ነው? በእነዚያ ድርሰቶች አማካይነት የተላለፈው መልእክትስ፡ የማን ኖርዋል? በእነዚህ ኹሉ ሥራዎች አማካይነት የተከሠቱት ምስጢራትና የተላለፉት መልእክታት፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ መንፈስ ቅዱስ የገለጸልኝና ያስተማረኝ፡ የልጅሽና የአንችው አይደሉምን?

"«'**‹ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!›** የሚለው መጽሐፍ የተዘጋጀው፡ ‹ኢትዮጵያዊ ነኝ!› የሚለው ሰው ኹሉ፡ ያን ተመልክቶ፡ የአንቺንና የልጅሽን ማንነት ፈልጎ በማግኘት፡ ከአንቺና ከልጅሽ ለመድረስ፥ በዚህም የፍለጋ ግኝቱ ምክንያት፡ የራሱን ማንነት፡ በትክክል ለማወቅ እንዲችል፡ ለመርዳት አይደለምን?

"«'**‹ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!›** የሚለውስ መጽሐፍ፡ የያዘው ቍም-ነገር፡ አንቺ፡ ከልጅሽ በተሰጠሽ ሥልጣን፡ ይኸው፡ እንደዚህ፡ እንደዛሬው ቃልሽ፡ ልጆችሽንና ሰውን ኹሉ፥ ፍጥረተ-ዓለሙንም በመላ፡ በልጅሽ ፊት የምትፋረጅበት አይደለምን?

"«'**‹ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት›** የሚሉት መጽሐፎችስ፡ ይህንኑ፡ የልጅሽንና የአንቺን መልእክቶች፡ በእኔ ተላላኪነት፡ ለእኒሁ ልጆችሽና ለሌላውም ሰብአዊ ፍጡር፡ ያስተላለፍሽባቸው ጦማሮችሽ አይደሉምን?

"«'የቅርቡ፡ **‹ምሥ ራች!›** የሚለው መልእክት የተላለፈበት ዕትምስ፡ የኹሉ ፈጣሪ የኾነው ልጅሽ ወዳጅሽ፡ የዛሬ ኹለት ሽህ ሰባት ዓመት፡ በአንቺ ማንነት፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ያስገኘውን፡ የመጨረሻውንና ዘለዓለማዊዉን የብቅዓት ጸጋና ሕይወት፡ ለእያንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡር ያቀዳጀ መኾኑን፡ የሚያበሥርና የሚያሳውቅ መጽሐፍ አይደለምን?

"«'ትውልዱ፡ በቃልና በእነዚህ ድርሰቶች አማካይነት የተላለፈለትን፡ ይህን፡ የአንችንና የልጅሽን የወዳጅሽን መልእክቶች፡ መስማቱና መቀበሉ፥ መፈጸሙም ቀርቶ፡ ከቤተ-ሕዝቡና ከቤተ-ምልክናው ብቻ ሳይኾን፡ ከቤተ-ክህነቱ ጭምር፡ በእነዚህ መጻሕፍት ላይ፡ በግልጽና በሥውር፡ እየተካኼደ ያለውን፡ ረቂቅና ግዙፍ የተቃውሞ ዘመቻ፡ ተወዳጁ ልጅሽም፥ አንችም፡ የምታውቁት አይደለምን? ይህ ኹሉ እየኾነ እያለስ፡ እኔ፡ ይህንኑ ተልእኮዬን፡ መቼ አቋረጥሁ? አንችም፥ ልጅሽም፡ እስከጠራችሁኝና ለዚሁ ተልእኮዬ፡ በሕይወት-ሥጋ እቆይ ዘንድ እስከፈቀዳችሁልኝ ድረስ፡ እቀጥላለሁ እንጂ፡ አላቋርጥም፤ ዕውቀቴና ኃይሌ፥ መሪዬም በኾነው፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ በእሥር፥ በግዞትና በስደት እያለሁም፡ ይኸው እስካኹን ያላቋረጥሁትን አገልግሎት እንደማላቆም፡ ለአንችም፥ ለልጅሽም፡ የተሠወረ አይደለም።

"«'ነገር ግን፡ ይህን ኹሉ አድርጌ፡ እንኳንስ፡ ባዕዳኑ፥ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድም፡ የሰሙኝ አልመሰለኝም፤ ወደፊትም፡ የሚሰሙኝ አይመስለኝም፤ ስለዚህ፡ ‹ለልጅሽ ለወዳጅሽ የሚሣነው ስለሌለ፥ ለአንችም፡ ኹሉን ማድረግ ይቻልሻልና፡ በዚች ጾመ-ኢትዮጵያ፡ እንደእኔ፡ እንዲህ፡ ከፊታችሁ ወድቀው የሚማልሉትን፡ የታማኞች አገልጋዮቻችሁን ተማሕጽኖ ተቀብላችሁ፡ ለታላቅ መከራና ሥቃይ ለተዳረገው፡ ለዚህ፡ ለቃል ኪዳን ትውልዳችሁ፡ የሚሻለውን መፍትሔ አድርጉለት!› ከማለት በቀር፡ ሌላ ምን እላለሁ?

"«'እመቤቴ፣ እምዬ ድንግል ማርያም ሆይ! እንግዴህ፡ የእናንተን መፍትሔ ብቻ ለሚጠብቀው፡ ለዚህ አቤቱታዬ፡ መንሥኤ የኾነኝ ጽኑ ችግር፡ ይህ ነው።' አልኳት፡ በዚያው፡ በኅሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ።

"«እርሷም፡ 'አንተ፡ ገና፡ በገሃድ እንድታውቀው ስላልተደረገ፡ የሰሙህ ሳይመስልህ ቆይቷል እንጂ፡ ብዙዎች የሰሙህ አሉ፤ አኹንም፡ ብዙዎች የሚሰሙህ አሉና፡ ኺድ! ያልኩህን መልእክት፡ እንደተለመደው፡ አድርስላቸው! እስካኹን ያደረስኸው፥ አኹን የሰጠሁህና ወደፊት የምትቀበለውም መልእክት፡ የመንፈስ ቅዱስ ስለኾነ፡ ሳትፈራና ሳታፍር አድርስ! ልጄ ወዳጄና እኔ፡ ከአንተ ጋር ነን!' አለችኝ።

"«ለእርሷ፡ የእሺታ መልሴን ከመስጠቴ በፊት፡ ጌታዬ፥ አምላኬ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በቅድስት እናቱና በእኔ መካከል፡ የተካኼደውን፡ የቃል ምልልስ፡ ይሰማ ኖሮ፡ በዚያው፡ በኅሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ፡ እንዲህ አለኝ፡-

"«'በእግዚአብሔር እም እናቴ ሰውነትና በእኔ ትስብእት፡ ለዘለዓለም ሕያው ኾኖ በሚኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ ምሕረታችንና ቸርነታችን፡ ከዚህ የኢትዮጵያ ትውልድ አይርቅም፤ ክህደቱና ዓመፁ፥ አመንዝራነቱም ስለተደራረበበት፡ ይህ ትውልድ፡ በሥጋውም፥ በነፍሱም፡ በረሃብና በጥማት፥ በእርዛትና በደዌ፥ በእሥራትና በስደት ፥ በእርስ በርስ ፍጅትና ዕልቂት፡ ይኸው ይሠቃያል።

"«'ይህ ኹሉ የኾነውና የሚኾነው፡ ትውልዱ፡ ከኃጢአቱ፡ በንስሓ ላለመመለስ፡ በእንቢተኝነቱና በልበ ደንዳናነቱ፡ ከመጽናቱ የተነሣ ነው።

"«'ደግሞም፡ ከትውልዱ፡ እያንዳንዱ፡ በግል፥ በጋራም፡ ኹላቸው፡ እናቴንና እኔን፡ የበለጠ እንዲያውቁን፥ ከፈተናውና ከመከራውም ተምረ ው፥ በእነዚሁም ተገሥፀው፡ በንስሓ እንዲመለሱ ለማድረግ ነው።

"«'እየደረሰባቸው ያለውን፡ ይህን ኹሉ ፈተናና መከራ፡ ለደኅንነታቸው እንዲበጃቸው እናደርግላቸዋለንና፡ የወሰንነው፡ የኢትዮጵያ ቀን ደርሶ፡ የጊዜው ቸርነታችን እስኪገለጥ ድረስ፡ ካለፈው ኃጢአታቸው ተጸጽተው፡ንስሓ ከመግባትና በትዕግሥታቸው ከመጽናት በቀር፡ በሚደርስባቸው ፈተናና መከራ ተሠቅቀው፡ ከቃል ኪዳን ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው እንዳይነዋወጡ ንገራቸው! ምከራቸው! አስጠንቅቃቸው! ገሥጻቸውም!

"«'‹እናንት የኢትዮጵያ ልጆች!› እያልሁ፡ የተለዩ የእናቴ ልጆች አድርጌ፡ በእርሷ ስም የምጠራው፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና አምልኮው፥ ምግባሩና ኑሮው ላይ፡ የክህደትንና የዓመፅን፥ የአመንዝራነትንም ኃጢአት በመፈጸም፡ እንዲህ ቢያሳዝነኝም፡በእርሷ ስም የምጠራቸውን፡ እርሱንና የሚኖርባትን ይህችን ምድር፡ ለእናቴ፡ ርስት አድርጌ ሰጥቼ፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ የጠበቅኋቸው፥ ወደፊትም፡ የምጠብቃቸው፡ ለምን እንደኾነ፡ ለዚሁ ትውልድ፡ አበክረህ ንገረው!

"«'ይኸውም፡ የቀደሙት ወላጆቹ፡ ጠብቀው ስላኖሩት፥ የዛሬዎቹ ታማኞች አገልጋዮቼም፡ ተረክበው ስላጸኑት፥ በእኔና በእነርሱ መካከል ስላለው፡ ስለቅዱሱ ኪዳኔ ብዬ መኾኑን፥ እንዲሁም፡ ስለእናቴና ስለስሜ ስል መኾኑን አሳውቃቸው!' አለኝ፡ በዚያው፡ በጎሊናዬ ውስጥ።

"«የእናትና ልጇ ንግግር ማብቃቱን፡ በመንፈሴ እንደተረዳሁ፡ ለእርሱ፡ ለፈጣሪዬ፥ ለእመቤቴም፡ የእሺታ መልሴን፡ በዚያው በጎሊናዬ እንዳለሁ ከሰጠሁ በኋላ፡ ኹለንተናዬ፡ በልዩ ደስታና እርካታ ተውጦ፡ እንደመባነን አልሁ፤ እስከዚያች አፍታ ድረስ፡ ተከድነው የቆዩ ዓይኖቼን ገላልጬ፥ በግንባሬ ተደፍቼበት ከነበረው ስግደቴም፡ አንገቴን ቀና አድርጌ ተነሣሁ።

"«ይገርማችኋል! ለካ፡ '**ወአልቦ ፍርሃት፡ ውስተ ተፋቅሮትነ!**

"«'በፍቅራችን ውስጥ ፍርሃት የለም!' የሚለው፡ የመንፈስ ቅዱስ ቃል አይታበልም፤በዚህ መልክ፡ ከአምላክና ከእናቱ ጋር፡ በጎሊናዬ ውስጥ፡ በመንፈስ መነጋገር ጀምሬ፡ እስክፈጽም ድረስ፡ ከፍቅር ድፍረት በቀር፡ የፍርሃት ስሜት፡ ጨርሶ አልነበረብኝም።» (፩ ዮሐ. ፬፥ ፲፰።)

## "ሰላም፡ ለኢትዮጵያ"ን በሚመለከት።

"«**ኹለተኛው ቍም-ነገር፡** ‹በመላው ዓለም የሰፈነችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ለፍጥረቷ የሰጠችው ሰላም፡ ምን ዓይነት ነው?› በሚል ንኡስ አርእስት፡ ይኸው፡ ካህን ልጃችን ኤርምያስ ያቀረበው ነው። እርሱንም፡ እንዲህ ሲል ጽፎታል፦

"«እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡'**ሰላም ለኢትዮጵያ!**' በሚል ስያሜና ዓላማ፡ የጾመ ኢትዮጵያን ሥርዓተ-ጸሎት ተከትለን፡ ባለፉት ዓመታት፡ የጳጉሜን ዕለታት፡ የጾምና የምጽዋት፥ የጸሎትና የስግደት ሱባኤያዊ ምግባራችንን፡ በያለንበት በማካኼድ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ ሃይማኖታዊ ተልእኳችንን መፈጸማችን ይታወሳል።

"«ታዲያ! እንዲያ ባለው፡ በተሟላው፡ ሥጋዊ፥ ነፍሳዊና መንፈሳዊ ትጥቃችን ተሰልፈን፥ በተጨማሪ፡ የፀረ-ኢትዮጵያነትን፡ የኃይል ጥቃት መክተን በመቋቋም፡ የተከናወነው፡ ያ፡ የዓመቱ ተጋድሏችን፡ ተፈላጊውን መልካም ፍሬ በማስገኘት፡ ተሟልቶ መፈጸሙንና በእኛ አሸናፊነት ማብቃቱን የተገነዘቡ፡ የቅርብና የሩቅ ሰብአውያን ወገኖቻችን፡ ዛሬስ ስንቶች ይኾኑ? በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታዊና ምግባራዊ ኃይል የተገኘውን፡ ይህን መልካም ፍሬ፡ እያንዳንዳችን ብናውቀውም፡ ለሌሎች የማሳወቅ ግዳጅ እንዳለብን ደግሞ፡ እናምንበታለን።

"«ይህን የድምዳሜ አሳብ መሠረት በማድረግ፡ እውነታውን፡ ለሌሎች ለመግለጽና ለማስጨበጥ ስንል፡ ከላይ ለተጠቀሰው ጥያቄ፡ ስንሰጥ የቆየነውን መልስ፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ አብራርተንና አስፋፍተን አቅርበነዋል። ስናቀርበውም፡ እንዲሁ ዝም ብለን አይደለም።

"«በአንድ ወገን፡ የዛሬውን የኢትዮጵያ ትውልድ በሚመለከት፡ በኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና ውስጥና መካከል፡ እርስ በርስ እስከመተላለቅ ባደረሰ መጠን፡ እየተካረረ የኼደው መቃቃርና መወጋገዝ፥ ጥላቻና ፀብ፡ እየባሰ እንደቀጠለ ይታያል። በሌላው ወገን ደግሞ፡ ‹ሕዝባዊ አገዛዝ [Democracy]› በሚባለው ሰብኣዊ ይትበሃል ሽፋን፡ ሥልጣናቸውን፡ በየተወሰኑ አገሮች ኾነ፡ በመላው ዓለም ዘርግተው ባሰፈኑት፡ የሰዎች ኃያላን መንግሥታት የበላይ መሪነት በሚካኼደው፡ ሥልታዊ የአገዛዝ ምርጫ ምክንያት፡ በዓለሙ ሕዝቦች ላይ፡ በተባባሰና በተጠናከረ ኹኔታ፡ እየተስፋፉ የኼደውን ጠንቀኛ ችግር እንመለከታለን።

"«በዚህ ጊዜ፡ '**ዑቁ ኢያስሕቱክሙ! ወአመ ሰማዕክሙ ቀትለ፥ ወድምፀ ፀባኢት፡ ዑቁ ኢትደንግፁ፣ እስመ ግብር ይከውን ዝንቱ፤ ወባሕቱ፡ አኮ በጊዜሃ ዘየኀልቅ። ወይትነሥኡ ሕዝብ፡ ዲበ ሕዝብ፤ ወነገሥት፡ ላዕለ ነገሥት። ወይመጽእ ረኃብ፥ ወብድብድ፥ ወድልቅልቅ፥ ወሀከክ፡ በበብሔሩ። ወዝንቱ ኵሉ፡ ቀዳሚሁ ለሕማም።**

"«'ጦርነትን፥ የጦርነትንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊኾ ን ግድ ነውና፡ እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ! አትደንግጡ! ነገር ግን፡ ፍጻሜው ገና ነው፤ ሕዝብ፡ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም፡ በመንግሥት ላይ ይነሣሉ፤ በየሀገሩም፡ ረኃብ፥ ቸነፈርም፥ የምድር መናወጥም፥ ሁከትም ይኾናል። እነዚህም ኹሉ፡ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።' ተብሎ፡ በመምህራችን፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ የተነገረን መለኮታዊ ቃል፡ መርሕ ኾኖ የሚያረጋጋንና የሚያነቃቃን፥ የሚያጠናክረንና የሚመራን እውነታ ስለኾነ፡ ትዝ ይለናል። (ማቴ. ፳፬፥ ቍ. ፬-፯።)

"«ለዚህ እውነታ ማስረጃነት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በዓለሙ ኹሉ፡ በገሃድ ሲካኼዱ፥ በግዘፍም ሲፈጸሙ የሚታዩትን ኹኔታዎችና ድርጊቶች፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ፡ አግባብና አስፈላጊ ይኾናል።

"«እነዚህም፡ በእያንዳንዱ፡ የምድሪቱ አህጉራት ዘንድ ኹሉ የሰፈነውን፡ የአስተዳደር ጒድለትና የፍትሕ ቀውስ፥ ምስቅልቅሉ በወጣው፡ ሙዓለ ንዋይና በጥቂቶች የሀብት ክምችት ምክንያት የተናጋውን፡ የዓለማውያኑን ኑሮ፥ በሥራ እጦትና በድኅነት ሥቃይ፥ በቀሣፊ ደዌያትና በመዘዘኛ ሕክምና፥ በሌሎች አገሮች ሕዝባዊ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ በመግባትና በሃይማኖት ሽብርተኞች ጀብድ መነሻነት የተስፋፋውን፡ የእርስ በርስ ዕልቂትና የጦርነት ማዕበል የሚያጠቃልሉ ናቸው።

"«ይህ ብቻ ሳይበቃ፡ በተፈጥሮ ኃይላትና በሰው-ሠራሽ ጥፋት፡ እየደረሰ ያለውን የተለያየ መዓት፥ በተለይም፡ ሕዝብ፡ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም፡ በመንግሥት ላይ የመነሣሣቱ ነውጥ፥ በመጨረሻም፡ በአምልኮ ባዕድና በክፋት መንፈስ መስፋፋት ረገድ፡ እየጨመረና እየተባባሰ፥ እየከበደና እየተወሳሰበ የኼደውን እጅግ አሳዛኝ ኹኔታ፡ ከዚህ ጋር ዐብሮ ማውሳት ይቻላል።

"«እነዚህን የመሰሉት፡ የተፈጥሮና ሰው-ሠራሽ መቅሠፍቶች መበርከት፥ ጠቅላላውን፡ የሰውን ልጆች ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊና ኹለንተናዊም ጽኑ ችግር አስተውሎ በማገናዘብ፡ ይህን እውነታ፡ ኹሉም በያለበት፡ በጠለቀና በመጠቀ፡ ሃይማኖታዊ አእምሮ፡ በቀላሉ ሊመለከተው ይቻለዋል።

"«በዚህ፡ '**ሰላም፡ ለኢትዮጵያ!**' በሚለው ስያሜና ዓላማ፡ ባለፉት ዓመታት የፈጸምናቸው፡ የጳጉሜ ጾምና ጸሎት ምሕላዎቻችን፡ እንደማንኛዎቹም የጾመ-ኢትዮጵያ ሱባኤዎቻችን፡ ያስገኙት ፍሬያማ ውጤት አለ።

"«ይኸውም፡ **'እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ሰላም፡ የሰብአዊው ፍጥረት መጀመሪያ ከኾኑት፡ ከአዳም እና ሔዋን ህልውና አንሥቶ፡ እስከዛሬ፥ ለዘለዓለምም፡ በቅዱሱ ኪዳን አማካይነት፡ ለሰው ልጆች ኹሉ ተሰጥታለች፤ ነገር ግን፡ ተጠብቃ የኖረችው፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ ብቻ በመኾኑ፡ እኛ ልጆቻቸው፡ ይህን እውነታ፡ ለእየራሳችን ዐውቀን፥ ለሌሎችም ለማሳወቅ መቻላችን ነው።"** በሚል አጭር ቃል ሊገለጽ ይቻላል።

"«እግዚአብሔራዊ የኾነውን፡ ይህን የልዕልና ዕውቀት ለማግኘት ደግሞ፡ በቅድሚያ፡ ራስን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማብቃት ያስፈልጋል።

"«እንግዴህ፡ እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ 'መልካም ፍሬ' ከተባለው፡ ከዚህ ብቅዓት የተደረሰው፡ እንዲሁ በከንቱ፥ ወይም፡ በቀላሉ ሳይኾን፡ **በእውነተኛ ንስሓ ጠርቶ ከተመራ፡ ሃይማኖታዊ ምግባር** መኾኑ፡ በአጽንዖት ሊታወቅ ይገባል። ያም ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ለአገራችንና ለሕዝቧ፥ እንዲሁም፡ በስደት ና በልዩ ልዩ ምክንያት፡ በመላው ዓለም ለተበተነው ወገናችን፥ ለቀረውም ዓለም ጭምር፡ እውነተኛዪቱን **የእግዚአብሔርን ሰላም** ለማስገኘት ይበቃ ዘንድ፡ በቅድሚያ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ሃይማኖትና ምግባር ከታነጸው፡ ከእየራሳችን ንጹሕ ልቦና የመነጨው ንስሓችን፡ በፈጣሪና በቅድስት እናቱ መንበር ፊት፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ መቅረብ እንዳለበትና እንደነበረበት፡ ያለጥርጥር ይታወቃል።

"«እንዲህ ካልኾ ነ በቀር ደግሞ፡ ይህን የመሰለው ሕያው ጸጋ፡ በሌላ ዘዴና መንገድ፡ ከቶ ሊገኝ የሚቻል አይደለም። አዎን! በዚያ ንስሓችን ላይ ተመሥርቶ የተካኼደውና የተፈጸመው፡ ጾምና ጸሎት፥ ምጽዋትና ስግደት፡ እነሆ፡ ያን፡ በእየራሳችንና በአገራችን ላይ የታየውን፡ የመልካም ፍሬ ምርት፡ በእውን አበርክቶ ለማቅረብ ተቻለው።

"«ይህን እውነታ በሚመለከት፡ ቀደም ብለውና በጊዜው ተላልፈው በነበሩት መልእክቶቻችን አማካይነት፡ ዘለዓለማውያን የኾኑ፡ አንዳንድ ቊም-ነገሮች፡ በተቻለ መጠን፡ ለኹሉ ተሠራጭተው እንደነበረ ይታወሳል።

"«እነዚያን ቊም-ነገሮች የተመለከታቸውና የሰማቸው፡ አስተዋዩ ኢትዮጵያዊ ወገን ኹሉ፣ ወንድ ኾነ ሴት፡ የዚህን እውነታ ምንነት፡ በቀላሉ እንደተረዳው ሊታበል አይቻልም። አዎን! ይኸው ሃይማኖታዊ ምግባራችን፡ ለዚህ የአሸናፊነት ፍሬ የበቃው፡ የዛሬ ኹለት ሺህ ስምንት ዓመት፡ በሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ በጸደቀችውና በጸናችው፡ በእውነተኛዪቱ **የእግዚአብሔር ሰላም** ፍቱን መሣሪያነት መኾኑን ስንገልጽ፡ እጅግ ደስ እያለንና ይህን ላደረገ ፈጣሪያችን፡ የሚገባውን ምስጋናችንን እያቀረብን ነው።

"«የዚህች፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** ፍቱን መሣሪያነት፡ በሃይማኖትም፥ በምግባርም የተረጋገጠው፡ በዚያ፡ በአዲስ ኪዳኑ፡ የምሕረት ዘመን መባቻ [መግቢያ] ነበር፤ ያም ዘመን፡ በዲያብሎስ አበጋዝነት በሚመራው፡ የሰዎች የክፉትና የጥፋት ኃይላት፥ በኃጢኣትና በሞትም ላይ፡ እርሷ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ የድል አድራጊነት ዘውድን፡ የተቀዳጀችበት ምዕራፍ ነበር፤ ከዚያም ወዲህ፡ ይኸው የአሸናፊነት ህልውናዋ፡ በእውነተኞቹ የእግዚአብሔር ወገኖች ልቦና ውስጥ፥ **በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥትም** አማካይነት፡ የምድርን ኹለንተና አጥለቅልቆና በዓለም ሕዝቦች መካከል ሰፍኖና ገንኖ ይታያል።

"«ይኹን እንጂ፡ 'ለኢትዮጵያ፡ ሰላምን ለማስገኘት' በሚል ዓላማ፡ በ'ሰላም ለኢትዮጵያ' የኅዋ ሰሌዳ አሳሳቢነት ተጀምረው፡ ባለፉት ዓመታት የተካኼዱት፡ የጿጉሜ አጽዋማትና ጸሎታት፡ 'ለኢትዮጵያ፡ ሰላምን አስገኝተዋል!' የሚለው፡ ይህ፡ ከዚህ በላይ የተሰጠው መግለጫ፡ በዘመኑ 'ሃይማኖት-የለሹ' ኢትዮጵያዊ ትውልድ ዘንድ፡ ግራ ሊያጋባና ተቀባይነትን ላያገኝ ይችላል።

"«በእርግጥ፡ 'ሃይማኖት የለኝም!' ሊል በሚችል ሰብአዊ ፍጡር ዘንድ፥ ወይም፡ የሃይማኖት ጒድለት ባላቸው ዘንድ፡ ይህን የመሰለው፡ ግራ የመጋባትና የመጠራጠር ችግር መፈጠሩ እንደማይቀር ግልጽ ነው።

"«ያ፡ ግራ የገባውና የሚጠራጠረው ወገን፡ ለዚህ ግራ መጋባትና ጥርጣሬ የተዳረገው፡ በራሱ ፍላጎትና ምርጫ እንጂ፡ ያስገደደው፡ ሌላ ሰብአዊ፥ ወይም መንፈሳዊ ፍጡር፥ ወይም፡ የበላይ ኃይል ኖሮበት አይደለም።

"«ወይም፡ ይህን እውነታ የመቀበል ፍላጎት ኖሮትም ቢኾን፡ ይህንኑ ምርጫ ለማድረግ፡ ሥልጣንና መብት፥ ችሎታም አጥቶ አይደለም። የዚያ ወገን ባልደረባ የኾነው፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ለዚያ፡ ግራ ለሚያጋባውና ለሚያጠራጥረው፥ ደካማና እኩይ ለኾነውም ለተፃራሪው የመንፈስ ወገን፡ ራሱን አሳልፎ የሰጠው፡ በገዛ ፈቃዱ ነው።

"«እንዲህ፡ የሃይማኖት-አልባነት አባዜ የተጠናወተው፥ ወይም፡ የሃይማኖት ጉድለት ያለበት ተጠራጣሪ (መናፍቅ) ኾኖ፡ ግራ የተጋባውና ወላዋይ የኾነው፡ አዎን! በራሱ ምርጫ ነው፤ ስለዚህ፡ እነሆ፡ **በውስጡም፥ በውጭውም፡የእግዚአብሔርን ሰላም አጣ!** ለጠንቀኛ ጽኑ ብኩንነትም ተጋልጦ፡ ለክፉው ፍዳ ሊዳረግ በቃ! ከዚህ የተነሣም፡ ይኸው ምድራዊና ሥጋዊ ኑሮውን፡ በሥቃይ የሚገፋ ኾነ!

"«ይህም ማለት፡ 'ያ ሰው፡ እውነታውን አምኖ መቀበሉ ቀርቶ፡ **ስለእግዚአብሔር ሰላም** የምትናገረውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት ሰምቶና ተረድቶ፡ ለማወቅ እንኳ ፍላጎት፡ ጨርሶ የሌለው ፍጡር መኾኑን፡ ለራሱም፥ ለፈጣሪውም፥ ለሌላውም ፍጡር አረጋግጦ አሳየ!' ማለት ነው፤ በዚህ ግብሩም፡ የተፈጠረባትንና ባሕርዩ የኾነችውን፡ 'ኅሊና ' የምትባለውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ ከራሱ ውስጥ ገላልጦ ለማወቅ፡ ሰብአዊ ፍላጎቱን ከማነሣሣት ይልቅ፡ ላልተፈጠረበት የግራ-ቢስነት ሓሰት፡ ራሱን ለማስገዛት መጣርን መፍቀዱንና መምረ ጡን፡ በግል አስተሳሰቡና በህልውናው አካኼድ፡ እነሆ፡ ራሱ መሰከረ።

"«ስለዚህ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ባለማወቅ ጨለማ ተውጦና በድንቍርና መረብ ተተብትቦ፥ በሓሰትም እሥራት ተቀፍድዶ መኖርን የመምረ ጥ፥ ያን ኑሮ ተቀብሎ፡ በዚያ አሳዛኝ ኹኔታ የመኖርም ዝንባሌው፡ ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች፡ ከአዳምና ከሔዋን አንሥቶ የነበረ ነው።

"«ያም ኹኔታ፡ ዛሬ ያለ እና ወደፊትም፡ እስከዓለም ፍጻሜ የሚቀጥል መኾኑ፡ ይኸው፡ በግልጽ ይታያል። የእግዚአብሔርን እውነት ለማወቅ አለመፈለጉና ወደዚያ ግብ ለመድረስ፡ ጥረቱ ቀርቶ፡ አንዳችም ዓይነት ሙከራን አለማድረጉ፡ ከዚያ ፍላጎት አለመኖር የተነሣ መኾኑ የታወቀ ነው።

"«ይህ አቋሙ፡ ከላይ በተወሳው የሃይማኖት ጉድለትና የአላዋቂነት አስተሳሰብ የተመረዘውን፡ ራሱን፡ ሰብአዊዉን ፍጡር፡ የቱን ያህል እንደጎዳው፡ ለራሱ አረጋግጦ ለማስረዳት፡ የራሱ፡ የዛሬው የሰው ልጅ፡ አሳዛኝ ኹኔታ ይበቃል።

"«አዎን! ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ፡ በፈጣሪ በኩል የተካኼደው፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ ገልጦ የማሳየቱና አግዝፎ የማሳወቁ ነገር፡ ምስጢር ሳይኾን፡ ገሃድ ወጥቶ፡ በእውን የተከሠተውና የተፈጸመው፡ የዛሬ ኹለት ሽህ ስምንት ዓመት መኾኑ፡ በታማኞቹ የቅዱሱ ኪዳን አማኞች ዘንድ፡ በሃይማኖት፡ ተቀባይነትን አግኝቷል።

"«ይህም ማለት፡ ቀድሞ የነበረችውና ኋላ፡ በራሳቸው፡ በፍጡሮቹ ሰዎች የተሳሳተ የምርጫ ጠንቅ ምክንያት፡ ለበርካታ ሽህ ዓመታት፡ ታጥታ የቆየችውን፡ ያቺኑ፡ አማናዩቷን፡ **የእግዚአብሔርን ሰላም፡** ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ቤዛነት፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ልጆች ብቻ ሳይኾን፡ ለመላው ፍጥረተ-ዓለምና ለሰው ዘር ኹሉ፡ መልሶ ለማስገኘት የተቻለ መኾኑ፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ፡ በይፋ የተገለጠበትና የተረጋገጠበት ጊዜ፡ እስካኹኗ ቀን ድረስ፡ 'የኹለት ሽህ ስምንት ዓመታት ዕድሜን አስቆጥሯል!' ማለት ነው።

"«ነገር ግን፡ አብዛኛው የሰው ወገን፡ ይህን፡ **የእግዚአብሔርን ሰላም፡** በውስጣችንና በመካከላችን፥ ባካባቢያችንም፡ በእውን የመኖሯን ተጨባጭ እውነታ በሚመለከት፡ ምንም ዓይነት ድርጊት እንዳልተፈጸመ፥ ምንም ዓይነት ኹኔታም እንዳልደረሰ፡ እንደፍሬ-ቢስና እንደከንቱ ነገር ቆጥሮ፡ በንቀት ስለተወው፡ እነሆ፡ ሰብኣዊው ችግርና ሥቃይ፡ እየጨመረ ኼዶ፡ በእርስ በእርስ ጦርነቶች ውስጥ ተዘፍቆ እየተላለቀ ካለበትና ይህንኑ ይዞታውን ከቀጠለበት፡ ከአኹኑ ደረጃ ሊደርስ ችሏል።

"«አዎን! በመጀመሪያ፡ በሥጋቸው ወንድና ሴት፥ በነፍሳቸውም ደግሞ፡ በራሱ መልክ አድርጎ የፈጠራቸው፥ በመጨረሻም፡ በቅዱስ መንፈሱ፡ የልጅነትን ጸጋ ያቀዳጃቸው እግዚአብሔር፡ ከመለኮታዊ ዕውቀቱና እውነቱ፥ ፍቅሩና ደስታው ጋር፡ <u>ሰላሙን</u> ጭምር፡ ለእኒያ፡ ለመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን፡ በምልዓትና በስፋት ሰጥቷቸው ነበር።

"«እነርሱ ግን፡ በሥጋ ወልደው ከሚያሳድጉ፡ ከሰዎች ወላጆች ይልቅ፡ እጅግ በበለጠ ደግነትና ርኅራኄ፥ እንክብካቤና ምቾት የያዛቸውን፥ ያን የመሰለውን፡ ፍጹም የሕይወት ጸጋና ሀብት ያጎናጸፋቸውን፡ የሚያውቁትን ፈጣሪያቸውን ትተው፡ የማያውቁትን፡ የክፋትና የሓሰት፥ የጥላቻና የጦርነት አባትና አበጋዝ የኾነውን ዲያብሎስን ተከተሉ።

"«ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ያች፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** በሰው ልጆች ዘንድ፡ ከደረሰባትና ከሚደርስባት የፍላጎት ማጣትና የፈቃደኝነት ጉድለት የተነሣ፡ ከሌሎቹ የደግነት ባሕርያት ጋር ዐብራ፡ ከሰዎች ልቦና ታጣች፤ ተሠወረች። በእርሷ ፈንታ፡ የእርሷና የመሰሎቿ ደጋግ ባሕርያት ተቃራኒዎች የኾኑት፡ የክፋት ጠባያት፡ በሰዎች ልቦና ውስጥ ተተኩ፤ ሰፈኑ።

"«‹ለመኾኑ፡ **'የእግዚአብሔር ሰላም'** ስንል፡ ምን ማለታችን ነው? **'የእግዚአብሔር'** የተባለችው **'ሰላም'**፡ ምን ዓይነት ናት? ሌላ ሰላም፥ ወይም፡ ሌሎች ሰላሞች አሉን?› የሚል ጥያቄ፡ የእግዚአብሔርን እውነት በማያውቁና በማያምኑ ዘንድ መኖሩ አይቀርም፤ ሊጠየቅ የሚያስፈልግ፥ አጥጋቢ መልስ ሊስሰጠውም የሚቻል፡ ተገቢ ጥያቄ ነው።

"«መልሱም፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል የሚጠቃለል ይኾናል፡- ‹**'የእግዚአብሔር ሰላም'** ስንል፡ ከፍጹሟ **የእግዚአብሔር ፍቅር** የምትመነጨውን፡ ጥንታዊቷንና ብቸኛዪቱን፥ ደጊቱንና መልካሚቱን፥ ንጹሒቱንና እውነተኛዪቱን <u>ሰላም</u> ማለታችን ነው።

"«እርሷም፡ **'አነ ውእቱ፡ ፍኖተ-ጽድቅ ወሕይወት፤ ...ወአንስ፡ በእንተ ዝንቱ ተወለድኩ፤ ወእንበይነ ዝንቱ መጻእኩ ውስተ ዓለም፣ ከመ እኩን ሰማዕተ በጽድቅ!'**

"«'እኔ፡ የእውነት መንገድ፥ ሕይወትም ነኝ፤ ሰው ኾኜ የተወለድሁት፥ ወደዚህም ዓለም የመጣሁት፡ ስለእውነት ምስክር ልኾ ን ነው!' ብሎ በተናገረው፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ሰው መኾን፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** በዚህ ዓለም፡ በሰዎች መካከል፡ በሕያው ሰውነት፡ ገዝፋ ታይታለች፤ ተመላልሳለች።

"«ይህችው **የእግዚአብሔርዋ ሰላም፡** በመለኮታዊ ሰውነቱ የተገለጠችበት፡ **የሰላሙ ንጉሥ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡** ከኢትዮጵያዊቷ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ተወልዶና አድጎ፡ በዚህ ዓለም የተመላለሰበትን ሰብአዊና መለኮታዊ ተልእኮ እንደፈጸመ፡ የተናገራቸውን ሕያዋን ቃላት፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ፡ እግዚአብሔር፡ **ስለሰላም ምስጢርና ስለምንነቷ፡** ለፍጥረተ-ዓለሙ ያደረገውንና የገለጠውን፡ ዕፁብ ድንቅ የኾነውን፡ መለኮታዊ ሥራውን፡ በእውን አረጋግጦ ያሳያል፤ እነዚህም፦

"«፩ኛ፡ የሾህ አክሊሉን ተቀዳጅቶ፡ በመስቀል ዙፋኑ ላይ ከመቸንከሩ በፊት፡ በዋዜማው ምሽት፡ **'ወእንዘ ይበልዑ፡ ነሥአ ኅብስተ፡ እግዚእ ኢየሱስ፤ ወባረከ፤ ወፈተተ፤ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ፤ ወይቤሎሙ፦ ‹እንክሙ! ብልዑ! ዝ ውእቱ ሥጋየ!› ወነሥአ ጽዋዐኒ፤ ወአእኰተ፤ ወወሀቦሙ፣ እንዘ ይብል፦ ‹ስትዩ እምኔሁ፡ ኵልክሙ! ዝ ውእቱ ደምየ፡ ዘሐዲስ ሥርዓት፣ ዘይትከዐው፡ በእንተ ብዙኃን፡ ለኅድገተ ኃጢአት!›**

"«'እየበሉ ሣሉ፡ ጌታችን ኢየሱስ፡ ኅብስቱን አነሣ፤ ባረከውም፤ ቈረሰውም፤ ለደቀ-መዛሙርቱም ሰጣቸው፣ እንዲህ እያለ፦ ‹እንካችሁ! ብሉ! ይህ፡ ሥጋዬ ነው!› ጽዋውንም አነሣ፤ አመሰገነም፤ ሰጣቸውም፣ እንዲህ እያለ፦ ‹ስለብዙዎች የኃጢአት ስርየት የሚፈስስ፡ የአዲሱ ሥርዓት [ኪዳን] ደሜ፡ ይህ ነውና፡ ኹላችሁም፡ ከእርሱ ጠጡ!›' (ማቴ. ፳፮፥ ፳፮-፳፰።)

"«፪ኛ፡ ራቁቱን፡ ተቸንክሮ ሣለ፡ **'ወይቤ፡ እግዚእ ኢየሱስ፦ አባ! ሥረ ይ ሎሙ! እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ!'**

"«'ጌታችን ኢየሱስ፦ ‹የሚያደርጉትን አያውቁምና፡ ይቅር በላቸው!›' (ሉቃ. ፳፫፥ ፴፬።)

"«፫ኛ፡ በትንሣኤ አካል፡ ከመቃብር ተነሥቶ፡ ደቀ-መዛሙርቱ፡ በኀዘንና በቀቢጸ-ተስፋ (ተስፋ በመቍረጥ)፥ በፍርሃትና በድንጋጤ ተውጠውና ተሰብስበው በነበሩበት ቤት ውስጥ፡ በመካከላቸው ተገኝቶ፡ **'ሰላም ለክሙ!'**

"«'ሰላም፡ ለእናንተ ኾነ!' ብሎ ያስሰማቸው ቃሎቹ ናቸው። (ዮሓ. ፳፥ ፲፱።)

"«እኒህን ቃላት የተናገረው፡ ይኸው እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የክፋትና የሓሰት [የኃጢአት]፥ የጥፋትና የሞት አበጋዝ የኾነው ዲያብሎስ፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት ጀምሮ ያስነሣውን፡ የጥላቻና የግድያ፥ የደም መፋሰስና የዕልቂት ጦርነት፡ በፍቅር ቤዛነቱ የመስቀል ኃይል ተሠውቶ፡ የዘር ጠላቱን፡ ፈጽሞ ድል በመንሣት፡ ለአንዴና ለዘለዓለም አስወግዶ የደመሰሰው፡ የመልካምና የእውነት [የጽድቅ]፥ የልማትና የሕይወት ባለቤት የኾነው ነው።

"«አዎን! ከተቸነከረበት መስቀሉ ሳይወርድ፡ ነፍሱ፡ ከሥጋው ተለይታ፡ ዘለዓለማዊዉን ነጻነት፡ ለሙታን ነፍሳት ለማብሠር፡ ወደሲዖል ስትኼድ፥ ሥጋው ደግሞ፡ ወደመቃብር ወርዶ፡ ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት፡ የሰንበትን ዕረፍት ካረፈ በኋላ፡ መለኮት የተዋሐዳቸው፡ ሥጋውና ነፍሱ፡ እንደገና አንድ ኾነውለት፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው፥ ወደሰማይም ያረገው፥ በአባትና እናቱ ዙፋን ቀኝ ባለው፡ የእኩልነት ዙፋኑም የተቀመጠው፥ በመንፈስ ቅዱስነቱም፡ ወደዓለሙ ተመልሶ፡ እነሆ፡ ለ፯ሺ፭፻፰ ዓመታት በሰፈነችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥቱ፡** ከንግሥተ-ነገሥታት ወንግሥታት እናቱ፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ጋር፡ በንጉሠ ነገሥት ወንግሥታትነትና በሊቀ ካህናትነት፡ እየመራና እያስተዳደረ የሚገኘው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

"«**የእግዚአብሔር ሰላም፡** እንግዴህ፡ ይህች ናት።

"«በእርሷ አንጻር ደግሞ፡ ማለትም፡ **የእግዚአብሔር** እንደኾነችው፡ እንደዚችው **ሰላም፡** ማስመሰያና የሓሰት የኾኑ፡ የሰዎች፥ ወይም የዲያብሎስ፡ የምትሓት ሰላሞች አሉ።

"«ስለእነዚህ የሰላም ዓይነቶች፡ አስከፊ ምንነትና መራራ ፍሬነት፡ እዚህ ላይ፡ ብዙም ማተት፡ የሚያስፈልግ አይመስልም፤ ምክንያቱም፡ ከአዳምና ሔዋን ጊዜ አንሥቶ፡ በቃኤል ወገኖች፡ እየተካኼደ ባለው፥ የአቤል ወገን በኾነው፡ በኖኅ ዘመን የደረሰው፡ የጥፋት ውኃም እንኳ፡ ሊያሻሽለው ሳይችል ቀርቶ፡ ይኸው፡ እስከዛሬ በቀጠለው፡ የሰው ልጆች አስተሳሰብ፥ አኗኗርና ድርጊት፡ እነሆ፡ በገሃድ ስለሚታይና በግዘፍ ስለሚዳሰስ ነው።

"«እነዚህን የመሰሉትን የሰላም ዓይነቶች፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን 'የኢትዮጵያ ልጆች' አንቀበላቸውም፤ ዕውቅናም አንሰጣቸውም።

"«እኛ አምነን፥ ዕውቅናንም ሰጥተን የተቀበልናት፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** ይህች ናት፡- በጥንቱ የፍጥረት ዘመን፡ ለአዳምና ለሔዋን የተሰጠች ኾና ሣለች፡ ነገር ግን፡ እነርሱና ከእነርሱ በኋላ የተተኩት፡ 'የሰው ልጆች' የተባሉት ዘሮቻቸው፡ እርሷን፡ ካለመፈለጋቸው የተነሣ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ከእነርሱ ተለይታ፥ ይኹን እንጂ፡ 'የእግዚአብሔር ልጆች' በተባሉት ዘሮቻቸው በኩል ስለተፈለገች፡ በእነርሱ ዘንድ ተወርሳ፡ በመከበርዋ፡ እነርሱን ጠብቃ የቆየችዋን ነው፡ እኛ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** የምንላት።

"«በመጨረሻውም ዘመን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡- **'ሰላምየ፡ አኀድግ ለክሙ፤ ወሰላመ አቡየ፡ እሁበክሙ፤ አኮ፡ በከመ ይሁብ ዓለም፡ ዘእሁበክሙ አነ።**

"«'ሰላሜን እተውላችኋለሁ! የአባቴንም ሰላም እሰጣችኋለሁ! እኔ የምሰጣችሁ ሰላም፡ ዓለም የሚሰጠውን ዓይነት አይደለም።' ብሎ ተናግሮላት፡ ላልፈለጓትና ለተዉዋት፡ ለሰው ልጆች ሳይቀር፡ በጸጋ የተመለሰችውን፡ **የእግዚአብሔርን ሰላም** ነው፡ እኛ፡ **'የእግዚአብሔር ሰላም'** የምንላት። (ዮሐ. ፲፬÷ ፳፯።)

"«መምህራችን እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ **ስለእግዚአብሔር ሰላም** ምስጢር ምንነት፡ ለይቶ፡ ይህን መለኮታዊ ቃል የተናገረው፡ ለእነማን እንደኾነ፡ አበክሮ ማወቅና መገንዘብ÷ **አተኵሮ መመልከትም ያስፈልጋል፤ ይገባልም።**

"«አዎን! **የእግዚአብሔርን ሰላም** የምናገኛት፡ እርሱን ብቻ፡ ከምንም÷ ከማንምም በላይ÷ ከየራሳችንም በላይ ሳይቀር፡ በፍጹም እውነተኛነት፡ የምንወድድ መኾናችንን ስናረጋግጥ ብቻ ለመኾኑ፡ የተናገረውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ ሌላውን ቃሉን፡ እስኪ እንስማ!

**"«'ኢይምሰልክሙ ዘአምጻእኩ ሰላመ ለምድር፤ አላ መጥባሕተ። ...ዘይመጽእ ኀቤየ÷ ወይፈቅድ ይትልወኒ፡ ለእመ ኢጸልአ አባሁ÷ ወእሞ÷ ወብእሲቶ፣ ወቤቶ÷ ወውሉዶ÷ ወአኀዊሁ÷ ወአኃቲሁ÷ ወዓዲ ነፍሶሂ፡ ኢይክል ከዊነ ረድእየ። ...ወሰብአ ቤቱ፡ ይፃረሮ ለሰብእ።**

**"«'...ዘይፈቅድ ይትልወኒ፡ ይጽልአ ለነፍሱ! ወያጥብዕ! ወይንሣእ መስቀለ ሞቱ! ወይትልወኒ! ወዘይፈቅድ፡ ያድኅና ለነፍሱ፡ ለይግድፋ፤ ወዘሰ ገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ፡ ይረክባ። ወምንተ ይበቍዖ ለሰብእ፡ ለእመ ኵሎ ዓለመ፡ ረብኀ፤ ወነፍሶ፡ ኀጕለ። ወምንተ፡ እምወሀበ ሰብእ፡ ቤዛሃ ለነፍሱ?"**

"«'ሰላምን፡ በምድር ላይ ያመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ። ...ማንም፡ ወደእኔ የሚመጣ÷ ሊከተለኝም የሚወድ ቢኖር፡ አባቱንና እናቱን÷ ሚስቱንም÷ ቤቱንም÷ ልጆቹንም÷ ወንድሞቹንም÷ እኅቶቹንም÷ የራሱን ሕይወት እንኳ ሳይቀር ባይጠላ፡ ደቀ-መዝሙሬ ሊኾ ን አይችልም። ...ለሰውም፡ ቤተሰቦቹ፡ ጠላቶች ይኾኑበታል።

"«'...ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር፡ ራሱን ይጥላ! ይጨክንም! የሞቱን መስቀልም አንሥቶ ይዞ፡ ይከተለኝ! ራሱን ሊያድን የሚወድ ኹሉ፡ እንዲህ ያድርግ! ስለእኔ፡ ራሱን፡ እንዲህ የጣለማ፡ ራሱን፡ ድኖ ያገኘዋል። ሰው፡ በሥጋው ብቻ፡ ዓለሙን ኹሉ ቢያተርፍ÷ ለነፍሱ የሚረባውን፡ የመንፈሱን ግን ቢያጐድል፡ ምን ይጠቅመዋል? ሰው፡ ዐውቆ ቢኾን ኖሮ፡ ስለነፍሱ ጠቀሜታ፡ ምን ዓይነቱን ቤዛ ሊከፍል በወደደ ነበር?!' (ማቴ. ፲÷ ፴፬-፴፱፤ ፲፮÷ ፳፬-፳፮። ሉቃ. ፲፬÷ ፳፮-፳፯።)

"«አዎን! ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የተወለደው፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ እኒህን ቃላት የተናገረው፡ ሕያው መመሪያውን አምነውና ተከትለው ለፈጸሙት፡ ለቀደሙትና ዛሬም ለሚፈጽሙት፡ አማኝና ታማኝ ለኾኑት ወገኖቹ ነው።

"«እንግዴህ፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** የምትገኘውና የምትኖረው፥ የምትሰፍነውም፡ በሰው ልቦና ውስጥ ነው። የእግዚአብሔር እንደኾኑት፡ እንደመንፈሱ፥ እንደመንግሥቱ፥ እንደእውነቱ፥ እንደዕውቀቱ፥ እንደፍቅሩ፥ እንደሕይወቱ፥ እንደብርሃኑ፥ እንደሰንበቱና እንደት ንሣኤው ኹሉ ማለት ነው።

"«ስለዚህ፡ ከላይ፡ በመልእክታችን መግቢያ ጀምሮ እንደገለጽነው፡ አንድ ሰብኣዊ ፍጡር፣ ሴትም ኾነች ወንድ፣ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት ከሌለው፥ ወይም፡ የዚሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት 'ተከታይ ነኝ!' እያለ፥ ነገር ግን፡ በሃይማኖቱ ጐደሎነት ምክንያት፡ ተጠራጣሪ ከኾነ፡ በዚያ ሰው ልቦና ውስጥ፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** ልትገኝ፥ ልትኖርና ልትሰፍን ከቶ አትችልም፤ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** በዚያ ሰው ልቦና ውስጥ ከሌለች ደግሞ፡ ያ ሰው፡ በውስጡ፡ ለራሱ ብቻ ሳይኾን፡ ከውጭውና በውጭ ካሉት፡ የተፈጥሮ ወገኖቹ፥ የሥነ-ፍጥረቱ አካል አባሎች ከኾኑት ፍጡራንም ጋር፡ እውነተኛዋን ሰላም አግኝቶ፡ በሰላም ሊኖር፡ ፈጽሞ አይቻለውም።

"«ይህ ነው፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ችግር። በቀደሙት ወላጆቹና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ስምምነት አፍርሶና ክዶ፡ በዚያ፡ በተቀደሰው ቃል ኪዳን ላይ፥ በሃይማኖት ምልክቶቹና በምግባራዊው ሥርዓቱ ላይ ጭምር፡ ግልጽ ዓመፅንና የአምልኮ ምንዝርናን፡ በገሃድ እያካኼደ ስላለ፡ በራሱ ልቦና ውስጥ ኾነ፡ በአገሩና በወገኑ፥ በመካከሉና እርስ በርሱም፡ **እውነተኛዋን የእግዚአብሔርን ሰላም፡** በቅርብ ሊዳስሳትና ሊያገኛት ቀርቶ፡ በሩቁም እንኳ፡ በተስፋ ሊያያት፡ ከቶ አልተቻለውም።

"«ከዚህ የተነሣ፡ በአገር ውስጥም ኾነ፡ ከአገር ውጭ ያሉት፡ 'የኢትዮጵያ ነን!' እያሉ የሚመጻደቁት፡ የቤተ-ሕዝብ፥ የቤተ-ክህነትና የቤተ-ምልክና ወገኖች፡ በመካከላቸውና እርስ በርሳቸውም እንኳ ቢኾን፡ **የእግዚአብሔርዋን ሰላም** ሊያገኟት አልቻሉም።

"«ያ ቀርቶ፡ በሰብኣዊው፥ ወይም፡ በሌላው፡ በባዕዱ፡ ሥጋዊና ዓለማዊ ሰላም እንኳ መጠቀም አቅቷቸው፡ ይኸው፡ በመላው ዓለም ፊት፡ ሲሰላለፉና ሲጫጩሁ፥ ሲወነጃጀሉና ሲካሰሱ፥ ሲተናነቁና ሲተላለቁ፥ ከዚህም የተነሣ፡ **'ወለገብርሰ፡ እኩይ፥ ወሀካይ፣ አውጽእዎ፡ ውስተ ጸናፌ ጽልመት፣ ኀበ ሀሎ ብካይ፥ ወሐቅየ ስነን።"** እንደሚለው፡ እንደመለኮታዊውም ቃል፡

"«'ጨለማው ወደጸናበት ሜዳ አውጥተው እንደጣሉት፡ እንደሓኬተኛው ክፉ አገልጋይ፡ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት' በበዛበት፡ አሳዛኝና አሠቃቂ ኹኔታ፡ ሲማቅቁ ይታያሉ። (ማቴ. ፳፬፥ ፩-፲፬፤ ፳፫፥ ፲፬-፴።)

"«እንዲያውም፡ ቀድሞ፡ በኢትዮጵያ ምድር፡ በሥልጣን ላይ የቆዩት፡ የእነዚሁ፡ የሦስቱም ቤቶች ወገኖች፡ ከየሥልጣናቸው ተባርረው እንዲሰደዱና እንዲወገዱ፥ በእነርሱ ቦታ ላይ ደግሞ፡ አዲሶቹ ተተክተው፡ እነዚያን፡ ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ባለሥልጣኖች ሲያሠቃዩ የኖሩትን፡ እንዲያሠቃዩ የምታደርገው፡ ያች፡ በጽዋ አዳይነቷ፡ የማይቀረውን፡ የዳኝነቱንና የቅጣቱን ግዳጅ የምታስፈጽመው፡ መለኮታዊቷ የተፈጥሮ ሥርዓት፡ ተግባርዋን በመቀጠል እያካኼደች መኾኗን፡ ይኸው ትውልድ፡ በማስተዋል ሊመለከተው ጨርሶ እንዳልቻለ፡ እነሆ ይታያል።

"«ይህም ማለት፡ በቅድሚያ፡ 'በእግዚአብሔር ሥርዓተ-መንግሥት እየተመራሁ፡ ሕዝቡንና አገሪቱን አስተዳድራለሁ!' ይል የነበረው፡ የአጼ ኃይለ-ሥላሴ ትውልድ፡ ሊያከብረውና ሊጠብቀው በሚገባው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና ምግባሩ ላይ፡ በጨለማና በሥውር ሲፈጽም ከኖረው ክህደቱና ዓመፁ፥ ምንዝርናውም የተነሣ፡ ‹ደርግ› በተባለው፡ በይፋ፡ ‹እግዚአብሔር የለም!› በሚል፡ ባዕድና ሰይጣናዊ ፍልስፍና በሚመራ፡ ጨካኝና ግፈኛ ኃይል ከተጋለጠ በኋላ፡ ፍዳው ያመጣበትን ቅጣት፡ በዚሁ፡ በደርግ እጅ ተቀብሎ ማለፉን መዘንጋት ነው።

"«በማከታተል ደግሞ፡ ራሱ ‹ደርግ›፡ ጽዋ ፋንታው፥ ዕድል ተርታው ሲደርስ፡ እርሱም፡ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት ላይ፡ የፈጸመው ክህደት ና ዓመፅ፥ አመንዝራነቱም፡ ከቀደመው የባሰና በይፋ የተገለጸ ኾኖ ስለተገኘ፡ እርሱን በሚቀጣውና **የእግዚአብሔር ሰላም** በሌለው፡ በሌላ ተቃዋሚ ኃይል፡ ከሥልጣኑ ተባርሮ፡ እነሆ፡ እርሱም በድርሻው፡ በሠፈረበት የፍዳ ቊና እየተሠፈረበት፡ ይኸው፡ እርሱ ካፈራው ትውልድ ጋር፡ ከእርሱ በበለጠ፥ በተራቀቀና በሰላ ሠይፍ ሲመተር መገኘቱን፡ አለማጤን ነው።

"«በመጨረሻም፡ አኹን በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ፡ እንደ‹ደርግ› ኹሉ፡ የቅዱሱ ኪዳን ተቃዋሚነቱን፡ በግብር ጭምር፡ በይፋ ገልጦና አሳውቆ፡ በማናለብኝነትና በዕብሪት በሚያካኼድበት ጊዜ፡ በቀንደኞቹ፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው መሪዎች ላይ፡ በተከታታይ የደረሰው ድንገተኛ ቅሥፈት፡ መልእክቱ ምን፥ ለማንስ እንደኾነ አመዛዝኖ ለመረዳት የተሣነው መኾኑ ነው።

"«አስተዋይ ተመልካችን የሚያስገርም፡ አንድ ሌላ፡ ልዩ ነገር አለ፤ ይኸውም፡ የዛሬው፡ 'ኢትዮጵያዊ ነኝ!' የሚለው ትውልድ፡ ይህ ኹሉ የቊጣና የቅጣት መቅሠፍት የወረደበትና አኹንም፡ እየወረደበት ያለው፡ በምን ምክንያት እንደኾነ፡ ጠንቁን ሊያውቅ አለመፈለጉ፥ ወይም፡ አለመቻሉ ነው። ጠንቁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ከፈጸመው፡ ከራሱ ክህደት ፥ ዓመፅና አመንዝራነት የተነሣ መኾኑን ለመገንዘብ ቢችልም፡ በንስሓ በመመለስ ፈንታ፡ ከልጅ ወደልጅ ሲተላለፍ ከቆየው፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታዊ ውርሱ ጋር፡ እልህ ተጋብቶ፡ 'እንቢ! አሻፈረኝ!' ማለትን፡ ዐውቆና ፈልጎ መምረ ጡ ነው።

"«እንግዴህ፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** የሌለችበት ሰውነት ኾነ፣ ቤተሰብና ኅብረተሰብ፥ አገርና ዓለም፡ የህልውናው ዕድል ፈንታ፡ ይህ፡ '**ልቅሶና ጥርስ ማፏጨቱ ወደጸናበት ጨለማ ተጥሎ መሠቃየት**' መኾኑ፡ እጅግ ያስተክዛል።

"«ከዚህ ይልቅ፡ የበለጠ የሚያሳዝነው፡ 'ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ ሰላም የለም!' የሚል፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ አባል የኾነ ግለሰብ ቢኖር፡ ያ ሰው፡ ይህን የሚለው፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** በኢትዮጵያ፥ በዓለሙም ላይ ሳትኖር ቀርታ ሳይኾን፡ **በራሱ፡ በዚያ ግለሰብ ሰውነት ውስጥ ባለመኖርዋ ብቻ መኾኑን፡ ሊያውቅ አለመቻሉ እና አለመፈለጉ ነው።**

"«አዎን! የዚያ ሰው፡ *ሥጋዊውና* ነፍሳዊው፥መንፈሳዊዉም ኹለንተናው፡ በሁከት ማዕበል፡ ፈጽሞ የተጥለቀለቀውና የታወከው፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** በውስጡ እንድትኖር ካለማድረጉ፥ ወይም፡ ካለመፍቀዱ የተነሣ መኾኑን፡ ይኸው ሰው፡ ሊያውቅ አልቻለም፤ አልፈለገምም። እንዲያውም፡ ለእርሱ፡ ሰላሙን የነሣውና መከራ ሥቃዩን የሚያሳየው፡ ያ፡ በአገሩና በዓለሙ ላይ፡ ሰፍኖ ያለው፡ ሰብአዊው የአገዛዝ ኃይል፡ እርሱ ራሱ፡ በፈጣሪውና በቅድስት እናቱ ቅዱስ ኪዳን ላይ፡ በፈጸመው ክህደት ፥ ዓመፅና የአምልኮ ምንዝርና ምክንያት፡ የቅጣት ዋጋውን ሊከፍለው የተሠየመ፡ ፍርድ አስፈጻሚ መኾኑን፡ ሊገነዘብ አልቻለም።

"«በዚህ ኹሉ ጊዜ፥ ወይም፡ በእነዚህ ኹኔታዎች መነሻነት፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** በኢትዮጵያና በመላዋ ምድር ላይ፥ ወይም፡ በዚያ ግለሰብ፥ ቤተሰብና ኅብረተሰብ ውስጥ፥ አካባቢም፡ 'የለችም' ማለት አይደለም፤ **የእግዚአብሔር ሰላምማ፡ ቀድሞ፡ በፍጥረት መጀመሪያ፥ ኋላም፡ የዛሬ ኹለት ሺህ ስምንት ዓመት ከባተው [ከገባው]፡ ከመጨረሻው፡ የምሕረትና የሕይወት ዘመን ወዲህ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነት ሰፍና፡ እየተመራችና እየተጠበቀች፡ በተረጋገጠው እውንነቷ፡ ገሃድ ኾናና ገዝፋ አለች።**

"«ይህም እውነታ፡ ከላይ ቀደም ብሎ፡ በሚበቃ ተብራርቷል። ሊያያት፥ ሊያገኛትና ሊጠቀምባት ያልቻለው እኮ፡ እስካኹን ተዘፍቆ ከሚማቅቅበት፡ የክህደት ፥ የዓመፅና የምንዝርና ኃጢአቱ፡ 'በእውነተኛ ንስሓ አልመለስም!' ብሎ፡ ልቡናውን ያደነደነው፡ ይኼ፡ የዛሬው፡ 'ኢትዮጵያዊ ነኝ!' የሚለው ትውልድ ነው።

"«እውነተኞቹና ታማኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ልጆችማ፡ በውስጣቸውም፥ በውጫቸውም፥ በመካከላቸውና ባካባቢያቸው፥ በቤተሰባቸውና በኅብረተሰባቸው፥ በአገራቸውና በዓለሙም ዘንድ፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** ሰፍና፡ እነሆ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ጥበቃና ምግብና፣ አመራርና አስተዳደር፡ እየኖሩባት ስለሚገኙ፡ ለእግዚአብሔርና ለቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ ምስጋናቸውን፡ ያለማቋረጥ ከማቅረብ፥ ለዚህ ጸጋ ላልታደሉት ወገኖቻቸውና ለመላው ፍጥረተ-ዓለምም፡ ከመጸለይ በቀር፡ ከፈጣሪያቸው፡ የጎደለባቸው፡ አንዳችም ነገር፡ ከቶ የለም።

"«**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር** *መንግሥትም፡* እንደሰዎች ድርጊት ሳይኾን፡ የቃል ኪዳን ፈጣሪዋና አምላኳ፡ እንደሠራትና የቅዱሱ ኪዳን ታማኞች ልጆቿ፡ ጸንተው በቆሙላት ይዞታዋ፡ ይኸው፡ የማይገሠሥ ማንነቷንና ስሟን እንደጠበቀች፡ ካልተከፋፈሉትና ካልተለያዩት፡ ሕዝቧና ምድርዋ ጋር፡ በ**እግዚአብሔር ሰላም** ተጠብቃ ትገኛለች።

"«አዎን! በማስመሰል፡ 'ኢትዮጵያዊ ነኝ!' የሚለው፡ ይህ፡ ከሃዲውና ዓመፀኛው፥ አመንዛሪውና ክፉው ትውልድ፡ እንደፍላጎቱ፡ በሥልጣን ላይ ያስቀመጠው አገዛዝ፡ በታጠቀው የተግሣፅና የፍዳ ሠይፍ፡ ቀጥቶና አስተምሮ፡ ወደ ንስሓ እስኪመልሰው ድረስ፡ እርሷ፡ 'ኢትዮጵያ'፡ ይኸው፡ በነጻነት ህልውናዋና በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፡ መለኮታዊ አመራርዋንና አስተዳደርዋን፡ በበላይነትና በተጠናከረ ይዘት ቀጥላበታለች።

<u>"«ይህም ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ ባለፉት የቅርቦቹ ዓመታት፡ ለመላው ዓለም፡ ይፋ ባወጣቻቸው ዐዋጆቿ አማካይነት፡ እውን ኾኖ ታይቷል፤ እየታየም ነው።</u>

"«ይህች፡ የእኛ ኢትዮጵያ፡ ራሷ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ስለኾነች፡ በምድር ላይ፡ ዳር ድንበር ሳይከልላትና የሚወስናት ጽንፍ ሳይኖር፡ ይኸው፡ በሰማያት ሳይቀር፡ በመላው ፍጥረታተ ዓለማት ዘንድ ታውቃ፥ በመላእክትና በሕዝቦችም ልቦና ውስጥ፡ በሃይማኖት ተመሥርታ፡ በእውነትና በመንፈስ ከሚመለከው መለኮታዊ ልጇ ወዳጇ፡ ኢየሱስ መሲሕ ጋር፡ በእግዚአብሔር አብ፡ መፅምርትነቷ [ሙሽርነቷ]፥ በእግዚአብሔር ወልድ፡ እናትነቷና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መንበረ ጸባዖትነቷ፥ በእግዚአብሔር መንግሥትነቷም ሰፍና፡ እነሆ፡ ስትወደስና ስትመሰገን ትኖራለች።

"«እንዲህ እንደመኾኗ፡ በዛሬው የመጨረሻ ዘመን፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ ለአልጫው ዓለም፡ ጨው፥ ለጨለማውም ዓለም፡ መብራት ኾነው፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ በመላው ዓለም፡ አብዝተውና አስፋፍተው፡ ይዘሩትና ይናኙት ዘንድ፡ ይኸው፡ በምድር ላይ፡ ባሉ አገሮች ኹሉ፡ ተሠራጭተው እንዲኖሩ አሰማርታቸዋለች።

"«በዚህም ረቂቅ ምግባርዋ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፡ በፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ፡ የሰፈነ መኾኑ፡ በብዙዎች ዘንድ እንዲከሠትና እንዲታወቅ የማድረጓን ኺደት ፡ በበለጠ ቀጥላበት ትገኛለች።

"«ይህ ኹኔታ፡ ስለ**እግዚአብሔር ሰላም፡** እስካኹን ለተገለጠው እውነታ፡ ግዙፍ ማረጋገጫ መኾኑን ለመገንዘብ ደግሞ፡ ለማንኛውም እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው፡ የሚሳነው አይኾንም።»"

## በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ የሰላም ምንነትና ማንነት።

"**የእግዚአብሔር ሰላም**፡ እውነተኛ ምንነትና ማንነት እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! በፍጡሮቻችን ሰዎች ዘንድ፥ በተለይም፡ 'ክርስቲያን ነን!' በምትሉት ወገኖች ዘንድ፥ ይልቁንም፡ 'የኢትዮጵያ ልጆች' ተብላችሁ፡ በተቀደሰው ስሜ በተጠራችሁት፡ በእናንተ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ሳይቀር፡ በዚችው በ**እግዚአብሔር ሰላም** ስም፡ ሲፈጸም የተኖረውና አኹንም፡ ሲካኼድ የሚታየው **ተፃራሪ ድርጊት፥ ይኸውም፡ "ጦርነት" የተባለው ጠንቀኛ ጠላት፡** ከወዴት፥ እንዴትስ መጣ?

"ለዚህ ከባድና አሳሳቢ ጥያቄ፡ ትክክለኛውንና እውነተኛውን መልስ መስጠት፡ እጅግ አስፈላጊና ተገቢ ከኾነበት የመጨረሻው ወሳኝ ዘመን ተደርሷል። የዚሁ ጥያቄ፡ አቅራቢዎቹም፥ መላሾቹም፥ ምስክሮቹና ዳኞቹም፡ እናንተው፡ እየራሳችሁ ናችሁ።

"እናንት ልጆቼ! እናንት ፍጡሮቻችን ሰዎችም ኹሉ!

"ከዚህ ቀጥሎ ለማሰማችሁ የዐዋጅ ቃሌ፡ መነሻ ይኾነኝ ዘንድ፡ ባለፈው፡ በ፲ኛው መለኮታዊ ቃለ-ዐዋድ፡ ለእናንተ ከነገርኋችሁ መካከል፡ በጥቂቱ ጠቅሼ ላስታውሳችሁ ነውና፡ እስኪ፡ እርሱን፡ እንደገና፡ በጽሙና አዳምጡት! በማስተዋልም፡ ተመልከቱት!

"ያም፡ እኛ እግዚአብሔራችሁ፡ በቅድሚያ፡ ይህችን ፍጥረተ-ዓለም፡ እንዲህ፡ አሟልተንና አከናውነን ካዘጋጀንላችሁ በኋላ፡ ለእናንተ፡ ከመልካችን አንሥቶ፡ የእኛ የኾነውን ኹሉ በመስጠት፡ እናንተን ፈጥረናችሁና ወልደናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ፡ በየግላችሁ፥ በኅብረተሰብነትም፡ ኹላችሁ፡ እርሷን፡ ይህችኑ ፍጥረተ-ዓለም፡ በዐፅመ-ርስትነት ወርሳችኋት፡ በፍጹም ተድላና ደስታ፥ በፍቅርና በሰላም፡ ተስማምታችሁና ተባብራችሁ፥ ለዘለዓለምም፡ ሕያዋን ኾናችሁ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ባለቤትነትና ሥርዓት፡ ከእኛ ጋር፡ በክብርና በምስጋና፡** ትኖሩባትና ትገለገሉባት፥ ታስተዳድሯትና ትዝናኑባት፥ ትጠብቋትና ትቈጣጠሩዋት ዘንድ፡ የተለገሠቻችሁ መኾኑን የሚያረጋግጠው፡ እንዲህ የሚለው ምዕዳኔ ነው፡-

"«አዎን! እኛ፡ እናንተን፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች፡ በመልካችን የፈጠርናችሁና ከእኛ፡ ከመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፡ እንደአንዳችን ለመኾን የበቃችሁበትን፥ የገናናው ክብራችን ተሳታፊዎች ትኾኑ ዘንድ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም አማካይነት፡ የምንነት አካላችንን አጐናጽፈንና የማንነት ባሕርያችንን አቀዳጅተን፡ በአርአያችን ያስገኘናችሁ ነን። እናንተም፡ በእኛና ከእኛ፤ ለእኛም፡ እንዲህ የተገኛችሁ ናችሁ።

"«ጥንቱኑ፡ በዚህ ኹኔታ የፈጠርናችሁ እኛ፡ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፡ የቀድሞዎቹም ኾኑ የኋለኞቹ ወገኖቻችሁ፤ እናንተ ጭምር፡ ያማሰናችሁትን [ያበላሻችሁትን] እና ያቃወሳችሁትን፥ ያጣመማችሁትንና ያጠፋችሁትን፥ ያሳደፋችሁትንና ያረከሳችሁትን ኹሉ፡ ማንነታችሁንና ምንነታችሁን ሳይቀር፡ እኔ፡ እግዝእተብሔር እም፡ በድንግል ማርያም የትስብእት ምሥዋዓ-መድኃኒትነቴ፤ እኔ፡ እግዚአብሔር ወልድም፡ በኢየሱስ መሲሕ የትስብእት መስቀለ-ሰላም ቤዛነቴ፡ አድሰንና አስተካክለን፥ አቃንተንና አልምተን፥ አንጽተንና ቀድሰን፡ ይኸው፡ ወደቀደመው ድንግል አካልነቱና ንጽሓ ባሕርይነቱ መለስነው!

"**«እኛ፡ እናንተን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችንን፡ እንዲህ አድርገን፡ ለእኔነትና ለእኛነት ያበቃናችሁ እኮ፡ በዘለዓለማዊነት በሠራነው ዓለም፡ እኛን መስላችሁ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት፡ በፍጹሙ መልካም ሕይወት እንድትኖሩ እንጂ፡ ከሥጋዊው አእምሮአችሁ ከፈለቀው፡ ከዚህ የተሳሳተ እምነታችሁና ክፉ አስተሳሰባችሁ የተነሣ፡ ይኸው አኹን እንደምታዩት፡ ፍጻሜው፡ "ሞትና ዕልቂት" ለኾነው ህልውና፡ እየራሳችሁን እንድታዋርዱና እንድትዳርጉ አልነበረም፤ አይደለምም።»**

"እንግዲህ፡ '**ሣህል ወርትዕ ተራከባ! ጽድቅ ወሰላም ተሰዓማ!**

"'ቸርነት እና ቅንነት ተገናኙ! እውነት እና ሰላም ተሳሳሙ!' ብለን፡ ቀደም አድርገን፡ ከነቢያታችን፡ በአንዱ እንዳሰማነው ኹሉ፡ ለእናንተ ተብሎ የተዘጋጀው፡ ይህ ፍጥረተ-ዓለም፥ እናንተም **የተፈጠራችሁት**፡ እንዲህ፡ የእግዚአብሔር፥ በእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር በኾነችው **እውነት** እና ከእርሷ በተገኘችው **ሰላም** ተመሥርታ በምትካኼደው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት፡ እኛን መስላችሁ፡ በፍጹሙ መልካም ሕይወት እንድትኖሩ** ብቻ ነው።

"እውነታው ይህ ኾኖ ሳለ፡ ታዲያ! ከዚህ፡ ከመልካሙ ሕይወት፥ ከዚህ፡ ዘለዓለማዊ ቅዱስ ዓላማና ግብ፡ ፈጽሞ በተለየው፥ እንዲያውም፡ ተፃራሪና ሰይጣናዊ በኾነው፡ "**ጦርነት**" በሚባለው፡ የጭከናና የግድያ ክፉ ግብር ተማርካችሁ ልትዘፈቁበት እንዴት ቻላችሁ? ጥንቱኑስ፡ ይህንኑ፡ "**ጦርነት**" የተባለውን፡ አንድስ የኾነ ጉድ፡ ማን አመጣው? እንዴትና ከየትስ ተገኘ?

"የዚህ፣ በተለይም፡ "**ጦርነትን፡** ማን አመጣው?" የሚለው ጥያቄ መልስ፣ በግልጽ የታወቀ ስለኾነ፡ በአጭር ቃል፡ ሊሰጥ የሚቻል ነው፤ ይኸውም፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለተቃዋሚዎቹና ሰቅለው ለገደሉት አይሁድ፡ '**አንትሙሰ፡ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ፤ ወፍትወቶ ለአቡክሙ ትፈቅዱ ትግበሩ። ወውእቱሰ ቀታሌ ነፍሰ ሰብእ ውእቱ እምትካት፤ ወኢይቀውም በጽድቅ፤ እስመ አልቦ ጽድቅ በኀቤሁ፤ ወሶበሂ ይነብብ ሓሰተ፡ እምዚአሁ ይነብብ፤ እስመ ሓሳዊ ውእቱ፤ ወአቡሃ ለሓሰት።**

"'እናንተማ፡ ከአባታችሁ፡ ከሰይጣን ናችሁ፤ የአባታችሁን ፈቃድ ልትፈጽሙ ትወድዳላችሁ። እርሱም፡ ከጥንት፡ የሰው ነፍስ፡ ገዳይ ነው፤ እውነት በእርሱ ዘንድ ስለሌለች፡ ለእውነት አይቆምም። ሓሰትን ሲናገር፡ ከራሱ ይናገራልና፤ ሓሰተኛ፥ የሓሰት አባትም ነውና።' ብሎ እንደተናገረው፡ የጦርነትን ፅንሰ-ሓሳብ፥ ተገብሮውንም፡ ሌላ ማን ያመጣዋል? ይኸው፡ 'ሰይጣን' የተባለው ዲያብሎስ ነው እንጂ።(ዮሓ. ፰፥ ፵፬።)

"ይኸው፡ ሓሳዊ የኾነው፡ የጦርነት ፅንሰ-ሓሳብ፥ አድራጎቱም፡ 'እንዴትና ከየትስ ተገኘ?' ለሚለው፡ ተጓዳኝ ጥያቄ ደግሞ፡ መልሱ፡ ይኸው፡ "ሰይጣን" የተባለው ዲያብሎስ፡ ራሱ ቀስቅሶ ስላመጣው፡ የ'ጦርነት' ጠንቀኛ ሥሪት፡ ከዚህ በሚከተለው የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅስ ውስጥ የተጻፈው ማብራሪያ፡ እንዲህ ይላል፡-

"'**ወፀብእዎ በሰማይ፡ ለውእቱ አርዌ፤ ሚካኤል፥ ወመላእክቲሁ፤ ወተፃብእሙ ውእቱ አርዌ፡ ምስለ መላእክቲሁ። ወስእኖሙ፤ ወኢረከበ እንከ፡ መካነ፡ በውስተ ሰማይ። ወወድቀ ውስተ ምድር፡ ውእቱ አርዌ ዐቢይ፤ ...ወበዘነቡ ይስሕብ ሣልስተ እዴሆሙ ለከዋክብተ-ሰማይ፤ ወያወርዶሙ ውስተ ምድር፤ ወአርዌሰ፡ ዐቢይ ውእቱ ቀዲሙ፣ ዘአስሓቶ ለኵሉ ዓለም፥ ዘስሙ፡ ‹ሰይጣን›። ወወድቀ ውስተ ምድር፤ ወመላእክቲሁኒ፡ ወድቁ ምስሌሁ፡ ውስተ ምድር።**

"'**...አሌ ላ ለምድር፥ ወለባሕር! እስመ ወረደ ሰይጣን ውስቴቶሙ፡ ምስለ ዐቢይ ሕምዙ፤ እስመ የአምር፡ ከመ ውኁድ መዋዕል ተርፎ።**

'''*ወሶበ ርእየ ዝክቱ አርዌ፡ ከመ ወድቀ ውስተ ምድር፡ ...ወቆመ ...አንጻረ ይእቲ ብእሲት፡ ...እንተ ትለብስ ፀሓየ ወወርኀ ታሕተ እገሪሃ፤ ወዲበ ርእሳኒ፡ አክሊል፣ ዘዐሠርቱ፥ ወክልኤቱ ከዋክብት፡ ...ከመ ሶበ ወለደት ፡ ይብላዕ ሕፃና። ወወለደት፡ ወልደ ተባዕተ፤ ዘውእቱ ይርዕዮሙ ለኵሉ አሕዛብ፡ በበትረ ሓጺን። ወመሰጥዎ ለውእቱ ሕፃን፤ ወወሰድዎ ኀበ እግዚአብሔር፤ ወኀበ መንበሩ።*

'''*ወጐየት ይእቲ ብእሲት፡ ውስተ ገዳም፣ ወውስተ መካን፡ዘአስተዳለወ ላቲ እግዚአብሔር፡ ከመ ትትዐቀብ በህየ፥ በኵሉ መዋዕል፣ ዐሠርተ፥ ወክልኤተ ምእተ፥ ወተስዓ ዕለተ። ...ዴገና፡ ...ውእቱ አርዌ፡ ለእንታክቲ ብእሲት፡ እንተ ወለደት ሕፃነ ተባዕተ።*

'''*ወተውህባ ለይእቲ ብእሲት፡ ክልኤ ክንፍ፡ ከመ ዘዐቢይ ንስር፣ ከመ ትሥርር ውስተ ገዳም፥ ወውስተ መካን፡ ኀበ ትትዐቀብ በኵሉ መዋዕል፡ ዘመነ፥ ወአዝማነ፥ ወመንፈቀ ዘመን፡ እምቅድመ ገጹ፡ ለውእቱ አርዌ። ወሠረረ፤ ወዴገና ውእቱ አርዌ። ወአውፅአ እምነ አፉሁ፡ ውእቱ አርዌ፡ ማየ ብዙኀ እንተ ድኅሬሃ፡ ለይእቲ ብእሲት፡ ከመ ፈለግ ዐቢይ፡ ከመ ይንሥአ ውኂዙ። ወረድአታ ምድር፡ ለይእቲ ብእሲት፤ ወአርኀወት አፉሃ ምድር፤ ወሰረበቶ፡ ለውእቱ ውኂዝ፡ ዘአውኀዘ ውእቱ አርዌ፡ እምነ አፉሁ። ወኢያእመረ፡ ከመ ተውህበ ላቲ፡ ክንፍ።*

'''*ወተምዐ ውእቱ አርዌ፡ ላዕለ ይእቲ ብእሲት። ወሖረ ይፅብአሙ፡ ለእለ ተርፉ ውሉዳ፤ ወለእለ የዐቅቡ ትእዛዘ እግዚአብሔር፤ ወይሄልዉ በጽድቁ ለኢየሱስ ክርስቶስ። ወቆመ ውእቱ አርዌ፡ ላዕለ ኆጻ ባሕር።*

'''በሰማይ፡ ሚካኤል፡ ከመላእክቱ ጋራ ኾኖ፡ አውሬውን [ዲያብሎስን] ተዋጋው፤ አውሬውም፡ መላእክቱን ይዞ፡ ተዋጋቸው። አልቻሏቸውምም። ከዚያ ወዲያም፡ ይኸው ታላቁ አውሬ፡ በሰማይ፡ ሥፍራ ስላላገኘ፡ ወደምድር ወደቀ። ...ጅራቱም፡ የሰማይ ከዋክብትን ሲሶ እየሳበ፡ ወደምድር አወረዳቸው! ወደምድር የወደቀው፥ [ሰይጣናት] መላእክቱም፡ ዐብረውት፡ ወደምድር የወደቁት፡ ይኸው አውሬ፡ ‹ሰይጣን› የተባለው፥ ዓለሙንም ኹሉ ያሳተው፡ የቀደመው፡ ታላቁ እባብ ነው።

'''...ለምድርና ለባሕር፡ ወዮላቸው! ሰይጣን [ዲያብሎስ]፡ የቀረው የአገዛዝ ዘመኑ፡ አጭር መኾኑን ዐውቆ፡ ከታላቁ የክፋት መርዙ ጋር፡ ወደእነርሱ ውስጥ ወርዷልና።

'''*ይኸው አውሬ፡ ተዋርዶ፡ በምድር ላይ መውደቁን ሲያይ፡ ...ፀሓይን ተጐናጽፋ፥ ጨረቃም፡ ለእግሮቿ፡ ብርኵማ ኾኖላት፥ በራሷ ላይ፡ የዓሥራ ኹለት ከዋክብት ዘውድን የተቀዳጀች፡ አንዲት፡ ልትወልድ ያላት ሴት [ኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም]፡ በምትወልድበት ጊዜ፡ ሕፃኗን [ኢየሱስ መሲሕን] ሊበላ፡ ከፊት ለፊቷ ቆመ። እርሷም፡ አሕዛብን ኹሉ፡ በብረት በትር፡ ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ወንድ ልጅ ወለደች። ይህም ሕፃን፡ ወደሰማይ ተነጠቀ፤ ወደእግዚአብሔር፥ ወደዙፋኑም ተወሰደ።*

"'ሴቲቱም፡ እግዚአብሔር፡ ሺህ ከኹለት መቶ ዘጠና ለሚኾነው፡ ለዚያ ጊዜና በዚያ ሥፍራ ተጠብቃ እንድትቆይበት የሚያስፈልጋትን ኹሉ ወዳሰናዳላት በረሀ ሸሸች። አውሬውም፡ ወንድ የኾነውን ሕፃን ልጅ የወለደችውን፡ ይህችኑ ሴት አሳደዳት።

"'ሴቲቱም፡ አንድ ዘመንና ዘመናት፥ የዘመን እኩሌታም በኾነው፡ በዚህ ጊዜ ኹሉ፡ ከዚሁ አውሬ ፊት ርቃ፡ ወደምትጠበቅበት፡ ወደዚያ የበረሀ ሥፍራ ትበርር ዘንድ፡ የታላቅ ንስርን የሚያህሉ፡ ኹለት ክንፎች ተሰጧት። አውሬውም በረረ፤ አሳደዳትም። ሴቲቱ፡ በታላቅ የወንዝ ውኃ እንድትወሰድ ሊያደርግ፡ ይኸው አውሬ፡ ከአፉ፡ ብዙ ውኃን አውጥቶ፡ ከሴቲቱ በስተኋላ አፈሰሰ። ምድሪቱ ግን፡ሴቲቱን ረዳቻት፤ ለሴቲቱ፡ ክንፍ እንደተሰጣት ያላወቀው አውሬ፡ ከአፉ ያፈሰሰውን፡ ያን ውኃ፡ ምድሪቱ፡ አፏን ከፍታ ዋጠችው።

"'አውሬውም [ዲያብሎስ]፡ በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ፡ የቀሩትን ልጆቿን፥ የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ የሚጠብቁትን፥ በኢየሱስ መሲሕ እውነት የሚኖሩትንም [በቅዱሱ ኪዳን፡ 'የኢትዮጵያን ልጆች' የኾኑትን] ሊዋጋ፡ ኼደ።

"'ይኸው አውሬ፡ [ከሓሰት አባትነቱ የተነሣ፡ ብዛት ካላቸው፡ ከርኵሳን መናፍስት ሠራዊቱና ከተከታዮቹ የሰው ወገኖች ጋር፡ የማይቀረውን የዘለዓለም ውድቀቱን አረጋግጦ ሊያሳይ] በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ።" (ራእ. ፲፪፥ ፩-፲፯።)

"ስለዚህ፡ ይኸው፡ በምድር ላይ፡ በሰዎች መካከል እየተካኼደ ያለው ጦርነት፡ ፅንሰ-ሓሳቡ፥ ድርጊቱም የተገኘው፡ ከዚሁ፡ ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ ሰይጣናት መኾኑን፡ ይህ፡ የባለአደራው ልጇ፡ የዮሓንስ ራእይ መጽሓፋዊ ጥቅስ፡ በሚበቃ ያስረዳችኋል።

"ይኹን እንጂ፡ ይህን፡ የጦርነት ዝክረ-ነገር በሚመለከት፡ ያለውንና የኾነውን መለኮታዊ ምስጢር፡ እናንተ ኹላችሁ፡ እስካኹን፡ በሃይማኖታችሁ አማካይነት፡ ልታውቁትና ይህንኑ ዕውቀታችሁን፡ በምግባር ላይ ዐውላችሁት፡ ለመልካሙ የሰላም ፍሬ ልታበቁት ይገባችሁ የነበረ ሲኾን፡ ነገር ግን፡ በእናንተ በኩል፡ የኾነውና እየኾነ ያለው፡ የዚያ ተቃራኒው ኾኖ በመገኘቱ፡ እኔ፡ አኹን፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ ራሴ፡ ገልጬ እነግራችሁ ዘንድ፡ አስፈላጊ ኾኗል።

"የምነግራችሁም፡ ይህ ነውና፡- ሰምታችሁ ፈጽሙት! ቀድሞ፡ በእግዝእተብሔር እም'ነቴ [እናትነቴ]፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ በመለኮትነት የወለድሁት፡ ልጇ ወዳጇ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኋላ በመጨረሻ ደግሞ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ግብር፡ በዚሁ፡ በእግዝእተብሔር እም'ነቴ ከተዋሓድኋት፡ ከእኔዪቱ፡ ኢትዮጵያዋ እናቱ፡ ከድንግል ማርያም፡ በሰውነት የወለድሁትና 'ኢየሱስ መሲሕ' ተብሎ፡ በምድር ላይ የተገለጠው፡ ለምን ይመስላችኋል?

"በዚህ ረገድ፡ እናንተ ኹላችሁ፡ በተለይም፡ 'ክርስቲያን ነን!' የምትሉት፡ በየሃይማኖታችሁ፡ በግልጽ የተነገረና የተጻፈ በመኾኑ፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደዚህ ዓለም፡ በሰውነት፡ የመጣበትን ምክንያትና ዓላማ፡ የምታውቁት ኾኖ ሣለ፡ ነገር ግን፡ ዐውቃችሁት፡ ልትከተሉትና ልትጠቀሙበት ስላልፈለጋችሁት ብቻ፡ ያ ምክንያትና ዓላማ፡ በእውነተኛው ትክክለኛ መልኩና ይዘቱ፡ በምግባር ላይ ባለመዋሉ፡ መልካሙን ውጤት ሳያስገኝ መቅረቱ፡ ይኸው እንደሚታየው፡ እርግጥ ነው።

"እንግዴህ፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደዚህ ዓለም፡ በሰውነት፡ የመጣበት፡ አንዱ፡ ታላቁ ምክንያትና ዓላማ እኮ፡ ይኸው፡ የሓሰቱና የክፋቱ፥ የጥፋቱና የጦሩ አባትና አበጋዝ የኾነው ዲያብሎስ፡ በሰማይ ፈጥሮትና ሠርቶበት፥ ነገር ግን፡ በፍጻሜው፡ ድል ተነሥቶ፡ ከነሠራዊቱ ሰይጣናት ጋር፡ ወደምድር የተጣለበትንና ይዞት የመጣውን፡ ይህንኑ፡ 'ጦርነቱ'ን፡ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ ከመላው ምድረ-ገጽ ለማስወገድ መኾኑ፡ በመጨረሻው ድሉ፡ እውን ኾኗል።

"ይኸውም፡ ይኸው፡ አውሬው ዲያብሎስ፡ ፍጡሮቻችን የኾኑትን፡ የሰው ወገኖች፡ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት፡ እርስ በርሳቸው ሲያጣላና ሲያፋጅ፥ ሲያስተናንቅና ደም ሲያፋስስ፥ ሲያጋድልና ሲያስተላልቅ የኖረበትን፥ ማብቂያ ያልተገኘለትንም፡ ይህንኑ ጦርነት፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀለ-ሰላም፡ የድል ሞቱ ያስወገደው፡ መኾኑ ነው።

"እነዚህ፡ ፍጡሮቻችን የኾኑት፡ የሰው ወገኖችም፡ በዚችው ምድራችን ላይ፡ ከሚርመሰመሱት መካከል፡ ከእየራሳቸው የክፋት እምነታቸውና የጥፋት ግብራቸው የተነሣ፡ በሥነ-ፍጥረት የቍጣ መቅሠፍቶች ድምሳሴ፡ ተርፈው የቀሩት ናቸው። ይህን እውነታም፡ ቀደም ብዬ ከጠቀስሁላችሁ፡ የመጽሓፍ ጥቅስ ጋር፡ የራሳችሁ የታሪክ ድርሳናትም ያረጋግጡታል።

"አዎን! ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደዚች ምድር፡ በሰውነት የመጣው፡ በዚሁ፡ በክፉው አውሬ በተመሰለው፡ በዲያብሎስና በሠራዊቱ ሰይጣናት ተፃራሪነት፡ በሰማይ ተነሥቶ የነበረውን ታላቅ ጦርነት፡ በቅዱሳን መላእክቱ አማካይነት ያስገኘውን ድል፡ በምድርም ሊፈጽም መኾኑን፡ ልታውቁት ይገባል። ልጄ ወዳጄ፡ በሰማይ፡ ያስገኘው ድል በተፈጸመ ጊዜ፡ የኾነውና የተደረገው፡ በዚሁ፡ በራእየ ዮሓንስ መጽሓፍ የተከተበውን ዜና መዋዕል ታስታውሳላችሁ። እንዲህ የሚል ስለኾነ፡ እንደገና ስሙት!

**"'ወሰማዕኩ ቃለ ዐቢየ፡ በውስተ ሰማይ፡ ዘይብል፦ ‹ኮነት መድኃኒት፥ ወኀይል፥ ወመንግሥት፡ ለአምላክነ! ወሥልጣን ለመሲሑ! እስመ ወድቀ መስተዋድይ፡ ዘአስተዋደዮሙ ለአበዊነ፡ ቅድመ እግዚአብሔር፡ መዐልተ፥ ወሌሊተ።› ወሞእዎ እሙንቱ፡ በእንተ ደመ በግዑ፥ ወበእንተ ቃለ ጽድቆሙ፤ እስመ ኢያብደሩ ነፍሶሙ፡ እስከ ለሞት። ወበእንቲአሆሙ፡ ተፈሥሑ ሰማያት፤ ወእለ ይነብሩ ውስቴቶን።**

"'ታላቅ ቃልም፡ በሰማይ ሰማሁ፤ እንዲህ ሲል፡- ‹አኹን፡ ማዳንና ኃይል፥ መንግሥትም፡ ለአምላካችን፥ ሥልጣንም፡ ለመሲሑ ኾነ! በእግዚአብሔር ፊት፡ ቀንና ሌሊት፡ ከሣሽ የኾነው፥ የአባቶቻችን ባለጋራቸው፡ ወድቋልና።› እነርሱም፡ ከበጉ ደም የተነሣ፥ ከእውነት ቃሎቻቸውም የተነሣ፡ ድል ነሡት፤ ነፍሳቸውንም፡ እስከሞት ድረስ እንኳ፡ አልወደዱም። ስለእነርሱም፡ ሰማያት፥ በውስጣቸውም የሚኖሩት ኹሉ፡ ደስ አላቸው።' (ራእ. ፲፪፥ ፲-፲፪።)

"ዛሬም፡ እናንተ፡ በቅዱሱ ኪዳን ልጆቼ የኾናችሁት፡ በምድር ላይ ተሠራጭታችሁ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፥ እናንተንም መስለው፡ በያሉበት የሚያመልኩን ፍጡሮቻችንም ኹሉ! ይህን በመሰለው ደስታና ሓሤት ተመልታችሁ የምትኖሩ አይደላችሁምን? አዎን! ናችሁ እንጂ።

"ይህን በመሰለው ደስታና ሓሤት ተመልታችሁ የምትኖሩትም፡ ያለ ምክንያት አይደለም። ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የዛሬ ኹለት ሽህ ስምንት ዓመት፡ የዚሁ፡ የዝንተ ዓለሙ ጦርነት ወሳኝ በኾነው፡ በመስቀሉ የሰልፍ ሜዳ ላይ፡ ተዋጊ ጠላቱና ጦር መሪው በኾነው በዲያብሎስ ትእዛዝ፡ ዕርቃነ ሥጋውን ኾኖ፡ እጆቹና እግሮቹ፡ በአራቱ ማዕዘናተ ዓለም፡ ተዘርግተውና ተወጥረው፥ በብረት ችንካርም ተቸንክረው፥ ጎኑን፡ በጦር ተወግቶ፥ በራሱም ላይ፡ የእሾህ አክሊልን ደፍቶ፡ በቆረሰው ቅዱስ ሥጋውና ባፈሰሰው ክቡር ደሙ፡ ሞቶና ተገንዞ፥ ተቀብሮና መበስበስን አጥፍቶ በመነሣቱ ነው።

"ያን፡ አውሬው ዲያብሎስ፡ በሰማይ፡ በቅዱሳን መላእክት ላይ፥ በምድርም፣ በእናንተና በፍጡራን ሰዎቻችን ላይ ሲያካኼድ የኖረውን ጦርነት፡ በመከላከያ ጋሻና በግድያ መሣሪያ ተቋቁሞና ተዋግቶ ሳይኾን፡ **'አባ ስረይ ሎሙ! እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ!**

"'አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና፡ ይቅር በላቸው!' በሚል በርኅራኄና በይቅርታ፥ በምሕረትና በፍቅር የሰላም ቃል ብቻ፡ የራሱን የሰውነት አካል፡ ለዕርድ እንደቀረበ፡ እንደበግ ጠቦት አመቻችቶ በመስጠት፡ በቤዛነት ታርዶና ተሠውቶ፡ የዘር ጠላቱን፡ ዲያብሎስን፡ በድል አድራጊነት፡ እንዴት ቀጥቅጦ ኃይሉን እንዳሳጣው፥ **ጦርነትንም፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ለዘለዓለም፡ እንዴት እንዳስወገደው፤ ሰላሙንም፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ እንደምን እንደመለሰ**፡ በገሃድ፡ በማሳየቱ፥ በይፋም፡ በማሳወቁ ነው። (ሉቃ. ፳፫፥ ፴፬።)

"ታዲያ! ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዲህ አድርጎ፡ በታላቁ ዘለዓለማዊ ድል ያጠናቀቀውንና ያስወገደውን 'ጦርነት'፡ ዛሬ፡ እናንተ፡ እንዲህ በሰፋና በተራቀቀ ዘዴ፡ እያደገና እያሠቀቀ እንዲኼድ ያደረጋችሁት፡ እናንተው፡ የክፉው ወገኖች የኾናችሁት፡ ልበ-ደንዳኖቹ ሰብአውያን ፍጡሮቻችን፥ በተለይም፡ እናንተ፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ፡ እየራሳችሁን፡ 'ክርስቲያን ነን!' የምትሉ ግብዞች ወገኖች አይደላችሁምን? አዎን! በእርግጥ ናችሁ።

"ይህንም ድርጊት፡ በድፍረትና በማናለብኝነት የምትፈጽሙት፡ የእኛን የፈጣሪያችሁን፡ የሰላም መንገድንና የመልካም ሕይወት መመሪያ ሥርዓትን፡ በክርስቲያንነታችሁ ተቀብላችሁ ከመከተል ይልቅ፡ የእርሱን፡ የዲያብሎስን የክፋት ፈለግና ክፉ ምክሩን ተቀብሎ የመፈጸም ዝንባሌ ስላላችሁ ብቻ ነው።

"ለዚህና በዚህ ረገድ፡ ባለፉት ዘመናት፡ በእርግጥ ሲፈጸም ለተኖረው፥ አኹንም እየተፈጸመ ላለው እውነታ ማረጋገጫ ይኾኑ ዘንድ፡ ሊቀ ርቡ ከሚችሉ አያሌ ማስረጃዎች መካከል፡ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ፡ በይፋ የታወቁትንና በታሪክ የተመዘገቡትን፡ ኹለቱን ብቻ፡ እዚህ ላይ እጠቅስላችኋለሁ።

"እነዚህም፡ በእናንተ፡ የካቶሊካዊት ቤተ-ክርስቲያን መሪዎችና አባሎች በኾናችሁት መነኰሳትና አማኞች፥ እንዲሁም፡ በአውሮጳ ክፍለ-ዓለም በምትኖሩ፡ "ክርስቲያን ነን!" በምትሉ፡ የፀረ-ማርያም ወገኖች ዘንድ፡ ከ፲፩ኛው እስከ ፲፭ኛው ምእተ ዓመታተ-ምሕረት ድረስ፡ ለአራት መቶ ዓመታት ያህል የተካኼደውን፡ በአንድ በኩል፡ ውሳጣዊዉን የእርስ በርስ ዕልቂት በሚመለከት፡ "የኑፋቄ ምርምር" [Inquisition] የተባለውን፥ በሌላ በኩል ደግሞ፡ አፍአዊዉን የባዕዳን ፍጅት በሚመለከት፡ "የመስቀል ጦርነት" [Crusade] የተባለውን፡ የሚያካትቱት፡ ኢክርስቲያናዊ የግፍና የጭካኔ ድርጊቶቻችሁ ናቸው።

"'ልጆቼ! ሕዝቤ! ፍጡሮቼ!' የምላችሁ፡ እናንተ፡ የምታዳምጡኝ፡ ወንዶችና ሴቶች! እንግዴህ ተመልከቱት! በአረማውያንና በአሕዛብ ዘንድ እንኳ የማይደረገው፡ ይህን የመሰለው ድርጊት፡ 'ክርስቲያን ነን!' በምትሉ ወገኖች ዘንድ፡ መታሰቡና መወጠኑ፥ መካኼዱና መፈጸሙም፡ ለእየራሳችሁ፡ አያስደንቃችሁምን? አያስገርማችሁምንስ? ከዚያም አልፎ፡ አያሳዝናችሁምን? ይኼ ድርጊት እኮ፡ ዛሬም፡ በእናንተ፡ የእነዚሁ ወገኖች በኾናችሁት፡ በእናንተ ጭምር፡ እየተካኼደና እየተፈጸመ ይገኛል። ታዲያ! ይኼ ኹሉ፡ በመላው ዓለም፡ በያለበት፡ በተለያየ መልኩና ይዘቱ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ እየተካኼደና እየተፈጸመ ያለው ፍጅትና ትንንቅ፥ ግድያና ዕልቂት፥ ደም መፋሰስና መጨራረስ፡ ከቶ ምንድር ነው? ጦርነት አይደለምን? ነው እንጂ። ለዚህ፡ ምን ጥርጥር አለው? የለውም።

"ይህማ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም እና ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ፡ ወደዚህ ዓለም፡ ወደእናንተ መጥተን፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ መሲሕ፡ በሴትነትም፥ በወንድነትም፡ ሰው ኾነን፡ ያን ኹሉ የመስቀል ፈተናና መከራ፥ ሥቃይና ሞት በመሥዋዕትነትና በቤዛነት ተቀብለን፡ በትንሣኤያችንና በዕርገታችን፥ በመንፈስ ቅዱስም መውረድ፡ እናንተን፡ ከእንዲህ ዓይነቱ ሰይጣናዊ ግፍና ጭካኔ አድነናችሁ፡ ዘለዓለማዊዉን ድል፡ ለእናንተ፡ በማጎናጸፍ፡ ከጦርነት ነጻ የኾነ፡ ሰላማዊ ሕይወትን አስገኝተንላችሁ ሣለ፡ ያን መልካም ጸጋ፡ 'አንቀበለውም!' ብላችሁ፡ ስጦታችንን መጋፋታችሁና መቃወማችሁ አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

"ይህማ፡ እኛ፡ ታላቁን የመጨረሻ መሥዋዕትነትና ቤዛነት ከፍለን፡ ከለገሥናችሁ፡ ከዚያ የድል በረከታችን በፊት፡ በአውሬነትና በአረማዊነት፥ በአሕዛብነትና በክፉው ሰውነት ትኖሩበት፡ በነበረበት ጊዜ፡ ታካኺዱትና ትፈጽሙት የነበረው፡ አሠቃቂው የግፍና የጭካኔ አኗኗራችሁ መገለጫ አይደለምን?

"እንግዴህ፡ ይኼን የመሰለውን ግብራችሁን ነው? 'ሥልጣኔ! ሥልጣኔ! ያውም፡ ‹ክርስቲያናዊ› ሥልጣኔ!' እያላችሁ፡ የምትመጻደቁበትና የምትመኩበት? አዎን! ይኼ፡ 'ጦርነት' የምትሉት፡ የግፍና የጭካኔ ተግባራችሁ ነው? ክርስቲያንነት? ወይም፡ ሥልጥንና?

"ይህንንማ! እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመሥዋዕትነት መድኃኒትነታችንና በመስቀል የሰላም ቤዛነታችን ያስወገድነው አይደለምን? አዎን! በእርግጥ፡ የዛሬ ፪ሺ፰ ዓመት፡ ያስወገድነው ነው እንጂ።

"እናንተማ፡ ጥንቱኑም፡ እኛን ፈጣሪያችሁን መስላችሁ፡ የክፋት ጠንቅ፥ የኃጢኣት ቀንበርና የሞት ፍዳ ሳያገኛችሁ፡ በመልካም ሕይወት፡ ለዘለዓለም ትኖሩ ዘንድ፡ በእኛ መልክና ከእኛ፡ እንዳንዳችን አድርገን የፈጠርናችሁ ስትኾኑ፡ እናንተ ግን፡ ያን እግዚአብሔራዊ ተፈጥሮአችሁን ለውጣችሁና ያጎናጸፍናችሁን፡ የክብር ጸጋ፡ "እንቢ!" ብላችሁ፡ በገዛ ምርጫችሁና ፍላጎታችሁ፥ ፈቃዳችሁና ውሳኔያችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለክፋቱ አበጋዝ፡ ለዲያብሎስ ወገንነትና ተገዢነት የዳረጋችሁ አይደላችሁምን? አዎን! ናችሁ።

"እንዲያ ብትኾኑብንም እንኳ፡ እናንተን ፍለጋ፡ ወደእናንተው መጥተንና ሰው ኾነን፡ በፈጸምነው የመሥዋዕትነት መድኃኒትነታችንና ባስገኘነው የመስቀል ሰላም ቤዛነታችን፡ እናንተ፡ ኹላችሁ፡ በእኛ በእግዚአብሔር አብእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ፡ ቅድስት ሥላሴነታችን ተጠምቃችሁ፡ ከእኛ፡ እንደገና በእውነትና በመንፈስ በመወለድ፡ የእኛ የእግዚአብሔር ልጆች፥ ነጋሢዎችና ካህናት [በየሙያችሁ አገልጋዮች] ትኾኑ ዘንድ፡ አላበቃናችሁምን? አዎን! አብቅተናችሁ ነበር።

"ከዚህ የተነሣም፡ 'ክርስቲያን' ተብላችሁና በክርስትና ስም ተጠርታችሁ፥ እየራሳችሁንም፡ ከዚያ አውሬነታችሁና አረማዊነታችሁ፥ አሕዛብነታችሁና ክፉ ሰውነታችሁ፡ ለውጣችሁና ነጻ አድርጋችሁ አልነበረምን? አዎን! ፈጽማችሁ ነበር።

"ታዲያ! ይህን ኹሉ ሥርዓት መፈጸማችሁ፡ ከቀድሞው ምንነታችሁና ማንነታችሁ፡ በክርስቶስ ተለውጣችሁ፡ አዲሱ ሰው፥ እርሱም፡ 'ክርስቲያን' መኾናችሁን፡ ማረጋገጣችሁ አይደለምን? አዎን! በእርግጥ፡ ነው እንጂ።

"አለዚያማ፡ እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በእግዚአብሔርነታችንና በሰውነታችን፡ ስለእናንተና ለእናንተ የከፈልነውን፡ ያን የሚያህል፡ የመሥዋዕትነት መድኃኒትነታችንና የመስቀል ሰላም ቤዛነታችንን፥ እናንተም፡ እየራሳችሁን፡ ለክርስቲያናዊው ዘለዓለማዊ ሕይወት አብቅታችሁ፡ እንደገና የተወለዳችሁበትን፡ የክርስትናን እምነትና የለበሳችሁትን አዲስ ሰውነት፡ ከንቱ ማድረጋችሁ አይደለምን? አዎን! በእርግጥ፡ ነው እንጂ።

"አያችሁ! እናንት 'ልጆቼ! ሕዝቤ! ፍጡሮቼ!' የምላችሁ፡ እናንተ፡ ወንዶችና ሴቶች! ከኛ መለኮታዊ ፈቃድ ውጪ በመኾናችሁ፥ ደግሞም፡ ክፉውን ጦርነት፡ ድል መንሣት ስለምትችሉበት መንገድ፡ የተውንላችሁን አርአያነት፡ 'አንቀበልም!' በማለታችሁ፡ ምን እየደረሰባችሁ ነው?

"ከጥንቱ ጀምራችሁ ያስለመዳችሁትን፥ እኛ ግን፡ በቸርነታችን የሻርንላችሁንና በመሥዋዕትነት መድኃኒትነታችንና በመስቀል ሰላም ቤዛነታችን፡ ያስወገድንላችሁን፡ ያንኑ፡ ለዲያብሎስ ፍላጎት፡ የመገዛት ዝንባሌያችሁን፡ አኹንም በመከተልና በተግባር ላይ በማዋል፡ እናንተው ራሳችሁ፡ የፈጠራችሁት፡ ያ፡ 'የኑፋቄ ምርምር'፥ ያ "የመስቀል ጦርነት"፡ በእናንተው፡ በሰዎች ፍጡሮቻችን መካከል፡ እንዴት ዓይነቱን፡ የሃይማኖት መለያየትንና መጠላላትን እንዳመጣባችሁ፥ እንዲያውም፡ በጸና መልኩና ይዘቱ እንዲባባስ በማድረግ፡ ወደእርስ በርስ ጦርነት መርቶ እንዳስተላለቃችሁ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ክፉው ዓላማችሁ፡ እንዳልሠራላችሁና እንዳልጠቀማችሁ፡ አያችሁት አይደለም? አዎን! በገሃድና በግዘፍ አያችሁት።

"ያ ብቻም አይደለም፤ በየአብያተ-ክርስቲያናችሁ መካከል፡ በብዛት መከፋፈልንና ፀብ ክርክርን፥ በይሁድና፥ በክርስትናና በእስልምና ሃይማኖቶቻችሁም መካከል፡ የበለጠ መቃቃርን፥ በቅዱሳት መካናት ይዞታዎችም ረገድ፡ ምንም ያህል ለውጥ ሳይገኝ ከመቅረቱ በቀር፡ በእስላሞቹ እጅ እንዳለ ኾኖ፡ በመካከላችሁ ሳይቋረጥ የቆየው ጦርነት፡ ይኸው፡ እስከዛሬ፡ ተፋፍሞና ተጠናክሮ፥ ተስፋፍቶም ሲካኼድ ይታያል።

"እንዲያው ለመኾኑ፡ እናንተ የሰው ወገኖች! **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነታችን፡** እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በታወቀው የመሥዋዕትነት መድኃኒትነታችንና በመስቀል ሰላም ቤዛነታችን፡ አድሰን ባጸናነው፥ እናንተም፡ 'መሲሕ' የሚለውን፡ የልጄን የወዳጄን፡ የኢየሱስን፡ የግእዝ ቃለ-ስያሜ፡ በግሪኩ ቋንቋችሁ፡ 'ክርስቶስ' ባላችሁበት አጠራራችሁ፡ እየራሳችሁን፡ 'ክርስቲያን' ባሰኛችሁበት፡ በቅዱሱ ኪዳን የክርስትና ሃይማኖታችሁ በታነጸው አእምሮአችሁ፡ ይህን ኹሉ፡ የክፋትና የጥፋት ድርጊት፡ ቀድሞውኑ፡ ስታስቡትና ስታውጠነጥኑት፥ ስታካኺዱትና ስትፈጽሙት፡ በሰይጣናዊው የሓሰት ዝንባሌያችሁ አንጻር፡ መንፈስ ቅዱሳዊው የእውነት ጠበቃ የኾነው ኅሊናችሁ፡ ምን እያላችሁ ነበር?

"ይኸው ኅሊናችሁም፡ በእያንዳንዳችሁ፡ የሰውነት ተፈጥሮአችሁ ውስጥ፡ ገና በማሕፀን ሽልነታችሁ ቅጽበታዊ ጊዜ፡ በምስጢረ ሥላሴ የተዋሕዶ ሥርዓት፡ ከቅዱሱ መንፈሳችን ከፍለን የሰጠናችሁ፥ እኛ፡ 'መንፈስ' የምንለውና እናንተ ግን፡ 'ኅሊና' የምትሉት፥ በዚያ ማሕፀን፡ ከነፍሳችሁና ከሥጋችሁ መካከል፡ ዐብረን አስቀምጠንላችሁ የነበረው አካልና ባሕርይ ነው።

"የጦርነት ነገር፡ እንዲያ፡ ገና በአእምሮአችሁ ውስጥ በሚሠርፅበት ሰዓት፡ ታዲያ! ይኸው መንፈሳችሁ፥ ይኸው ኅሊናችሁ፡ እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በዚህ ረገድ፡ በመሥዋዕትነት መድኃኒትነታችን፡ የፈጸምንላችሁን፡ የመስቀል ሰላም ቤዛነታችንን በማዘከር፡ 'ተዉ እንጂ! ይኼማ አይኾንም፤ አይደረግምም።' አላላችሁም ነበርን? በእርግጥ፡ ብሏችኋል እንጂ፤ ሳይላችሁማ፡ እንዴት ይቀራል!?

"ይኸው መንፈሳችሁ፥ ይኸው ኅሊና ችሁ፡ በእያንዳንዳችሁ ሰውነት ውስጥ፡ ሕያው ህልውና ያለው ኹኖ፡ በዚያ እንዲገኝ ያደረግነው እኮ፡ እንኳንስ፡ የሰው ሕይወት፡ በግፍ ግድያ የሚጠፋበትን፡ ይህን፡ የጦርነትን፡ ታላቅ ጉዳይ ይቅርና፡ ማናቸውንም፡ ጥቃቅን ነገሮችን በሚመለከት ሳይቀር፡ እንደእኛ ኹኖ፡ ተገቢውንና አስፈላጊውን እግዚአብሔራዊ ዕውቀት እንዲገልጽ፥ ምክሩንና ዳኝነቱንም እንዲያበረክት፥ ተግሣፁንና ማስጠንቀቂያውንም እንዲሰጥ፥ ቍጥጥሩንም እንዲያደርግ ስለኾነ፡ ያለማቋረጥ የሚፈጽመው፡ ይህ፡ ከእኛ የተቀበለው የተልእኮ ግዳጁ፡ ምንጊዜም፡ ከእርሱ የሚጓደል አይደለምና። ይህን እውነታ፡ በምንም ምክንያት፥ በምንም መንገድ፡ ልታስተባብሉት አይቻላችሁም።

"ስለዚህ፡ እናንተ፡ ኹላችሁ፥ በተለይ፡ እናንተ፡ እየራሳችሁን፡ 'ክርስቲያን ነን!' ብላችሁ የምትጠሩ ኹሉ፡ የእኛ አማኞችና ተከታዮች፥ ፈቃድ ፈጻሚዎች ሳትኾኑ፡ የዲያብሎስ አማኞችና ተከታዮች፥ ፈቃድ ፈጻሚዎች መኾናችሁን፡ ይኸው፡ በተግባራችሁ ያሳያችሁ መኾናችሁን፡ እየራሳችሁ አረጋገጣችሁ።

"እንዲያው ለመኾኑ፡ በየትኛውም ዓይነት፡ -በሥጋዊዉም ኾነ፡ በመንፈሳዊው- አእምሮአችሁ ብታስቡት፡ እንኳንስ፡ እኔ፡ መለኮታዊቷ እና ሰብአዊቷ እናቱ ተጨምሬ፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ቀድሞ፡ በሰማይ፡ በመለኮትነቱ፥ ኋላም፡ በምድር፡ በሰውነቱ፡ እየተከተለ፡ ይኸው፡ የክፋቱ አበጋዝ የኾነው፡ ሓሰተኛውና ርኩሱ መንፈስ፡ ዲያብሎስ፡ ያስነሣበት የነበረውን፡ ረቂቅና ግዙፍ፥ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሰልፍና ጦርነት፡ የተዋጋው፥ ያሸነፈውም፡ እንዴት እንደነበረ፡ በየግላችሁ ስለምታውቁት፡ እኔ፡ አኹን፡ እንደገና ላስረዳችሁ፡ የሚያስፈልግ አይደለም።

"ይኸው ዲያብሎስ፡ እንደፈለገውና ባመጣጡ እንዳደረገው፥ በእኔ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም ላይ ሳይቀር፡ በተለይ በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ላይ፡ በሰውነታችን እየመጣብን፡ ያካኼደውና የፈጸመው ጦርነት፡ በታላቅ የጭካኔ ኃይሉ እንደነበረ፡ እየራሳችሁ፡ በየሃይማኖታችሁ ከምታውቁት በላይ፡ እኔም፡ ቀደም ብዬ፡ በተደጋጋሚ ባሰማኋችሁ ዝክረ-ነገር፡ በዝርዝርና በሚበቃ ተረድታችሁታል።

"ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንደዚያ፡ እንደበግ ተነድቶና ታሥሮ፥ ተገርፎና በመስቀል ላይ ተቸንክሮ፡ ለመታረድና ለመሞት የበቃው፥ እንዲያውም፡ ስላሠቃዩት ወገኖቻችሁና ለዚህ ግፍ አፈጻጸም ስላነሣሣቸው፡ ስለዲያብሎስ ጭምር፡ ይቅርታን፡ ከእኛ፡ እንዲያ፡ እስከመጠየቅ የደረሰው፡ ታዲያ! ለምን ኖሯል!? ቀድሞ፡ በሰማይ፡ በመለኮትነቱ፥ ኋላም፡ በምድር፡ በሰውነቱ፡ እርሱን፡ ዲያብሎስን፡ በመለኮታዊው እና በትስብእታዊው የማይወሰን ኃይሉ፡ ተቋቁሞና ተዋግቶ ማሸነፍ ስላቃተው ነበርን!? አይ! ያስ አይደለም። ታዲያ! ለምን ኖሯል?

"ያማ! በሰላማዊው እግዚአብሔርና በጦረኛው ዲያብሎስ፥ በመልካሙና በክፉው፥ በእውነትና በሓሰት፥ በሕይወትና በሞት መካከል፡ በዚሁ፡ በዲያብሎስ የተፈጠረው ጠላትነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፥ ለዘለዓለምም ሊወገድና ዘለዓለማዊው ዕርቅ ሊመሠረት የሚቻለው፡ በፍቅር እንጂ በጥላቻ፥ በሰላም እንጂ፡ በጦር ኃይል አለመኾኑን፡ ለሰብኣውያን ፍጡሮቻችን ኹሉ፡ ለመጨረሻ ጊዜ አረጋግጦ ለማሳወቅ አልነበረምን?

"አዎን! ይህን እውነታ፡ ለፍጥረታተ ዓለማቱ ኹሉ፡ ለማሳወቅ ነበር።

"ነገር ግን፡ ያ ኹሉ ጥረታችን፡ መና፤ ከንቱም ኾኖ፥ ሳይሠራም ቀርቶ፡ እነሆ፡ መላው ዓለምና ነዋሪዎቿ የሰው ልጆች፡ በዲያብሎሳዊው የጦርነት ሥልጣንና አገዛዝ ሥር፡ በባርነት ቀንበር ታግተው የሚኖሩ ምስኪን ሰለባዎች ኾኑ።

"እንግዴህማ! ይኼ ሓሳዊ የክፋትና የጥፋት ግብር፡ እንዴት እንዲህ ሊቀ ጥል ይችላል? አይችልም። እኔና ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዲህ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ተገልጠንና ገሃድ ኾነን፡ ፍጥረታተ-ዓለማችንን፡ በሰማይም፥ በምድርም፡ እየመራንና እየጠበቅን፥ እየመገብንና እያስተዳደርን፥ እየተቆጣጠርንና ይኸው፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌም እያናገርኋችሁ ባለንበት፡ በዚህ ጊዜማ፥ እንግዴህ ወዲህ፡ ይህ ኹሉ፡ የዲያብሎስ አገዛዝ ሊኾ ንና ሊቀ ጥል አይችልም።

"አታዩምን? አታስተውሉምንስ? ዲያብሎስና ጭፍሮቹ፡ ርኩሳን መናፍስትና ክፉዎች ሰዎች ያመጡትን፡ የጥፋትና የጦርነት ነገር ኹሉ፡ እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በውርደት ና በትሕትና፡ በከፈልነው የፍቅር መሥዋዕትነታችንና የሰላም ቤዛነታችን፡ መላውን፡ ምድራዊ ፍጥረተ-ዓለም፡ እንዴት አድርገን፡ በሥጋና ደም ቍርባናችን አንጽተንና ቀድሰን እንዳደስነው!?

"እኛን ለፈለጉንና ለመረጡን፥ ላመኑብንና ለተከተሉን ሰብአውያን ፍጡሮቻችንም ኹሉ፡ ከክፉው የዲያብሎስ ገዢነት፡ ወደመልካሙ የእግዚአብሔር ልጅነት፥ ከሓሰቱ የኃጢአት ኑሮ፡ ወደእውነተኛው የነጻነት ህልውና፥ ከጨለማው የሞት ፍዳና ከማያቆመው የሲዖል ሥቃይ፡ ወደብርሃናዊው የትንሣኤ ሕይወትና ወደዘለዓለማዊው የሰንበት ዓለም፡ እንዴት አሻግረን፡ በዚህ ዓለም፥ በዚህ ሥጋዊ ሰውነት እያሉ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ውስጥ እያሳለፉ ያሉትን፡ ጦርነት አልባና ሰላማዊ የኾነ ገነታዊ አኗኗር፡ አታዩምን? አዎን! መልካሙን፡ እግዚአብሔራዊ ሕይወት፡ በምስጋና እየኖሩ ናቸው።

"ለዚህ ኹሉ እውነታ፡ ሌላ ማስረጃ ሳያስፈልግ፡ በቂና አጥጋቢ፥ ማጠቃለያና መደምደሚያ የኾነውን መለኮታዊ ምስክርነት፡ በቀጥታና በቀላሉ፡ ከራሷ **ከሥነ ፍጥረት** ታገኛላችሁ። ይኸውም፡ ባለፈው ያዋጅ ቃሌ፡ በሰፊው የተናገርሁላት፥ ተገቢውንና አስፈላጊውን መመሪያ ሰጥተን ያስገኘናትና የሠራናት፥ የምንመራትና የምንቆጣጠራት፡ ይህችው **ሥነ-ፍጥረት፡** አካላቷ የኾኑት፡ ምድርና ሰማይ፥ በውስጣቸው ያሉትም የፍጥረታት ዓይነቶች ኹሉ፡ የየአንዳንዳቸው፡ የአገልግሎት በረከት፡ አቅርቦትና ክዋኔ፡ በየአፍታውና በየደቂቃው፥ ሌት ከቀን፥ በየዐውደ ወርኁና በዓመቱ ዙርያ፡ ያለ አንዳች ቀውስና ሁከት፥ ፍጹም ጸጥታንና ጽናትን በተጐናጸፈ እንዲህ ባለ ሥርዓት፡ እንዴት እንዲካኼድ እንደምታደርግ፡ ይኸው፡ በማይዛነፈውና በማይቋረጠው ቋሚ ኺደቷ፡ ዘወትር ሲፈጸም የምትመለከቱት ነው።

"ታዲያ! አኹንም፡ ይህን የመሰለው ትንግርት፡ 'ጥንቱኑም፡ እንዴት እውን ሊኾ ን፥ ውጤቱም እንዲህ ሊሠምር ቻለ?' ብላችሁ የምትጠይቁ ብትኖሩ፡ መልሱ፡ 'እኛ፡ የሥነ-ፍጥረት ሠሪዎቿ፡ እርሷንና ሥርዓቷን፡ **በፍቅርና በሰላም** መሠረትነትና አቋምነት፥ ድምድማትነትና ጒልላትነት ስላነጽናት ነው!' የሚል ይኾናል።

"**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንም፡** እንደሥነ ፍጥረትና እንደሥርዓቷ ኹሉ፡ **በፍቅርና በሰላም** መሠረትነትና አቋምነት፥ ድምድማትነትና ጒልላትነት ያነፅናትና ያጸናናት በመኾኗ፡ ኹለቱም መለኮታውያን አካሎች፦ እነርሱም፡ **ሥነ ፍጥረትና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡** ይኸው፡ ለ፯ሺ፭፻፰ ዓመታት፡ ሳይነዋወጡና ሳይታወኩ፡ ከጦርነት ነጻ የኾነ ህልውናቸውን፡ ያለድቀት እንደቀጠሉ ይኖራሉ።

"ይህንም እውነታ፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ **'መንግሥትየሰ፡ ኢኮነት፡ እምዝንቱ ዓለም!**

"'መንግሥቴ፡ ከዚህ ዓለም አይደለችም!' ብሎ፡ በመስቀሉ መከራና በሞቱ፥ በትንሣኤውና በዕርገቱ፥ በመጨረሻም፡ በመንፈስ ቅዱስ መውረድ፡ በዚህ ዓለም፡ የዲያብሎስንና የክፉ ሰዎችን የአገዛዝና የጦርነት አቋሞችን አፈራርሶ ከማስወገዱ አስቀድሞ፡ በአይሁድ ግፊት፡ የስቅላት ሞትን ለፈረደበት፡ ለጲላጦስ የተናገረው ቃል አረጋግጦታል።

"ይኸውም፡ ዛሬ፡ **በእርሱ፡ በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ንጉሥነት፥ በእኔም፡ በእናቱ ንግሥትነት በምትመራው፥** ደግሞም፡ ምንጊዜም፡ ዲያብሎስንና የክፋት ሠራዊቱን እየተዋጉ ድል በሚነሡት፡ በቅዱሳን መላእክቱ፡ በእነሚካኤልና ገብርኤል አገልግሎት በምትጠበቀው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን የዐዋጅ ቃላት ተፈጽሞና እውን ኾኖ በመገኘቱ፡** እነሆ፡ የዚያች **መንግሥቱን ምንነትና ማንነት፡** በፍጥረተ-ዓለሙ ዘንድ፡ እንዲህ ባለው መልክና ይዘት፡ እንዲገለጥና እንዲታወቅ ማድረጉ ነው። (ዮሐ. ፲፰፥ ፴፫-፴፰።)

"ክፉን በክፉ መቃወም፡ የባሰ ክፋትን መፍጠር እንደመኾኑ ኹሉ፡ ኃይልን፡ በኃይል መቃወምም፡ እንዲሁ፡ የባሰ ተቃዋሚ ኃይልን ማስከተል ነው። ክፋትን፡ በደግነት፥ ኃይልንም፡ በፍቅር ተቀብሎ ማስተናገድ ግን፡ ኹለቱንም ኅሊና ትና ርእዮታት፣ ህላውያትም፡ በየአካላቸውና በየባሕርያቸው፡ ለደግነትና ለፍቅር፥ በመጨረሻም፡ <u>ለፍጹሟ የእግዚአብሔር ሰላም</u> ማብቃት ነው። ይህ፡ የሥነ ፍጥረት ሥርዓት፡ ቋሚና ፍሬያማ ኾኖ፡ በሕያውነት ሲሠራ ይኖራል።

"ለዚህ ነው፡ እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደዚህ ዓለም፡ በሰውነት መጥተን፡ ክፉውን የዲያብሎስን የጦርነት ኃይል፡ በመለኮታዊው ኾነ፡ በሰብአዊው ኃይል ሳይኾን፡ በመለኮታዊው ኾነ፡ በትስብእታዊው ፍቅር ተቋቁመን፡ ድል ልንነሣው የበቃነው። እናንተም፡ ኹላችሁ፡ ለመልካሙ ዘለዓለማዊ ሕይወታችሁ ስትሉ፡ በየግላችሁ፡ የእኛን፡ የፍቅርና የሰላም ፈለግ መከተልና መፈጸም የሚኖርባችሁ።

"እዚህ ላይ፡ አንተኑ ኤርምያስን ልጠይቅህ! ምንጊዜም፡ ቃሌን አምነህ የምትቀበልና የምትፈጽም መኾንህን ዐውቃለሁ።

"እዚሁ፡ አኹን፡ ዐብረኸኝ፡ በቅርብ ስላለህ ነው፡ ለዚህ የዐዋጅ ቃሌ ተአማኒነት እንዲያግዝ፡ አንተኑ፡ በአርአያነት ላቀርብህ የፈለግሁት። በግልም ኾነ በቤተሰባዊ ኑሮህ በኩል፡ በዚሁ በጦርነቱ ርእስ ረገድ፡ ያሳልፍኸው ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ እኔ የማውቀው ቢኾንም፡ ለሌሎች ትምህርት ይኾናቸው ዘንድ፡ እስኪ ንገረኝ! *[ጥቂት ቆይታ!]*

"ኤርምያስ ያለኝን፡ በእኔው አንደበት ስሙት! «እምዬ! ፈቃድሽ የኾነውን ጥያቄሽን፡ ዝም ብዬ በመፈጸም፡ መልሴን ከመስጠት በቀር፡ ለእኔ፡ ለታናሹ አገልጋይሽ፡ ይህን ክብር ስለመስጠትሽ፡ ሌላ የምለው ነገር አይኖረኝም።

"«አዎን! እመቤቴ ሆይ! እንደማንኛውም፡ ሰብአዊ ፍጡራችሁ ኹሉ፡ እኔም፡ ገና በማሕፀን ሣለሁ፡ በውስጤ ባሳደራችሁት የመንፈስ ቅዱስ ዕውቀቴ ምክንያት፡ ነፍስ ካወቅሁበት፡ ሕፃንነቴ አንሥቶ፡ እስከዚች አፍታ ድረስ፡ ለመከላከያ ኾነ፡ በሌላ ሰው ላይ፡ ጉዳትን ሊያደርስ የሚችል፡ ሥንጥርም እንኳ፡ ‹ልያዝ!› ብዬ፡ እንኳንስ ማድረጉ፡ በአሳብም እንኳ፡ በአእምሮዬ መሥረፁን አላስታውስም።

"«አኹን፡ አንቺ ርኅርኅቷ እናቴ፡ ይህን ጥያቄ፡ ለእኔ ባቀርብሽባት በዚች ሰዓት፡ የገረመኝና በቅጽበት የታሰበኝ ነገር ቢኖር፡ ይህ፡ የእኔ፡ የአኹኑ የትዝታ አስተሳሰቤ ሳይኾን፡ ከሥጋ ወላጆቼ ጀምሮ፡ ማንም ሌላ ሰው፡ ወንድ ኾነ፡ ሴት፡ እኔን፡ በእጁ ኾነ፡ በበትር ሊመታኝ፥ ወይም፡ ሊጎዳኝ የሞከረ፡ አንድም እንኳ እንዳልነበረ፡ በእርግጥ የማስታውሰው ነው።

"«ከሰባት ዓመታት በላይ፡ በእሥር ቤቱ ያቆየኝ፡ "ደርግ" የተባለው፡ የቅጣት ኃይል እንኳ፡ በባልደረቦቹ በኩል ያደርግልኝ ከነበረው፥ ካልፈለግሁትና ካልጠበቅሁት፡ አክብሮቱና እንክብካቤው በስተቀር፡ በንግግር እንኳ፡ ያስቀይመኝና ያሳዝነኝ የነበረ ቃልን እንዳልሰማሁበት ትዝ ይለኛል።

"«በዚህ ረገድ፡ የአንቺን፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ ቃልሽን ለማጽናት፡ ‹ይህ፡ በእኔና ለእኔ የኾነው እውነታ፡ አንቺ፡ በቸርነትሽ የገለጽሽልን፡ የሥነ-ፍጥረት ሥርዓት ውጤት ነው!› ብዬ እንዳምንና እንድቀበለው አስችሎኛል። እምዬ! ቃል አብዝቼ ከኾነ፡ ባሕርይሽ ነውና፡ ይቅር በዪኝ!»

## ለትዝብትና ለኑዛዜ ያህል፡ እናንተንም፡ ይህን፡ ልበላችሁ!

"በመላው ዓለም የምትገኙ፡ ሰብአውያንና ሰብአውያት ፍጡሮቼ! ይልቁንም፡ እየራሳችሁን፡ 'ክርስቲያን ነን!' የምትሉ ሕዝቦቼ፥ በተለይም፡ እየራሳችሁን፡ በስሜ፡ 'ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት!' ብላችሁ የምትጠሩና እንዲህ ተብላችሁ መጠራትንም፡ የምትወድዱ ልጆቼ!

"እኔ፡ እማውቃችሁና እምሳሳላችሁ እናታችሁ፡ ለጥቂት አፍታ፡ ወደኋላ፡ መለስ ብዬ፡ አንዳንድ ቊም-ነገሮችን ላስታውሳችሁ ነኝና፡ እስኪ! እናንተም፡ መንፈሳዊ ጆሮአችሁንና የየኅሊናችሁን መጋረጃ ከፍታችሁ፡ የእኛን መለኮታዊ እውነት ሰምቶና ተቀብሎ፡ ሊያስተውል በሚችለው፡ የአእምሮ መድረካችሁ ላይ ኾናችሁ፡ አዳምጡኝ!

"<u>አንደኛ፡</u> ስለኢትዮጵያ፡ **የእግዚአብሔር *መንግሥታችንና መንግሥታችሁ፡* *ምንነትና ማንነት፡*** ራሷ፡ ሕያው ኾና፡ በየራሳችሁ መንፈሳዊ ሰውነት ውስጥ፥ በውጭም፡ በግዙፉ ሥነ-ፍጥረታችን፡ እውን ኾና፡ እየሠራች ያለች በመኾኗ ታውቋታላችሁ።

"ከዚህም ጋር፡ በየጊዜያቱ፡ በአገልጋይ ልጃችን፡ በኤርምያስ አማካይነት፡ በቃልና በጽሑፍ፥ በዕትምም፡ እስካኹን ሲተላለፍላችሁ በቆየው ተከታታይ መልእክታችን፥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም፡ በእኔና በልጄ ወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የዐዋጅ ቃሎች፡ ስለእርሷ፡ በሚበቃ ስለተነገረና ተጽፎ ስለተነበበ፡ ብዙዎቻችሁ፡ በዚህ ዕድል በመጠቀም፡ እርሷን፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥታችንን*** በሚመለከት፡ የሚያስፈልጋችሁን ያህል እንዳወቃችሁና እንደተረዳችሁ፥ እንደተገነዘባችሁም ተመልክቻለሁ።

"ምናልባት እስካኹን፡ እየራሳችሁን፡ ለዚህ ዕድል ያላበቃችሁ ካላችሁ፡ አኹንና ምንጊዜም፥ ወደፊትም፡ ዕድሉ፡ ክፍት ኾኖ ስለሚጠብቃችሁ፡ በእርሱ ተጠቅማችሁ፡ አብዛኛዎቻችሁ፡ በፈቃዳችሁና በምርጫችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚሁ ገናና **እግዚአብሔራዊ ዕውቀት** ልታበቁ እንደምትችሉ ዐውቃለሁ።

"እንግዲህ፡ አስተውላችሁ ተመልከቱት! እንዲህ ያወቃችኋትንና እንዲህ ያለችውን፡ ይህችን፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥታችንንና መንግሥታችሁን*** እኮ ነው፡ እናንተ፡ ኹላችሁ፡ ዛሬ፡ እንዲህ፡ በቤተ ሕዝባችሁና በቤተ ምልክናችሁ ብቻ ሳይኾን፡ እንዲያውም በይበልጥ፡ በቤተ ክህነታችሁ ጭምር፡ በገሃድና በይፋ፥ በሕጎቻችሁ ሳይቀር፡ 'አናውቃትም! አንፈልጋትም! አንቀበላትም!' ብላችሁ፡ በምድር ላይ፡ አንዲት የቀረችን፡ የስማችን መጠሪያ አገርና ሕዝብ ቢኖሩን እንኳ፥ በተለይ እኔን፡ ከዚያች የቃል ኪዳን ዓፀመ ርስት አገሬ አስወጥታችሁ፥ ከእነዚያ ርስተ-ጕልት ሕዝቤም ለይታችሁና አሽቀንጥራችሁ ልትጥሉኝ እየሞከራችሁ ያላችሁት?!

"ይህን ስሞታ የማሰማችሁ፡ እንዲያው፡ ለትዝብቱ ያህል፡ በእየራሳችሁ ኀሊና እንድትገነዘቡት ብዬ ነው እንጂ፡ 'ሙከራችሁ ይሳካላችኋል!' ማለት አይደለም። እርሱማ፡ አይኾንላችሁም። ምናልባት፡ አኹንም፡ በዚሁ ሙከራችሁ ጸንታችሁ፡ በመቀጠል ላይ ከኾናችሁ፡ አትድከሙ! በምንም መንገድ፡ ፈጽሞ፡ የሚሳካላችሁ እንደማይኾን ተረዱት!

"ከዚያ ይልቅ፡ እናንተ፡ በእውነተኛ ንስሓችሁ ተመልሳችሁ፡ የዛሬ፡ ኹለት ሽህ ስምንት ዓመት በሰጠናችሁ፥ አኹንም፡ በዚህ ዐዋጄ፡ ባጸናሁላችሁ፡ የቃል ኪዳን ይቅርታችንና ምሕረታችን ተጠቅማችሁ፡ እየራሳችሁን አድኑ! ነገር ግን፡ ይህን ሃይማኖታዊ ምግባር በመፈጸም፡ እየራሳችሁን ለማዳን ካልፈለጋችሁ፡ እናንተው፡ ፈጽማችሁ ትጠፋላችሁ እንጂ፡ እርሷማ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥታችንና መንግሥታችሁ፡*** እየለማችና እያደገች፡ በዘለዓለማዊው ህልውናዋ ትቀጥላለች።

"የዚችው **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥታችንና መንግሥታችሁ*** በኾነው፡ **በቅዱሱ ኪዳን** ላይ፡ ዛሬ፡ ይህን፡ የአኹኑን፡ የክህደት ና የዓመፅ ድርጊታችሁን፥ የክፋትና የአምልኮ ምንዝርና ኃጢአታችሁንም፡ እያካኼዳችሁና እየፈጸማችሁ ያላችሁትን፡ እናንተን፡ በእነማን የምመስላችሁ ይመስላችኋል?

"በአንድ በኩል፡ 'የእስራኤል ልጆች ነን!' በሚሉት፡ በአፀራረ-እግዚአብሔርና በቀታልያኑ አይሁድ፤ በሌላውም በኩል፡ 'ክርስቲያን ነን!' እያሉ በሚመጻደቁት፡ በግብዞቹ፡ ኦርቶዶክሳውያን፥ ካቶሊካውያንና የፀረ-ማርያም ወገኖች ነዋ!

"በቅድሚያ፡ የመጀመሪያዎቹን በሚመለከት የምገልጸው ይኾናል፡-እነርሱም፡ **ኢትዮጵያውያኑ ልጆቻችንና አገልጋዮቻችን ከኾኑት፡ ከካህኖቻችን ከዮቶርና ከሙሴ** አፍ፡ ቀድሞ፡ ተምረዋትና ዐውቀዋት፥ ለጊዜውም ቢኾን፡ ተቀብለዋትና አምነውባት፡ እስከነቢያችን ሳሙኤል ድረስ፡ ሲሠሩባት ቆይተው፥ ኋላ፥ ከዚሁ ነቢያችንና ከእኛም፡ ተደጋጋሚ ምክርና ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም፡ ***'እንቢ! አሻፈረን! የአሕዛብን የአገዛዝ ልማድ እንጂ፡ በእናንተ፡ በእግዚአብሔር አባትነትና እናትነት፥ ንጉሥነትና ንግሥትነት፥ ካህንነትና ካህኒትነት የምትመራውን፡ ይህችኑ የእናንተን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን መለኮታዊ ሥርዓት አንፈልግም!'*** ያሉት፡ አይሁድ ናቸው። (፩ ሳሙ. ፰፥ ፩-፳፪።)

"የኋለኞቹም፡ አዲሱ ክርስቲያናዊ ቄሣር ቆስጠንጢኖስ፡ በ፫፻፳፭ ዓመተ-ምሕረት፡ በኒቅያ የሰበሰባቸው፥ እነርሱም፡ ይህችኑ፡ አንዲት፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥታችንን፡* ለኹለት በመክፈል፡** *መንፈሳዊዉን ወገን የሚወክለውን፡* **'ቤተ-ክርስቲያን፥** *ሥጋዊዉንም ወገን የሚወክለውን፡* ***'መንግሥት፥*** *በቋንቋቸው፡* 'Church and State' *ብለው ለፈጠሩት፡ የ'ሕዝባዊ አገዛዝ'* [Democracy] *ስልታቸው፡ መነሻ የኾነውንና ተፈጻሚነቱ እስከዛሬ የቀጠለውን መመሪያ፡ በሕግ መልክ ቀርጸው ያቀረቡለት፡* ፫፻፲፰ቱ የቤተ ክህነት *መሪዎቻቸውና ሊቆቻቸው* ናቸው።

"ይኸው፡ የኹለቱም ወገኖች ቃላቸውና ዝክረ-ነገራቸው፡ እየራሳቸው በጻፏቸው፥ *መላው* የዓለም ኅብረተሰብም በተቀበላቸው፡ በመጽሓፍ ቅዱስና በፍትሓ *ነገሥት ተመዝግበው* እየተነበቡ ይገኛሉ።

"እናንተም፥ ሌላውም፥ ኹላችሁም፡ ይህን ኹሉ እውነታ፡ *ታውቁታላችሁ።* ማወቅ ብቻ አይደለም። ለዚህ ኹሉ ፀረ-እግዚአብሔርና የግብዝነት *ሥራችሁ፡* እየተከፈላችሁ ያለውን የቅጣት ዋጋ፡ በእየራሳችሁም ላይ እየደረሰ ስላለ፡ ይኸው፡ እስከዛሬ፥ ወደፊትም፡ በሥጋትና በጭንቀት፥ ደም በመፋሰስና በዕልቂት ጦርነት ተዘፍቃችሁ የምትሠቃዩበትንና የምትማቅቁበትን ኹኔታ፡ ያለማቋረጥ ትመለከቱታላችሁ።

"*ታዲያ!* በአኹኑ ጊዜ፡ ይህን *መሰሉ* ኹኔታ፡ እንዴት! በእናንተ ዘንድ ሊኾ ን ቻለ!? *ያውም* በእናንተ፡ በእየራሳችሁ ኾነ፡ በባዕዳኑ ሳይቀር፡ በስሜ 'ኢትዮጵያውያን!' እና 'ኢትዮጵያውያት!' ተብላችሁ በምትጠሩት ዘንድ!? እኔም፡ "ልጆቼ!" እያልሁ በምጠራችሁ ዘንድ!?

"በቤተ-ሕዝቡ፥ በቤተ-ምልክናውና በቤተ-ክህነቱ ውስጥ ያላችሁ፡ *አዎን!* እናንተ ልጆቼ ሳትቀሩ፡ እናንተም ጭምር!? ይህ፡ እንዴት! በእናንተ ዘንድ ሊኾ ን ቻለ!? እኔን፡ በየልቦናችሁ 'እምዬ ማርያም!' እያላችሁና ከየአፋችሁ ሳትለዩኝ፡ ዘወትር የምትጠሩኝን፡ እኔን፡ እናታችሁን፡ በክህደታችሁና በዓመፃችሁ፥ በክፋታችሁና በአምልኮ ባዕድ አመንዝሪነታችሁ፡ እንዴት፡ እንዲህ አድርጋችሁ፡ ከየልቦናችሁ አውጥታችሁ ትጥሉኝ!?

"ሌሎቹ፡ የተቃዋሚዎቻችን ባዕዳን መሣሪያዎች ኾነው፡ እንዲህ ሲጥሉኝና ሲያጥላሉኝስ፡ እናንተም፡ ከእነርሱ ጋር ተባባሪዎች ኾናችሁና ዝም ብላችሁ እንዴት ትመለከታላችሁ? ሌላው ቢቀር፡ ከሚመጣው መቅሠፍታዊ ጥፋት፡ እየራሳችሁን ለማዳን ስትሉ፡ በእየራሳችሁ ውስጥ ያለኝን፡ የእናትነትና የሃይማኖትነት፥ የአገርነትና የንግሥትነት ቦታዬን፡ ለሌላው፡ ለአጥፊውና ለገዳዩ ክፉ አበጋዝ፡ እንዴት ለውጣችሁና አሳልፋችሁ ትሰጣላችሁ?

"የልጄ የወዳጄ፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እናት ከኾንሁት፡ ከእኔ በቀር፡ ከማናቸውም ተፈጥሮአዊና ሰው-ሠራሽ የጥፋት መዓት፡ ሊሠውራችሁና ሊያተርፋችሁ የሚችል፡ ሌላ ኃይል፡ በምድርም፥ በሰማይም እንደሌለ፡ 'አላወቃችሁም!' ልበልን? ካላወቃችሁ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ቀኑ ሳይመሽና ሰዓቷ ሳትደርስ፡ እውነታውን ለማወቅ፡ ነቅታችሁና ተግታችሁ፡ እየራሳችሁን አብቁ! ተዘጋጅታችሁም ጠብቁ!

"**<u>ኹለተኛ</u>፡** እዚህ ላይ ሳልጠቅስላችሁ የማላልፈው፡ ታላቅ ቍም-ነገር አለ፤ ይኸውም፡ 'ልጆቼ! ካህናቶቼ! ነጋሢዎቼ! ሕዝቤ!' በምላችሁ፡ በእናንተ ዘንድ፥ ደግሞም፡ "ብሔረ-ሙላዴ! ዐፅመ ርስቴ! ርስት ጕልቴ! መካነ-መንግሥቴ!" በምላት፡ በዚች ምድሬ ላይ፡ 'እግዚአብሔር' ከሚለው አጠቃላይ ስማችን ጋር፡ 'ኢትዮጵያ' በሚለው በተቀደሰው ስሜና በ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ስም፡ እየኾነና እየተፈጸመ የተኖረውን፥ እስከዛሬና ዛሬም፡ እየተካኼደና እየተፈጸመ ያለውን አደናጋሪ ኹኔታና አጠያያቂ ድርጊት የሚመለከተው ነው።

"እንግዴህ፡ በማስተዋል እዩት! ተመልከቱትም! እንዲህ ባለው፡ በተቀደሰው ስማችንና በተቀደሰችው ምድራችን ላይ፡ ለዝንተ ዓለም፡ እስካኹን የተፈጸመው፥ አኹንም፡ በእውን እየተፈጸመ ያለው፡ ከቶ ምንድር ነው? በይበልጥና አብዛኛው፡ በአምልኮ ባዕድና የእርሱ መራራ ፍሬ በኾነው፡ በእርስ በርስ ደም መፋሰስና መጋደል የተመላው፥ የጦር አበጋዙ ዲያብሎስም፡ ያን ኹሉ የሰው ደም በመጠጣት የሚረካበት፡ የጦርነትና የዕልቂት ድርጊት አይደለምን? አዎን! ነው።

"አኹን ካላችሁበት ጊዜ ጀምራ ችሁ፡ ወደቀደሙት የቅርቦቹ ዘመናት፡ ወደኋላ መለስ ብላችሁ በትኵረት ብትመለከቱ፡ ኹሉም፡ ፈጽመው፡ በዚሁ፡ የአምልኮ ባዕድ ቀንበር ተቀፍድደው፡ በሰልፉና በሠይፉ አበጋዝ፡ በዲያብሎስ እየተመሩ፡ በእርስ በርስ ደም መፋሰስና መጋደል የተላለቁበት፡ የጦርነትና የፍዳ ዘመን ኾኖ ታገኙታላችሁ።

"በእኛ መለኮታዊ ዕቅድ መሠረት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሓረግ፡ ስድስተኛ እርከን የኾነውን፡ የኪዳነ ዳዊትን አምላካዊ የቃል ኪዳን ዘር፡ ከእስራኤላዊው የዳዊት ልጅ፡ ከንጉሥ ሰሎሞን፡ በድንግል ማሕፀኗ ተቀብላ ትመለስ ዘንድ፡ ወደአባቷ፡ ወደመልከ-ጼዴቅ ከተማ፡ ወደኢየሩሳሌም የላክናት፡ ታማኟ ልጃችን፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ በዚያች ከተማ፡ ተልእኮዋን ፈጽማ፡ ስሜ ወደተጠራባት፡ ወደአገሯ ወደኢትዮጵያ እንደተመለሰች፥ ምኒልክንም እንደወለደች ታውቃላችሁ።

"ከምኒልክ ሥርወ መንግሥት የዘር ሐረግ የተገኘሁት እኔ፡ ድንግል ማርያም በወለድሁት፡ በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሰውነት፡ ያ፡ በኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳና በእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን የዘር ውሕደት የተመሠረተው፡ የሥርወ መንግሥት ሐረግ፡ በሥጋዊ የዘር ሐረግነቱ፡ አብቅቷል፤ቆሟል፤ የለም። እኔ፡ ድንግል ማርያም በወለድሁት፡ በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ መንፈሳዊና መለኮታዊ፥ ኹለንተናዊና ዘለዓለማዊ፡ የትውልድ ሐረግም ተተክቶ፡ እነሆ፡ ከዚያ ወዲህ፡ ለኹለት ሺህ ስምንት ዓመታት፡ እስካኹን ቀጥሎ ይገኛል። ወደፊትም የሚቀጥለው፡ ይኸው፡ ዘለዓለማዊና መለኮታዊ ሥርዓት ነው።

"ይህ የእግዚአብሔር እውነታ፡ እንዲህ በሚለው፡ በአደራ ልጄ፡ በዮሓንስ የምሥ ራች መጽሓፍ ተረጋግጧል፡- '**ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ፤ ወውእቱ ቃል፡ ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ፤ ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል። ...ወውእቱ ቃል፡ ሥጋ ኮነ። ...ውስተ ዚአሁ መጽአ፤ ወእሊአሁሰ ኢተወክፍዎ። ወለእለሰ ተወክፍዎ፡ ወሀቦሙ፡ ሥልጣነ፡ «ውሉደ እግዚአብሔር» ይኩኑ፤ ለእለ አምኑ በስሙ። እለ ኢኮኑ፡ እምነ ዘሥጋ፥ ወደም፤ ወኢእምሥ ምረተ ብእሲ፥ ወብእሲት፤ አላ፡ እምእግዚአብሔር ተወልዱ።**

"'በመጀመሪያ፡ ቃል ነበረ፤ቃልም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም፡ እግዚአብሔር ነበረ። ...ቃልም፡ ሥጋ ኾነ። ...የእርሱ ወደኾነው መጣ፤ የእርሱ የኾኑትም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ኹሉ ግን፥ በስሙ ላመኑት፣ ለእነርሱ፡ «የእግዚአብሔር ልጆች» ይኾኑ ዘንድ፡ ሥልጣንን ሰጣቸው። እነርሱም፡ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፡ ከሥጋና ከደም፣ ወይም፡ ከወንድና ከሴት ፈቃድ የተወለዱ አይደሉም።" (ዮሓ. ፩፥ ፩-፲፬።)

"እንግዲህ፡ 'የሰሎሞን ዘር ነን!' የሚሉ፡ በስሜ የሚጠሩ ወገኖችና የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 'ጳጳሳት' የሚባሉት መነኵሳት በመመሣጠር፡ **ይህን የእግዚአብሔርን ቃል እያወቁ፡ በድፍረት በመተላለፋቸው፡** የተዘፈቁበት ታላቅ ኃጢአት፡ ጉዳትንና ጥፋትን እንጂ፡ በተግባር ላይ ውሎ፡ ሊጠቅማቸው ሳይችል ቀርቷል።

"ከዚህ የተነሣ፡ እየራሳቸውን ብቻ ሳይኾን፡ ሕዝቤንና ምድረ ርስቴን፡ ለዲያብሎስ የአምልኮ ባዕድ ርኵሰትና በመካከላቸው ለሚካኼደው የእርስ በርስ ጦርነታቸው ዳርጓቸው፡ ይኸው፡ ለዝንተ ዓለም፡ ደም ሲፋሰሱና ሲተላለቁ፥ በየግላቸውና በጋራም፡ በሥጋቸውና በነፍሳቸው፥ በመንፈሳቸውና በኹለንተናቸው ሲሠቃዩና ሲማቅቁ ይኖራሉ።

"ለዚህ እውነታ፡ ምስክር እንዲኾናችሁ፡ 'የሰሎሞን ዘር' የሚባለው፡ ሓሳዊና አይሁዳዊ ይትበሃል፡ በእኛ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** ዘንድ፡ የተሻረና የማይሠራ፥ የሌለና ምትሓት መኾኑን፡ አረጋግጠን ያሳየንበትን መለኮታዊ ሥራ፡ እዚህ ላይ፡ በምሳሌነት በመጥቀስ አወሳላችኋለሁ።

"ይኸውም፡ በዚህ የዘር ሐረግ ውስጥ፡ 'ምንም ዓይነት አሻራ የላቸውም!' የተባሉትን፥ እንደተለመደውም፡ ከትውልዱ የክፋትና የክህደት ፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአት የተነሣ፡ ሊቀጡትና ዋጋውን ሊከፍሉት፡ በጉልበታቸውና በጦር ኃይላቸው፡ ሥልጣን የያዙትን፡ ቴዎድሮስን፣ ተክለ-ጊዮርጊስን፥ ዮሓንስን፡ የመሰሉትን አጼዎች፥ ደግሞም፡ "የዘውዱ ባለመብቶች ናቸው!" የተባሉት፤ ምኒልክንና እርሱ፡ "አልጋ ወራሼ" ብሎ የሠየመውን፡ የልጅ ልጁን ኢያሱን፥ ከዚያም፡ ምእመኒቱን ሴት ልጁን፡ ዘውዲቱን፥ በመጨረሻም፡ ኃይለ ሥላሴንና እርሱን ያስወገደውን፡ "ደርግ" የተባለውን የቍጣ ቡድን የመራውን መንግሥቱ ኃይለ-ማርያምን፥ የዛሬዎቹን፡ በእነመለስ ዜናዊ ተቋቁሞ፡ በእነደሳለኝ ኃይለ ማርያም የሚካኼደውን አገዛዝ የሚያካትተው ዝክረ-ነገር ነው። እነዚህ ገዢዎች፡ የሕይወት ዘመናቸው፡ በጦርነት ተጀምሮ፡ በጦርነት ማብቃት ብቻ ሳይኾን፡ አብዛኞዎቹ፡ ፍጻሜያቸው የማያምር ኾኖ፡ እየራሳቸውም፡ በጦር ሜዳው ላይ በጭካኔ እየተሠየፉ መውደቃቸው ይታወቃል።

"አዎን! አኹንም፡ የቅርቦቹን አጼዎቻችሁን ዝክረ-ነገር ባጭሩ ለመጠቃቀስ ያህል፡ ቴዎድሮስ፡ በዮሓንስ መሪነትና ግብረ-ዐበርነት፡ በወራሪነት ከመጣበት፡ የእንግሊዝ ጦር ጋር ሲዋጋ፡ ለድል ባለመብቃቱ አዝኖና 'እጄን፡ ለጠላት አልሰጥም!' ብሎ፡ ራሱን፡ በቆራጥነት ገደለ። ተክለ-ጊዮርጊስም፡ በጦር ኃይሉ ተመክቶ፡ በአማቱ፡ በዮሓንስ ላይ በመዝመቱ፡ በብቀላ ጭካኔ፡ የዓይን ብርሃኑን እስከማጣት ደርሶ፡ በሥቃይ ሞተ። ዮሓንስም፡ 'በሠፈሩት ቁና፡ መሠፈር አይቀርም!' እንደምትሉት፡ ከሱዳን የደርቡሽ እስላሞች ጋር ሲዋጋ፡ በሰማዕትነት፡ አንገቱን ተቀላ። ምኒልክም፡ በዮሓንስ ላይ በፈጸመው ደባ፡ መላ አካሉን ተጎድቶ፡ በኀዘን ዐረፈ። ኢያሱም፡ ለአንዳች ቍም-ነገር ሳይበቃ፡ በእሥር እንዳለ፡ 'ሞተ!' ተባለ። ዘውዲቱም፡ በኀዘንና በሠቀቀን ተቆራምዳ ያሳለፈችው ኑሮዋ አንሶ፡ ስለእምነቱ፡ በጦር ሜዳ ላይ ሲዋጋ፡ በደረሰበት የግፍ ግድያ የሞተውን የባሏን መርዶ ሰምታ፡ በዚህ ምክንያትና በሕክምና ሰበብ፡ 'ዐረፈች!' ተባለ።

"የመጨረሻው አጼ፡ ኃይለ-ሥላሴም፡ ፍጹም አስተማማኝና ንጹሕ የኾነውን፡ የእኛን፡ **የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን፡** መለኮታዊና ኪዳናዊ የእንክብካቤ ጥበቃችንን ንቆና አቃልሎ፥ ጥሎና ክዶ፡ በባዕዳን ጠላቶቹ ዓለማዊና ሥጋዊ ቃል ኪዳን መታመኑ አንሶት፡ የእነርሱን የብልጠት ፈሊጥ በመከተል፡ የገዛ ወገኖቹ የኾኑትን፡ ሕዝቦቹን እንኳ ለማመን ባለመቻሉ፡ ለራሱና ለቤተሰቡ፥ ለቤተ-መንግሥቱና ለአገዛዙ ደኅንነትና ጥበቃ 'ያስፈልጉኛል!' ያላቸውን፥ ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ የሚጠይቁትን፡ የስለላና የጦር ሥጋውያት ኃይላትን፡ ከክብር ዘበኛውና ከሕግ ዘበኛው፥ ከብሔራዊ ጦሩም አንሥቶ፡ 'የምድር ጦር'፥ 'የአየር ኃይል' እና 'የባሕር ኃይል' እስከተባሉት፥ እያንዳንዳቸው፡ በየዘርፋቸው፡ በዘመናዊው የስለላና የጦር መሣሪያ ትጥቆችን እስከተሚሉት፡ የነጭ ለባሽና የወታደር ተቅዋማት ድረስ፡ የራሱን ታላቅ የስለላና የጦር ሠራዊት ድርጅቶችን አቋቁሞ ይገዛ እንደነበረ ይታወሳል።

"ታዲያ! ኃይለ-ሥላሴ፡ መለኮታዊና ኪዳናዊ የቅዱሱን ኪዳን ውሉን አፍርሶ፡ 'League of Nations' ይባል ከነበረው፡ ከዚያ፡ ከ"ዓለም አሕዛብ ማኅበር" ጋር በመወገኑ፡ በእርሱና በእነዚሁ ተባባሪዎቹ ላይ፥ በግብረ-ዐበራቸው አሜሪካም ላይ ሳይቀር፡ በፋሺስቱ ኢጣልያዊ ካቶሊክ፡ በሙሶሊኒና በናዚስቱ ጀርመናዊ ፀረ-ማርያም፡ በሒትለር፥ እንዲሁም፡ በአረማውያኑ የጃፓን ጦረኞች እየተመራ በተካኼደው፥ 'ኹለተኛው የዓለም ጦርነት' በምትሉት፡ በታላቁ ፍጅትና ዕልቂት፡ የደረሰው አሠቃቂ ፍጻሜ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ፡ የማያዳግም ትምህርት ሳይኾነው ቀርቶ፥ እንዲያውም፡ ቀድሞ፡ ለአጼነት ወዳበቃችው፥ ኋላም፡ በኪዳነ ምሕረቷ፡ ይቅር ብላው፡ ተባርሮ ከሸሸበት ስደቱ፡ ወዳገሩ መልሳ፥ በዙፋኑም ላይ አደላድላ ወዳስቀመጠችው፡ ወደእኛዋና ወደራሱ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**፡ በእውነተኛ ንስሓ ሊቀ ርብና ሊማጸን፥ በእርሷም ሥርዓት እየተመራ ሊኖ ርና ሕዝቤን ሊያስተዳድር ሲገባው፣ ነገር ግን፡ እንደገና፡ ያንኑ፡ እንደዚያ ያለውን፡ የጦር ድርጅት፡ እንደገና መልሶ ማቋቋሙ፡ እናንት ልጆቼን፥ እናንት ሕዝቤን፥ እናንት ሰብአውያን ፍጡሮቼንም ሳይቀር፡ አያስደንቃችሁምን!? አያስገርማችሁምንስ!? አዎን! በእጅጉ፡ ያስደንቃል። በእጅጉም፡ ያስገርማል።

"ታዲያ! አኹንም፡ የኃይለ-ሥላሴ፡ ጠቅላላና የመጨረሻ ፍጻሜው፡ ከቶ፡ ምን ኾኖ ተገኘ!? ከእኛዋ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ይልቅ፡ ይኼ፡ የእኔው 'ይሻለኛል! ይበልጥብኛል!' ብሎ፡ በቤተ-ሕዝቡና በቤተ-ምልክናው፥ በቤተ-ክህነቱም ተባባሪነት ያቋቋመውና የተማመነበት፡ ራሱ፡ የስለላውና የጦሩ ድርጅት፡ በእርሱ ላይ በማመፅ፡ በክብር ዘበኛው አዛTh፡ በመንግሥቱ ንዋይና በፀጥታ ጥበቃው ኀላፊ፡ በወርቅነህ ገበየሁ፥ በሕግ ዘበኛው አዛTh፡ በጽጌ ዲቡም መሪነትና አቀነባባሪነት፡ የመጀመሪያው የመፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ ተካኼደበት።

"ከመጨረሻው ውድቀቱ በፊት፡ ጥቂት ቀደም ብሎ የተካኼደውና እንዲከሽፍ ያደረግንለት፡ ይኸው ሙከራ፡ ብዙ የእርስ በርስ ደም የፈሰሰበትና የግፍ ግድያ የተፈጸመበት ሲኾን፡ መደምደሚያ ማስጠንቀቂያ ይኾነው ዘንድ፡ በእኛ በኩል የቀረበለት፡ መልካም የንስሓ ዕድል ነበር። ነገር ግን፡ አኹንም፡ ሊጠቀምበት ባለመፈለጉ፡ በእርሱ፡ በኃይለ-ሥላሴና በመሰሎቹ፥ እንዲሁም፡ በተባባሪዎቹ መሥሪያ ቤቶች ላይ፡ ምንም ዓይነት የመሻሻል ውጤትን ማምጣት ያልተቻለ መኾኑ በተረጋገጠ ጊዜ፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ፡ ተመሳሳዩ፥ ነገር ግን፡ ካለፈው የባሰው የቅጣቱ ሠይፍና የጥፋቱ ማዕበል፡ ራሱ ካቋቋመውና ይመራው ከነበረው፡ ከዚያው፡ ከስለላውና ከጦሩ ድርጅት፡ ድንገት ደርሶ አጥለቀለቀው። እርሱም፡ "ደርግ" በሚል ስያሜ የታወቀው፡ ወታደራዊ ቡድን ነው።

"ይኸው ቡድን፡ ራሱን፡ በፀረ-እግዚአብሔርነት አደራጅቶና ሰይጣናዊ ማንነቱን፡ በይፋ አሳውቆ፥ በፍርድ ፈጻሚነቱም፡ ለኹሉ፡ ዋጋን ለመክፈል፡ የቅጣት ሠይፍን ታጥቆ መምጣቱን ዐውጆ፡ እርሱን ራሱን፡ ኃይለ-ሥላሴን፥ ከቤተሰቡም መካከል አንዳንዶቹን፥ የእርሱ የኾኑትን የቅርብ ዘመዶቹንና አገልጋዮቹን አሥሮና አሠቃይቶ ገደላቸው። የሰውኛ ሕገ-መንግሥቱንና ለሃምሳ ዓመታት ያህል የደከመባቸውን ሥራዎቹንም ኹሉ አፈራርሶ አወደማቸው።

"እኛንና የእርሱ ጭምር የኾነችውን፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡** ለረTከም ዘመናት፡ በአስነዋሪው የአምልኮ ባዕድ ኃጢአቱ ሳይቀር፡ በሥውር ብቻ ሳይኾን፡ በገሃድም ክዶ፡ በእርሷ ላይ ያመፀውና ያመነዘረው፡ ይኼ፡ በስሜ የተጠራው ክፉ ትውልድ፡ ለአገር ደኅንነትና ለሕዝብ ሰላም ጥበቃ 'ይኾነኛል!'፥ ወራሪ የውጭ ጠላትም ቢመጣብኝ፡ ተከላክሎ 'ይመልስልኛል!' ብሎ፡ በኩራት የተመካበት፡ ይኼው፡ የስለላና የጦር ድርጅት፡ ምስጢራዊ ፍላፃውን፡ ወደእርሱ ወደራሱ፡ ወደት ውልዱ አዞረበት፤ ገዳይ የጠብመንጃ አፈሙዙንም ደገነበት። መደገን ብቻ አይደለም፤ ተኮሰበት፤ መተኮስም ብቻ አይደለም፤ ጨፈጨፈውም። ሕፃን፡ ሽማግሌ፥ ሴት፡ ወንድ፥ ኮረዳ፡ ጐልማሳ፥ ምሁር፡ ጨዋ፥ ትልቅ፡ትንሽ፥ ካህን፡ ኳደሬ ሳይል፡ በተለያየ እንግዳ እምነትና ፍልስፍና የተከፋፈሉ አንጃዎችን ፈጥሮና አቋቍሞ፥ በጦር መሣሪያም አስታጥቆ፡ ኹሉን፡ እርስ በርሱ፡ ደም አፋሰሰው፤ አጋደለው፤ አፋጀው፤ አስተላለቀው፤ ለአራዊትና ለስደት ም ዳረገው።

"ያን የሚያህል የስለላና የጦር ድርጅት፥ የመሣሪያ ክምችትና የሠራዊት ብዛት፡ የውጭ ወራሪ ጠላትን መክቶ በመመለስ፡ የነጻነት ዋስትናን ለማስከበር መዋሉ ቀርቶ፡ እንዳለ፥ በሙሉ፡ የእርስ በርሱ መጠፋፊያና የራሱ የሕዝቡ መጫረሻ ኾኖ እንዲያገለግል ተደረገ። አዎን! ለሕዝቤ፡ የገዛ ምድሩ፡ የጦር ሜዳ ኾኖለት፡ ሥጋው፡ እንደቅርጫ ተተልትሎና ደሙ እንደጎርፍ ፈስሶ፥ ሬሳው፡ በመቃብር የማረፍን ዕድል እንኳ ሳያገኝ፡ በያለበት ወድቆና በስብሶ፤ ለአራዊት ምግብነት ተዳረገ።

"የራሱ የደርግ አወዳደቅና ፍጻሜው፡ በዚሁ የጦርነትና የዕልቂት መልክና ይዘት፥ እንዲያውም፡ ከዚህ በባሰና በከፋ ኹኔታ ቀጥሎና አብቅቶ እያለ፡ በባዕዳኑ የጦር ትጥቅና የገንዘብ፥ የዕውቀትና የእምነት ድጋፍ የተደረገላቸው፤ አኹንም፡ እየተደረገላቸው ያሉት፡ እነዚህ፡ የገዢነት ሥልጣኑን፡ በጦር ኃይል አሸንፈው፡ ከደርግ የተረከቡት፡ የዛሬዎቹ ተዋጊ ሰብአውያን ፍጡሮቼ፡ በዚህ፡ በስለላውና በጦርነቱ ረገድ፥ በሌላውም ኹሉ፡ እያካኼዱ ያሉት፡ ሥውር አሠራርና ግልጽ ተግባር፡ ካለፉት አገዛዞች ይልቅ፡ በባሕርዩ፡ እጅግ የተራቀቀና በግዝፈቱ እጅግ የከበደ ኾኖ፡ ቢበልጥ እንጂ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ፡ የሚያንስ አይደለም።

"ይልቁንስ፡ በእነዚህ፡ በዛሬዎቹ ያገር መሪዎች የአገዛዝ ጊዜ፡ በዚህ በተነሣንበት፡ በስለላውና በጦርነቱ አደረጃጀትና አሠራር ረገድ፡ እየተካኼደ ያለው ኹኔታ፡ እጅግ አሳሳቢ ወደኾነ፡ የጥፋት ደረጃ እያደገ የመኼዱን ነገር፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ አግባብ ይኾናል፤ ይኸውም፡ ቀደም ባለው፡ በተለይ፡ በኃይለ-ሥላሴ የሥልጣን ዘመን፡ ሊሠራበት ተጀምሮ የነበረው፡ ይኸው፡ የስለላውና የጦሩ ድርጅት፡ በስሜ በታወቀችው፡ በዚችው፡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ መጠሪያ፡ ካገር አልፎ ተርፎ፡ "የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት" እና "የአፍሪቃ አንድነት" ለተባሉት ፀረ-እግዚአብሔር ተቋሞች፡ ከመሥራችነትና ከቋሚ አባልነት ባለፈ መልክና ይዘት፡ የስለላና የጦር ወታደሮቿ፡ በእምነትና በገንዘብ ሳይቀር እየተገዙ፥ የእነዚሁ ድርጅቶች ቀንደኛ መሣሪያ በመኾን፡ የግድያውና የዕልቂቱ ሰይጣናዊ ዓላማቸው፡ ንቁ አገልጋዮች ኾነው መገኘታቸው ነው።

"በአኹኑ፡ በመጨረሻው ወሳኝ ዘመን ላላችሁት፡ ልጆቼና ሕዝቤ፥ ሰብኣውያንና ሰብኣውያት ፍጡሮቼም ኹሉ፡ የምላችሁን፡ ይህን የተለየ ቃል፡ ላንዲት አፍታ፡ በተለየ ንቃትና ትኵረት፡ አዳምጡኝ! እስኪ፡ በማስተዋልም ተመልከቱት!

"ባለፈው፡ በኹለት ሺህኛው ዓመተ-ምሕረት መባቻ [መግቢያ] ላይ፡ ከሺህ ዓመት እሥራቱ፡ ለጥቂት ጊዜ የተፈታው ዲያብሎስ፡ እንዲህ፡ የሚመራውና የእርሱ ተከታዮች በኾኑ የዓለም መንግሥታት የሚካኼደው፡ **ሦስተኛው የዓለም የሃይማኖት ጦርነታችሁ፡** እነሆ፡ ምድራችንንና በላይዋ የሚኖረውን፡ መላውን፡ ሰብኣዊ ፍጡራችንን፥ ሌላውንም ፍጥረታችንን ኹሉ፡ ነበልባሉ፡ እያቃጠለው፥ ማዕበሉም፡ እያጥለቀለቀው ይገኛል። ይኸውም፡ በአንድ ወገን፡ በግዙፉ ሥጋ በኩል የሚደርሰው፡ የሞቱና የዕልቂቱ፥ የረኃቡና የስደቱ ማዕበል ሲኾን፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በረቂቆቹ ነፍስና መንፈስ በኩል የሚመጣው፡ የድንጋጤውና የፍርሃቱ፥ የጭንቀቱና የሥጋቱ ነበልባል ነው። ይህንም ሥቃይ፡ እያንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡር፣ ሴቱም፥ ወንዱም፡ በእየራሱ የሚያውቀው ከመኾኑ ጋር፤ ይህ ፈተናና መከራ ያልደረሰበት ግለሰብ ካለም፡ በገሃድ ሊመለከተው እንደሚቻለው ይታመናል።

"እንዲያው ለመኾኑ፡ የእኛ የፈጣሪያችሁ ሀብት በኾነውና **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡** በበላይነት በምትመራው፥ በምትመግበውና በምታስተዳድረው፥ በምትጠብቀውና በምትቆጣጠረው፡ በዚህ፡ በመላው፡ የምድር ፍጥረተ-ዓለማችን ላይ፡ ዲያብሎስና ጭፍሮቹ የሰዎች መንግሥታት፡ እንደባለቤት ኾነው፡ እንዲህ፡ በክፉው የጦርነትና የጥፋት ዘመቻቸው ሲጨፍሩበት፡ እንዴት ዝም ይባል ነበር? ዝም አይባልም ነበር።

"ነገር ግን፡ ይህን የመሰለው ጥቃት ሊደርስ የቻለው፡ እናንተ ሰብኣውያንና ሰብኣውያት ፍጡሮቻችን፥ ይልቁንም፡ በስሜ፡ እየራሳችሁን፡ 'ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!' የምትሉት ወገኖች፡ ከደካማነታችሁና ካለማስተዋላችሁ የተነሣ፡ በቅዱሱ ኪዳናችን ላይ፡ ታላቁን የክህደትና የዓመፅ፥ የክፋትና የአምልኮ አመንዝራነትን ኃጢአት ፈጽማችሁ በመገኘታችሁ ምክንያት አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

"የክፋትና የጥፋት መሣሪያ በኾነው፡ ይህን በመሰለው፡ አሠቃቂ ጦርነት፡ ምድራዊው ፍጥረተ-ዓለም፡ በሚማስንበትና በሚሠቃይበት፡ በቀደመው ኾነ፡ በዚህ ዘመን፥ ለወደፊቱም ጭምር፡ ስለፍጥረተ-ዓለማቱ ደኅንነትና ሰላም ስትል፡ ምንጊዜም፡ **"እጆቿን ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!"** የተባለችው፡ ይህችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፥ እርሷም፡ እኔ፡** በማናቸውም ዓይነት ጦርነት መካከል፡ ጣልቃ ገብታ፡ ጦርነቱን ልታስቆም፥ ተዋጊዎችንም፡ ልታስታርቅ የሚገባት፡ በምድር ላይ፡ ሌላ ማንም መሰል የሌላት፡ ብቸኛዋ፡ የዓለሙ አስታራቂ ሽማግሌ፡ እርሷ ብቻ መኾኗ፡ በተቃዋሚዎቿ ዘንድ ሳይቀር፡ ሊታወቅ የሚገባ እውነታ ነው። ይህም እውነታ፡ በአረማውያኑና በአይሁዳውያኑ፥ በክርስቲያኑና በእስላሙ፥ እነርሱን በመሰሉ፡ በዓለሙ የሃይማኖት ስደተኞችም ዘንድ፡ ተፈጽሞ የታየ ስለኾነ፡ የተረጋገጠ ነው።

"ከዚህ የተነሣ፡ እንዲያውም፡ ዛሬ፡ ይህን፡ የባለቤትነትና የባለሙያነት ተልእኮዋን እንድትፈጽም ልትጠየቅ የሚገባት፡ እርሷ ብቻ ስትኾን፡ በፀረ-እግዚአብሔር ተቃዋሚዎቿ በኩል፡ የሠረፀውና የሚሠርፀው አሳብ፡ ሰይጣናዊ ካልኾነ በቀር፡ እርሷን፡ ከምድር ገጽ ለማስወገድ፥ የጥፋት ዘመቻንም፡ በእርሷ ላይ፡ በሥውርና በይፋ፡ ያውጁባት ዘንድ፡ ፍላጎቱ፡ ለምን፥ እንዴትስ፡ በየልቦናቸው ሊያድርባቸው እንደቻለ ለማወቅ፡ በእኛ፡ በፈጣሪዎቹ ዘንድ ሳይኾን፡ በፍጡራኑ ዘንድ ይከብዳል።

"በስሜ፡ **'ኢትዮጵያ'** የተባለችው፡ ይህችው አገራችሁ፡ ሲፈጸምባት የኖረው፡ ይህ ኹሉ ጥቃት ሳያንሳት፡ በአኹኑ ጊዜ ደግሞ፡ በስሟ የተጠራችሁት፡ እናንተው ራሳችሁ ዜጎቿ፡ ብላችሁ! ብላችሁ! የፈጸማችሁባትን የበደል በደል ልንገራችሁ!

**"ራሷን፡ ከተዋጊ ጦረኞች መካከል፡ ያሰለፈች ብቻ ሳትኾን፡ በዚሁ ሙያ፡ ከኹሉ በላይ የሠለጠነችና የላቀች መኾኗን በማስመስከር፡ ለዚህ ግልጋሎት፡ እንዲህ፡ የፀረ-እግዚአብሔር መንግሥታትና የድርጅቶቻቸው ምንደኛና ቅጥረኛ እስከመኾን ደርሳ፡ ግልጋሎቷን እንድታበረክት አድርጋችሁ፡ ለጦርነት አራማጅነቱ ደረጃ፡ 'ተፈላጊዋና ተመራጯ፥ ቀዳሚዋና ቀንደኛዋ፡ ኢትዮጵያ ናት!' ለመባል አበቃችኋት!**

"አዬ ልጆቼ! ይህን ታስሙኝ? ይህንም ታሳዩኝ? ይህን ዓይነቱን ጥቃት፡ በቀድሞዎቹ ልጆቼ ዘንድ ያልሰማሁትና ያላየሁት ስለኾነ፡ ከእናንተም፡ ከዛሬዎቹ፡ የምጠብቀው አይደለምና፡ ፈጥናችሁ፡ በንስሓ፡ ወደእኔ፡ ወደእናታችሁ ተመለሱ።

"እኔም፡ 'ኢትዮጵያ' የሚለው ስሜ፡ እንዲህ ሲረክስ፥ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕም፡ ለእናንተ፡ ለፍጡሮቹ፡ ባለው ፍጹም ፍቅሩ የተነሣ፡ ከእኔ የለበሰውን ሰውነቱን፡ በመስቀል ላይ ዕርቃኑን አስቸንክሮ፡ በቆረሰው ሥጋውና ባፈሰሰው ደሙ መሥዋዕትነት፡ በተቤዣችሁ፡ በእናንተ ፍጡሮቻችን ላይ፡ ዲያብሎስ፡ እንዲህ ሠልጥኖ፡ ይህን በመሰለው አሠቃቂና ሰይጣናዊ በኾነው ጦርነቱ፡ እንዲህ እንድትተላለቁ ሲያደርግ እያየን፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እኔም፥ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕም፡ ዝም አንልም። **የዛሬ ኹለት ሺህ ስምንት ዓመት፡ የተፈጸመውንና የታወጀውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ምሕረታችንን፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ የመንፈስ ቅዱስ ግብር አማካይነት፡ በእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡራችን ሰውነት ውስጥ፡ በፍሬያማው ሃይማኖታዊው ምግባር፡ እንዲከሠት እናደርገዋለን።**

"በዚያን ጊዜም፡ አዎን! ቀደም ብዬ የጠቀስሁትን ቃል፡ አኹንም ልድገመውና፡ **'ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም!**

"'ፍጥረተ ዓለሙ፡ በአንቺ ዳነ! በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!' የሚለው የታማኞች ልጆቻችን የዝማሬ ቃል፡ እውን መኾኑን፡ ይህንና ሌሎቹንም፡ የቃለ ዐዋዲ ምዕዳኖቼን ለመስማት ፈቃደኞች ለኾናችሁት፡ ለእናንተና ለፍጥረተ-ዓለሙ ጭምር እናረጋግጣለን። **በዚያም ሰውነት ውስጥ፡ በሰይጣናዊው የጦርነት ቦታ፡ እግዚአብሔራዊው ሰላም ተተክቶ ይሰፍናልና። በዚያን ጊዜ፡ ድሉ፡ የእናንተና የእኛ ይኾናልና።**

"እስካኹን፡ በመጠኑም ቢኾን፡ የዘረዘርሁላችሁን፡ ይህን አሳዛኝ ኹኔታ ያነሣሁት፡ በይበልጥ፡ የጦርነትን ነገር በሚመለከተው ርእስ ላይ ብቻ  በማተኰር፡ በጸጥታው ጥበቃና በጦሩ ድርጅት በኩል የደረሰውን፡ ለማውሳት ያህል እንጂ፡ ሰው-አመጣሹ 'ድርቅና ረኃብ፥ ቸነፈርና ደዌ፥ መፈናቀልና ስደት ' እየተባለ፥ ሳይኖርም፡ እንዳለ እየተደረገ፡ የሚሰማው፡ 'የተፈጥሮ' ተብዬው ችግር፡ ከዚህ ጋር፡ በተጓዳኝነት ይደርስና ይካኼድ የነበረ፥ አኹንም፡ ያለ መኾኑ እንዳይዘነጋ  ያስፈልጋል።

"ታዲያ! የእኛ፡ **የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** የኾነውን፡ መልካሙን የሕይወት ሥርዓት፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ አለመከተልና በንቀት አግልሎ መተው፥ የዲያብሎስ የኾነውንም፡ የሥውር ተንኰሉንና የግልጽ ጦርነቱን መንገድ መከተል፡ ፍጻሜው ይህ መኾኑን፡ ልጆቼ! የምታውቁት፡ እንግዴህ መቼ ነው? <u>ዛሬ መኾን ይኖርበታል።</u>

"ደግሞስ፡ ይኼን የመሰለው አሠቃቂ ድርጊት፡ በመላዋ ዓለም ያሉ፡ አሕዛቡ ኹሉ፥ "ሕዝቤ" የምላችሁ፡ እናንተም ሳትቀሩ፡ <u>**እያመለካችሁት**</u> ያላችሁት፡ የዚያው፡ የዲያብሎስ እንጂ፡ "የእኛና **የእግዚአብሔርዋ መንግሥታችን፡ የኢትዮጵያ አለመኾኑን የማያውቅ** ይኖራልን? አይኖርም። ከልጄ ከወዳጄ፡ ከእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የመስቀልና የሞት ቤዛነት የተነሣ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዘንድ፡ ሰላም እንጂ፡ ጦርነት እንደማይታወጅባት፤** ሕይወትን ማዳን እንጂ፡ የሞት፥ ወይም፡ የስቅላት ፍርድ እንኳ እንደማይሰጥባትም ስለሚታወቅ፡ ይህን የመሰለው አስተሳሰብና ድርጊት፡ በእኛና በመንግሥታችን ዘንድ፡ ከቶ የሚታለም  አይደለም።

"ይኼ ኹሉ ሰይጣናዊ ተግባር፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን የመመሪያ እምነትና ሥርዓት ተነሣ፡** እንግዴህ ወዲህ ፈጽሞ የሚያበቃ  ይኾናል።"

\+ \+ \+

## <u>ማስታወሻ</u>።

የመለኮታዊው ቃለ-ዐዋድ ባለቤት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ይህን የበዓለ-ኢትዮጵያን መልእክት በሚመለከት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ለኢትዮጵያ ልጆቿ የሰጠችው መመሪያ እነሆ፡-

«በበለጠ የተብራሩትና የተሟሉት፡"የሃይማኖት፤ የኪዳነ ቃል፡ የስባሔ ለእግዚአብሔር እና የሱላሜ፡ ለድንግል ማርያም" የተባሉት፡ አራቱ፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መደበኞች ጸሎቶቻችሁ፡ እንደተለመደው፡ በመለኮታዊው የዐዋጅ ቃሌ፡ እንዲደርሷችሁ ከማድረጋችን በፊት፡ ይኼ፡ የበዓለ-ኢትዮጵያ መልእክት፡ በበዓሉ መቃረብ ምክንያት፡ ቀድሞ እንዲወጣ በማስፈለጉ፡ እነዚሁ፡ በበለጠ የተብራሩትና የተሟሉት ጸሎቶቻችሁ፡ በበዓሉ ሥርዓት-ጸሎት ወስጥ ተካትተዋል።

"ይህ፡ የበዓለ-ኢትዮጵያ መልእክት፡ እንደመለኮታዊውቃለ-ዐዋድ ኹሉ፡ ከእኛ የተላለፈ፤ የእኛው ቃል መኾኑን፤ የእኔና የልጄ የወዳጄ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ማኅተም፡ በአርእስቱ በሠፈረበት፡ እግዚአብሔራዊ ሰሌዳችን ላይ ተጽፎ መውጣቱ፡ ይህን እውነታ አረጋግጦ አሳውቋችኋል።